# የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ

## ዘጠነኛ ክፍል


አዘጋጆች፡-

ደመላሽ ዓለሙ

ሳህሉ አክሊሉ

የሺጥላ መንግሥቴ

አርታኢ፡-

የኋላሸት ደሳለኝ

ገምጋሚዎች፡-

መኮንን አስማማው

ተስፋዬ ወ/ሚካኤል

ወርቁ አድማስ



AL GHURAIR
Printing and Publishing LLC

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

## ምስጋና

የዚህ መጽሐፍ ዲዛይን ህትመትና ስርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ኘሮጀክት (GEQIP) አማካኝነት ነው:: የኘሮጀክቱ ዋና ዓላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ለGEQIP የዋለውን ገንዘብ ያገኘው በብድር/በእርዳታ ሲሆን ብድሩን/ እርዳታውን የሰጡት ዓለምአቀፍ የልማት ማህበራት (IDA)፣ ፋስት ትራክ ኢንሼቲቭ ካታሊቲክ ፈንድ (FTI CF) እና ሌሎችም የልማት አጋሮች ማለት የፊንላንድ፣ የኢጣሊያ የልማት ማህበር፣ የኔዘርላንድና የታላቋ ብሪታኒያ የእርዳታ ድርጅት አለምአቀፍ የልማት ዋና ክፍል (DFID) ናቸው::

ሁሉንም በዝርዝር መጥቀስ የማይቻል በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ይህ የተማሪ መጽሀፍና የመምህር መምሪያ እውን እንዲሆኑ ያልተቆጠበ ድጋፍቸውን ሰጥተዋል:: በዚህም ትምህርት ሚኒስቴር ምስጋናውን ያቀርባል::

© በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
1ኛ እትም፣ 2004 ዓ.ም
ISBN 978-99944-2-253-1

**የአል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 5613**
**ዱባይ፣**
**የተባበሩት የአረብ ኤሜሬት**

**ከኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር**
**የፖ.ሳ.ቁጥር 100767**
**አዲስ አበባ**
**ኢትዮጵያ**

ጋር በመተባበር ይህን መጽሐፍ ለኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅተው አትመው፣ አሰራጭተዋል::

ሁሉም የህትመት መብቶች ተከብረዋል::

የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም እንደማይቻል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዲራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የኮፒራይትና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ 10ኛ አመት ቁጥር 55 አዲስ አበባ ጁላይ 19, 2004 ይከለክላል::

የስዕሎችን የኮፒ ራይት መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል:: ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን::

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**


**መግቢያ** ........................................................................ i

**ምዕራፍ አንድ:-** ቋንቋና ህብረተሰብ ...................................... ፩

**ምዕራፍ ሁለት:-** ስነ-ቃል ................................................... ፲፱

**ምዕራፍ ሦስት:-** ቤተ-መጻሐፍትና ሥነ-ጽሑፍ .......................... ፴፫

**ምዕራፍ አራት:-** ልቦለድ ................................................... ፶፫

**ምዕራፍ አምስት:-** ስነግጥም ................................................ ፷

**ምዕራፍ ስድስት:-** ተውኔት .................................................. ፺፯

**ምዕራፍ ሰባት:-** የአካባቢ ገለጻ ........................................... ፻፳

**ምዕራፍ ስምንት:-** መገናኛ ብዙሃን ..................................... ፻፴፫

**ምዕራፍ ዘጠኝ:-** ምርጥ ንግግር ........................................ ፻፵፯

**ምዕራፍ አስር:-** ክርክር .................................................... ፻፸፬

ተጨማሪ የንባብ መጻሕፍት ....................................... ፻፹

ማጣቀሻ መጻሕፍት ................................................. ፻፹፩

ቃላት ከነፍቻቸው .................................................. ፻፹፪

ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከነፍቻቸው ................................. ፻፹፫

# መግቢያ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎች የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ማጕልበትና የሥነጽሑፍና የሥነልሳን እውቀትን ማዳበር ናቸው:: እነዚህ ዓላማዎችም በመርሀ-ትምህርቱ ላይ በግልጽ ሰፍረው ይገኛሉ::

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ከሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች መካከል ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የመማሪያ መጽሐፍ ነው:: የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ደግሞ በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች በየጊዜው ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል:: አንደኛው የመርሐ ትምህርቱን አላማዎች በማስፈፀም ረገድ የመፅሐፉን አቅም ለማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መርሀ ትምህርቱ ላይ ማሻሻያ ወይም ለውጥ ሲደረግ ነው::

ይህ የ፱ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ በአዲስ መልክ እንዲዘጋጅ የሆነበት ምክንያትም በ፳፻፩ ዓ.ም. መርሀ ትምህርቱ እንዲሻሻል በመደረጉ ነው:: መጽሐፉ መርሀ ትምህርቱ ትኩረት የሰጠባቸውን ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ እንዲያካትት ጥረት ተደርጓል:: ምንባቦቹ ማብራሪያዎቹና መልመጃዎቹ መርሀ ትምህርቱን መነሻ በማድረግ በክሂልና በእውቀት ዘርፍ ተደራጅተው ቀርበዋል::

ምንባቦቹና ማብራሪያዎቹ፣ ግልፅና ሳቢ፣ መልመጃዎቹ ደግሞ አሳታፊ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል:: በየምእራፉ ማብቂያ ዐበይት ነጥቦች በማጠቃለያ መልክ ከመቅረባቸውም በላይ፣ ተማሪዎች የየምዕራፉን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ የሚያመሳክሩባቸው የግንዛቤ ማመሳከሪያ ነጥቦች ተዘጋጅተዋል:: ተማሪዎች በነዚህ ነጥቦች እየተመሩ የትምህርቱን ዓላማዎች በመፈፀም ረገድ በራሳቸው ያሉበትን ደረጃ መገምገምና ጉድለቶቻቸውን ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል:: በመሆኑም መጽሐፉ ትምህርቱን በሚፈለገው መንገድ ለመከታተልና የትምህርቱን ዓላማዎች ለመጨበጥ ያስችላል ተብሎ ይታመናል::

በመጨረሻም ለመጽሐፉ ዝግጅት ጽሑፎቻቸውን ያዋሱንን ሁሉ እያመሰገንን፣ ስለመጽሐፉ ከመምህራን፣ ከተማሪዎችና ከሌሎች የህብረተሰቡ ክፍሎች የሚቀርቡ አስተያየቶችን ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን እንገልፃለን::

# ምዕራፍ አንድ

## ቋንቋና ህብረተሰብ

**የምዕራፉ ዓላማዎች:- ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- የቋንቋን ምንነት ታስረዳላችሁ::
- የቋንቋ አገልግሎትን በቃልና በጽሑፍ ትዘረዝራላችሁ::
- ያዳመጣችሁትንና ያነበባችሁትን ሀሳብ በራሳችሁ አባባል እንደገና ትገልጻላችሁ::
- እያዳመጣችሁና እያነበባችሁ ዋና ዋና ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ ትይዛላችሁ::
- ከጽሑፍ ወይም ከንግግር ውስጥ የመንስኤና የውጤት ሃሳቦችን ለይታችሁ ታወጣላችሁ::
- ለቃላት ቀጥተኛና አገባባዊ ፍች ትሰጣላችሁ::

## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

፩. መምህራችሁ በሚነግሯችሁ መሠረት፣ ቡድን መስርታችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

1. ቋንቋ ምንድን ነው?
2. ቋንቋ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት ምንድን ነው?

፪. በውይይታችሁ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በቡድን መሪያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

፫. ከዚህ በታች በአንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሆኑት መምህርት ነኢማ ያሲን፣ መምህር ከተማ ዋቆና መምህርት ትብለጥ ተሰማ "የቋንቋ ምንነትና አገልግሎት" በሚል ርዕስ ያካሄዱት ውይይት በጽሑፍ ቀርቦላችኋል። ውይይቱን ካነበባችሁ በኋላ፣ ከምንባቡ ያገኛችኋቸውን ሐሳቦች በውይይታችሁ ካነሳችኋቸው ሐሳቦች ጋር አስተያዩ።

## የቋንቋ ምንነትና አገልግሎት

***የወይይቱ መሪ፣ መምህርት ነኢማ:-***

የዛሬውን ውይይት የመምራት ተራው የኔ እንደመሆኑ፣ በቅድሚያ የውይይት ሰዓታችንን ጠብቃችሁ እዚህ በመገኘታችሁ አመሰግናለሁ። ዛሬ "ቋንቋና ህብረተሰብ" በሚል ርዕስ እንወያያለን። ስለዚህም ውይይ ታችንን በቋንቋ ምንነት ላይ ሐሳብ በመለዋወጥ ብንጀምር ጥሩ ይሆናል።

***መምህር ከተማ:-***

ቋንቋ ከሰዎች አንደበት **የሚፈልቅ** ድምጻዊ መግባቢያ ነው። ሰዎች በቋንቋ ተጠቅመው ሐሳባቸውን ለሌሎች ሰዎች ያጋራሉ። የሌሎችንም

ሐሳብ እንዲሁ በቋንቋ አማካይነት ይቀበላሉ፡፡ አሁን እዚህ፣ እኔ ስለቋንቋ ምንነት የምናገረው በቋንቋ አማካይነት ሲሆን፣ እናንተም ሀሳቤን የምት ቀበሉትና ሀሳብ ሲኖራችሁ የምትገልጹት በቋንቋ ነው፡፡ ስለሆነም ቋንቋ ድምጻዊ የሆነ፣ ኢ-ደመነፍሳዊ መግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡

**ተማሪዎች! እስቲ እዚህ ላይ ንባባችሁን ገታ አድርጉና በተከታዩ ጥያቄ ላይ ሀሳብ ተለዋወጡ፡፡**

**ቋንቋ ድምጻዊ መግባቢያ ነው ካልን፣ እንስሳትም ድምጽ በማውጣት መልዕክት ይለዋወጣሉ፡፡ ይህንን የእንስሳት ድምጻዊ መግባቢያ ቋንቋ ልንለው እንችላለን? መልሳችሁን በማስረጃ አስደግፋችሁ ተናገሩ፡፡**

ሐሳቤን ግልጽ ለማድረግ ያህል፣ በድምጽ አማካይነት እንስሳትም ይግባባሉ፡፡ ለምሣሌ፣ **ከግጦሽ** መስክ የዋለች ላም **አመሻሽ** ላይ ወደ ቤት ስትመለስ ከጥጃዋ ጋር ከመገናኘቷ በፊት “እምቧ” ትላለች፡፡ ጥጃውም ቢሆን የናቱን መምጣት አውቆ በድምጹ ምላሽ ይሰጣል፤ ካልታሰረም ወደ እናቱ ይሮጣል፡፡ ይህ እንግዲህ እንስሳትም ድምጽ በማፍለቅ እንደሚግባቡ ያሳያል፡፡ ነገር ግን፣ የሰው ልጅ ቋንቋ እንደ እንስሳት ደመነፍሳዊና የማይለወጥ አይደለም፡፡ ይልቁንም **ተለዋዋጭና** በስርዓት **የሚሰደሩ** ድምጾች ስብስብ ነው፡፡

ቋንቋ ልክ እንደሰው ይወለዳል፡፡ የተናጋሪውን ህብረተሰብ ማህበራዊ ባህላዊ እድገት ተከትሎ ያድጋል፡፡ በሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋ ተናጋሪዎችን ሲያጣ ደግሞ እሱም አብሮ ይጠፋል፡፡ ነገር ግን፣ ያ ቋንቋ የመጨረሻውን ተናጋሪ እስካላጣ ድረስ “ሞተ” አይባልም፡፡ የተናጋሪዎቹን ባህል፣ ታሪክ፣ እውቀት ወዘተ. እንደያዘ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይሸጋገራል፡፡ በዚህ ሂደትም በየጊዜው ወደ ቋንቋው የሚገቡትን አዳዲስ ሀሳቦች ለመግለጽ በድምጾቹ፣ በቃላቱና በአገላለፁ ላይ ለውጥ ሊያስተናግድ ይችላል፡፡

***መምህርት ነኢማ:-***

መምህር ከተማ የቋንቋ ምንነትን በተመለከተ የሰጠው መግለጫ በጣም ጠቃሚ ሀሳቦችን ይዟል፡፡ በውይይቱ ቋንቋ የሰው ልጅ ብቻ ድምጻዊና **ኢ-ደመነፍሳዊ** መግባቢያ መሆኑን አሳይቶናል፡፡ ቀጥሎ ደግሞ በቋንቋ አገልግሎት ላይ ብንነጋገር ጥሩ ይመስለኛል፡፡

***መምህርት ትብለጥ:-***

ቋንቋ እርስ በእርሳቸው የተሳሰሩ ሁለት ተግባራት አሉት፡፡ አንደኛው ሐሳብን ማስተላለፍ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከሚነገረው ሐሳብ ጋር ተያይዞ የሚተላለፈው የተናጋሪው ማንነት ነው፡፡ በሐሳብ ማስተላለፊያነት የሚታወቀው የቋንቋ አገልግሎት ስነ ልሳናዊ ሲሆን፣ ማንነትን የሚያመለክተው አገልግሎቱ ደግሞ ማህበራዊ ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ስለአንድ ጉዳይ ከተናገረ ለአድማጩ የሚያስተላልፋቸው መልዕክቶች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው በቀጥታ ስለጉዳዩ የሰነዘረው አስተያየት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ስለራሱ ማንነት በተዘዋዋሪ መንገድ በአድማጩ ላይ የሚያሳድረው ግምት ነው፡፡

በመሆኑም አድማጩ፣ ተናጋሪው አስተያየቱን ሲሰጥ ከሚሰነዝረው ፍሬ ሐሳብ፣ ከቃላት አመራረጡ፣ ከድምጽ **አወራረዱ** ተነስቶ ስለተናጋሪው ማንነት ከሞላ ጎደል በትክክል መናገር ይችላል፡፡ ይኸውም ተናጋሪው የከተማ ሰው ወይም የገጠር ሰው፣ ወጣት ወይም **አዛውንት**፣ ወንድ ወይም ሴት፣ ገበሬ ወይም ነጋዴ፣ ወዘተ. መሆኑን ወይም አለመሆኑን አድማጩ ሊለይ ይችላል፡፡

***መምህርት ነኢማ:-***

የቋንቋ አገልግሎትን ዘርዘር አድርገን ካየነው ሰፊ ነው፡፡ ሆኖም መምህርት ትብለጥ ጠቅለል አድርጋ በሁለት በመክፈል ስነልሳናዊና ማህበራዊ አገልግሎቱን አስረድታለች፡፡ የዛሬውን ውይይታችንን ከማጠቃለሌ በፊት ተጨማሪ ሀሳብ ካላችሁ መድረኩ ክፍት ነው፡፡

### *መምህር ከተማ፡-*

እኔ መምህርት ትብለጥ ባነሳችው ላይ የምጨምረው አለኝ፡፡ ቋንቋ በማህበራዊ አገልግሎቱ ከግለሰብ አልፎ ባንድ አካባቢ የሚኖሩ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ሰዎችን፣ ያንኑ ቋንቋ ከሚናገሩ በሌላ አካባቢ ከሚኖሩ ሰዎች ለይተን እንድናውቃቸው ያደርጋል፡፡ በመልክኣ ምድር መለያየት ምክንያት በተለያዩ ቦታዎች ተሰራጭተው የሚኖሩ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች በየአካባቢያቸው የተለያዩ ዘዬዎችን ይፈጥራሉ፡፡

አማርኛ ቋንቋን በምሳሌነት ወስደን ብንመለከት፡- በወሎ፣ በሰሜን ሸዋ፣ በአዲስ አበባ፣ በጎጃምና በጎንደር… በስፋት ይነገራል፡፡ ይሁንና በየአካባቢዎቹ የሚነገረው አማርኛ በድምጽ፣ በቃላትና በአባባል ልዩነት ያስከትላል፡፡ የአዲስ አበባ ነዋሪ" ባቄላ" ሲል መንዜው "ባኤላ" ይላል፡፡ ወሎዬው "መሿጫ" ሲል፣ የቀረው አካባቢ "መፋቂያ" ይላል፡፡ ጎጃሜው እንዲሁ "አልበላም" ለማለት "አልበልቶም" ይላል፡፡ በተመሳሳይ አኳኋን ጎንደሬው "ልጅ" ለማለት "አሽከር" ይላል" የአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች በዚህ ዓይነት በየአካባቢያቸው የሚፈጥሩት ዘዬ ከወዴት እንደሆኑ የሚጠቁም መለያ ይሆናቸዋል፡፡ ሆኖም በአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች መካከል የዘዬ ልዩነት መኖር ከመግባባት አያግዳቸውም፡፡

### *መምህርት ነኢማ፡-*

ቋንቋ በማህበራዊ ተግባሩ የግለሰብ ተናጋሪን ማንነት መግለጽ ብቻ ሳይሆን በመልክአ ምድር ተለያይተው የሚኖሩ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች ከወዴት እንደሆኑ እንደሚያሳውቅ ከመምህር ከተማ ሐሳብ መገንዘብ ይቻላል፡፡

የእለቱን ውይይታችን ለማጠቃለል ያህል፣ ቋንቋ ድምጻዊና ኢ-ደመነፍሳዊ መግባቢያ እንደሆነ አይተናል፡፡ ይህ የሰው ልጅ መግባቢያ የሚወለድ፣ የሚያድግና ተናጋሪውን ሲያጣ የሚሞት ከመሆኑም በላይ ተናጋሪዎቹ እስከተገለገሉበት ድረስ ታሪክና ባህላቸውን ይዞ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገር መሆኑን አውቀናል፡፡ ቋንቋ ሁለት ዋና ዋና አገልግሎት እንዳለውም ተነጋግረናል፡፡ እንግዲህ የዚህ ሳምንት ስብሰባችንን እዚህ ላይ እናጠናቅቃለን፡፡

*(መነሻ ሀሣብ፣ ባየ ይማም፣2000፣XI-XII)*

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ:- ንባብ

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ።**

1. ዘዬ ምንድን ነው?
2. የሰው ልጅ ቋንቋ ከእንስሳት መግባቢያ የሚለየው በምንድን ነው?
3. ቋንቋ እንዴት እንደሚያድግ በምሳሌ አስረዱ፡፡
4. የቋንቋን ስነልሳናዊ አገልግሎት ግለጹ።
5. ሰዎች ቋንቋ ባይኖራቸው ኖሮ፣ ማህበራዊ ህይወታቸው ምን ገጽታ ይይዛል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

**፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ፣ ምክንያታችሁን ግለጹ፡፡**

1. ቋንቋ ድምጻዊ መግባቢያ ነው። ማንኛውም ድምጽ ደግሞ እስካግባባ ድረስ ቋንቋ ነው።
2. ቋንቋ በስርዓት የሚሰደሩ ድምጾች ስብስብ ነው፡፡
3. አንድ ቋንቋ "ሞተ" የሚባለው በተናጋሪዎቹ ላይ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋ ሲደርስ ነው።
4. የቋንቋ ስነልሳናዊ አገልግሎት የተናጋሪውን ማንነት ማሳወቅ ነው።
5. ቋንቋ ሀሳብ ማስተላለፊያ ብቻ ሳይሆን መቀበያም ነው።
6. አንድ ሰው ስለራሱ “እንዲህ ነኝ” ብሎ ካልተናገረ በስተቀር፣ ከንግግሩ ተነስተን ስለማንነቱ መረጃ ማግኘት አንችልም።
7. በአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች መካከል የዘዬ ልዩነት መኖር መግባባትን አያግድም።

**፫. ከዚህ በታች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ቃላት ቀርበዋል፡፡ ቃላቱ በምንባቡ ወስጥ ባላቸው አገባብ መሠረት ፍቻቸውን ስጡ፡፡**

**ምሳሌ፡-**

- ያጋራሉ፡- ያካፍላሉ፣ ይገልፃሉ፣ይነግራሉ፤
- የሚፈልቅ፡- የሚወጣ፣ የሚመነጭ

1. ግጦሽ
2. አመሻሽ
3. ኢ-ደመነፍሳዊ
4. ተለዋዋጭ
5. አወራረዱ
6. የሚሰደሩ
7. አዛውንት

## የቃላት አገባባዊ ፍች

አንድ ቃል በተለያዩ አውዶች ውስጥ ሲገኝ የሚኖረው አገባባዊ ፍች እንደየዓረፍተነገሮቹ ይለያያል፡፡ የአንድ ቃል ትክክለኛ ፍች የሚታወቀው በዓረፍተነገር ውስጥ ገብቶ ከሌሎች ቃላት ጋር በመሆን መልዕክት ሲያስተላልፍ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ "ሸረከተው" የሚለውን ቃል ወስደን በተለያዩ ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያለውን አገባባዊ ፍች እንመልከት፡፡

1. ወፍጮው ስለተበላሸ ጤፉን <u>ሸረከተው</u>፡፡
   ፍች፡- ገረደፈው፣ ከካው
2. አጥሩ ላይ የነበረው ምስማር የጫልቱን ቀሚስ <u>ሸረከተው</u>፡፡
   ፍች፡- ቀደደው፣ ተረተረው
3. ወታደሩ ጠላቱን በሳንጃ <u>ሸረከተው</u>፡፡
   ፍች፡- ወጋው

"ሸረከተው" የሚለው ቃል በሦስቱም ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተለያዩ ፍችዎች ወክሏል፡፡

**፬. ለሚከተሉት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት መዝገበ ቃላትን ተጠቅማችሁ ቀጥተኛ ፍቻቸውን ስጡ፡፡**

**ምሳሌ፡-**

ዘዬ- 1. ፈሊጥ፣ የአሰራር መንገድ
2. ልማድ
3. አካባቢያዊ አነጋገር፣ ቀበልኛ፡፡

ሰደረ- ደረደረ፣ በረድፍ አስቀመጠ፣ በተራ አስቀመጠ

1. ህብረተሰብ
2. መስክ
3. በደመ-ነፍስ
4. ማንነት
5. ማህበራዊ
6. ባህል
7. መልክአ ምድር

## ክፍል ሁለት:- ንግግር

**፩. በጥንድ ሆናችሁ ቀጥሎ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ። የደረሳችሁበትን መደምደሚያ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።**

1. ዘዬዎች እንዴት ይፈጠራሉ?
2. በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚኖር የዘዬ ልዩነት መግባባትን አያግድም የሚባለው ለምንድን ነው?

**፪. የሚከተሉት ሐረጐች ከምንባቡ የወጡ ናቸው። የያዙትን መልዕክት በራሳችሁ አባባል አብራሩ።**

1. ማህበራዊና ባህላዊ እድገት
2. የሰው ሥራሽና የተፈጥሮ አደጋ
3. የቋንቋ ማህበራዊ አገልግሎት

## ክፍል ሦስት:- ማዳመጥ

**፩. መምህራችሁ "መደበኛና ኢ-መደበኛ ቋንቋ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል።**

1. እያዳመጣችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ?
2. በጥንድ ከሆናችሁ በኋላ፣ በያዛችሁት ማስታወሻ በመታገዝ የጽሑፉን መልዕክት በራሳችሁ አባባል አንዳችሁ ለአንዳችሁ ተናገሩ።

## የማስታወሻ አያያዝ

እያነበብን ወይም እያዳመጥን ማስታወሻ የምንይዝባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከል ከመድረክ ንግግር፣ በአንድ ጉዳይ ላይ ከሚሰጥ ገለፃ፣ በሬዲዮና በቴሌቭዥን ከሚተላለፉ ኘሮግራሞች፣ ከመጻህፍት፣ ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች ንባብ ማስታወሻ መውሰድ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በየትኛውም ሁኔታና አጋጣሚ ማስታወሻ መያዝ ስንፈልግ የሚከተሉትን ነጥቦች ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡

- ለማስታወሻ መያዣ የሚያገለግል ወረቀትና ብዕር ማዘጋጀት፣
- ሀሳብን ሳይበታትኑ በሚደመጠው ወይም በሚነበበው ፍሬ ነገር ላይ ማሳረፍ፣
- የሚቀርቡትን ዋና ዋና ነጥቦች ባጭር ባጭሩ መመዝገብ፣ (ይህ በቃል፣በሐረግ ወይም በዓረፍተነገር ደረጃ ሊመዘገብ ይችላል፡፡ በየትኛው ደረጃ መስፈር እንዳለበት ለመወሰን እያንዳንዱን ነጥብ በኂላ ምን ያህል አስታውሰዋለሁ? ብላችሁ እራሳችሁን መጠየቅና መገመት ይጠበቅባችኂል?)
- የምታዳምጡትን ወይም የምታነቡትን ሁሉ ሳይሆን፣"ጠቃሚ መረጃ ናቸው" የምትሏቸውን ብቻ መርጦ መመዝገብ
- ማስታወሻ የመያዝ ተግባርን ካጠናቀቃችሁ በኂላ የጻፋችሁትን ማስታወሻ ደጋግማችሁ በማንበብ በትክክል ያልተመዘገበ ካለ ማስተካከል
- ማስታወሻውን ለተገቢው ዓላማ መጠቀም ናቸው፡፡

*(ደበበ ኃይለጊዮርጊስ፣ 1996፣ 660 ተሻሽሎ የተወሰደ)*

**፬. ከዚህ በታች ስለምክንያትና ውጤት የቀረበውን ማስታወሻ ካነባባችሁ በኋላ "የቋንቋ ልደትና ሞት" በሚል ርዕስ በመንስኤና ውጤት የተዋቀሩ አንቀጾችን የያዘ አንድ አጭር ጽሑፍ በንባብ ይቀርብላችኋል፡፡**

1. እያዳመጣችሁ፣ በመንስኤና ውጤት የተገለጹ ሀሳቦችን ብቻ ለይታችሁ በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ፡፡

2. በቡድን ሆናችሁ፣ በተናጠል የመዘገባችኋቸውን በመንስኤና ውጤት የተገለጹ ሀሳቦች ዝርዝር አስተያዩ፤ ባደመጣችሁት መሠረት በትክክል የተወሰዱ ስለመሆናቸው ተወያዩ፡፡
3. በውይይታችሁ የተስማማችሁባቸውን በመስኤና ውጤት የተገለፁ ሀሳቦች ዝርዝር በቡድን መሪያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## ምክንያትና ውጤት

የአንድ ነገር ውጤት ከሱ በፊት በሚኖር ምክንያት ወይም መንስኤ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ተናጋሪ ወይም ጸሐፊ ብዙውን ጊዜ የአንድን ነገር ውጤት ከምክንያቱ ጋር አብሮ የሚገልጽበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ የምክንያትና ውጤት ግንኙነትን ስንመረምር አንድ ምክንያት ብዙ ውጤቶችን ሊያስገኝ ይችላል፡፡ ብዙ ምክንያቶችም እንዲሁ አንድ ውጤት የሚያስገኙበት ሁኔታ አለ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ አንድ ምክንያት ውጤትን ሊያስገኝ፣ በተገኘው ውጤትና ለውጤቱ መገኘት ምክንያት በሆነው ነገር መካከልም ጥብቅ የሆነ ተጠየቃዊ ግንኙነት አለ፡፡

**ምሳሌ፡-**

የኃይል እጥረት ለደኖች መመናመን ዋነኛ መንስኤ እየሆነ መጥቷል፡፡ የኤሌትሪክ ኃይል ባልተዳረሰባቸው አካባቢዎች ህዝቡ ደንን እየጨፈጨፈ ለማገዶነት ያውላል፡፡ የደኖች በጭፍጨፋ መመናመን ደግሞ የአየር ንብረት መዛባትን ያስከትላል፡፡ በዚህ የተነሣ በቂ የዝናብ መጠን ላይገኝ ወይም ከሚፈለገው በላይ የዝናብ መጠን ተገኝቶ በሰዎች፣ በእንስሳትና በሰብሎች ላይ ትልቅ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡ በዚህ አንቀጽ ውስጥ የተገለፀውን የመንስኤና ውጤት ትስስር እንደሚከተለው መለየት ይቻላል፡፡

| **ምክንያት** | **ውጤት** |
|---|---|
| - የኃይል እጥረት | - የደኖች መመናመን |
| - የደኖች መጨፍጨፍ | - የአየር ንብረት መዛባት |
| - በቂ ዝናብ አለመኖር ወይም ከሚጠበቀው በላይ መጣል | - የሰዎች፣ የእንስሳትና የሰብሎች ጉዳት |

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

**በዚህ ምዕራፍ በቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ላይ የተደረገውን ውይይት በድጋሚ አንብባችሁ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት፣ በመንስኤና ውጤት የተገለጹ ሀሳቦችን በሚከተለው ሰንጠረዥ አስፍሩ፡፡**

| ምክንያት | ውጤት |
|---|---|
| ምሳሌ፣<br>- ቋንቋ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ተናጋሪ ሲያጣ<br>- ____________<br>- ____________ | - እሱም አብሮ ይጠፋል<br>- ____________<br>- ____________ |

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ በቅድሚያ ቋንቋ ከሰዎች አንደበት የሚፈልቅ ድምጻዊ መግባቢያ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ በድምጽ ስለመግባባት ስናነሳ እንስሳት በድምጽ እንደ ሚግባቡ የተረዳን ቢሆንም፣ የሰው ልጅ ቋንቋ ከኢ-ደመነፍሳዊነቱና ከተለዋዋ ጭነቱ አንጻር ከእንስሳት መግባቢያ ፍጹም የተለየ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ቋንቋ የሰው ልጅ ብቻ መግባቢያ መሆኑንም አውቀናል፡፡


ስለቋንቋ አገልግሎት ባነሣንበት ክፍል ደግሞ፣ ቋንቋ ያሉትን ሁለት የተሳሰሩ አገልግሎቶች አይተናል፡፡ አንደኛው አገልግሎቱ በቀጥታ ሀሳብን ማስተላለፉ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የተናጋሪውን ማንነት ማሳወቁ ነው፡፡ ከዚህ ጋር አያያዘንም የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ሆኖ በመልክአ ምድር ተራርቆ መኖር ዘዬን እንደ ሚፈጥርና የዘዬ ልዩነትም በድምጽ፣ በቃላትና በአባባል ደረጃ እንደሚንፀባረቅ ተመልክተናል፡፡

ከላይ ከተገለጹት በተጨማሪ፣ የማስታወሻ አያያዝ መመሪያን ተከትለን እያዳ መጥን ማስታወሻ ይዘናል፡፡ በያዝነው ማስታወሻ በመመርኮዝም ያዳመጥነውን ፍሬ ሀሳብ በራሳችን አባባል ገልጸናል፡፡  በተመሳሳይ መንገድ በመንስኤና ውጤት የተገለፁ ሀሳቦችን ካዳመጥነውና ካነበብነው ጽሑፍ ውስጥ ለይተን ማውጣት ችለናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. አንድ ሰው "ድምጽ በማውጣት የሚከናወን መግባቢያ ሁሉ ቋንቋ ነው" ቢላችሁ መልሳችሁ  ምንድን ነው?
2. የእንሰሳት መግባቢያ ከሰው ልጅ ቋንቋ ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?
3. የቋንቋን ማህበራዊ አገልግሎት በምሳሌ አስደግፋችሁ አብራሩ፡፡

4. ከዚህ በታች በቀረበው ክብ ምስል ውስጥ በምክንያትና ውጤት የተሳሰሩ ስድስት ሀሳቦች ሰፍረዋል፡፡ ሀሳቦቹን በመመርመር በተሰጠው ሰንጠረዥ ውስጥ ምክንያቶቹን ከውጤቶቻቸው ጋር አገናኙ፡፡




| ምክንያት | ውጤት |
|---|---|
| ምሳሌ፣ በርትቶ የሚያጠና ተማሪ | ዕውቀትን ይገበያል፡፡ |
| ➢ | ➢ |
| ➢ | ➢ |

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አንድ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ/✓/፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ/?/፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ/x/ ምልክቶችን በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (✓) | (?) | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የምንባቡን ፍሬ ነገር አንብቤ ተረድቻለሁ። | | | |
| 2 | ስለቋንቋ ምንነትና አገልግሎት መግለጽ ችያለሁ። | | | |
| 3 | ያዳመጥኩትንና ያነበብኩትን የጽሑፍ ሀሳብ በራሴ አባባል መግለጽ ችያለሁ። | | | |
| 4 | ከጽሑፍና ከንግግር መንስኤና ውጤት ያላቸውን ሃሳቦች ለይቼ በማውጣት ገልጫለሁ። | | | |
| 5 | ለቃላት አገባባዊና ቀጥተኛ ፍች መስጠት ችያለሁ። | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክቶችን ያደረጋችሁ ባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ምዕራፍ ሁለት

## ስነ-ቃል

**የምዕራፉ ዓላማዎች:- ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- ስለ ስነ-ቃል ምንነት፣ ባህርይና ተግባር በመረጃ አስደግፋችሁ ታብራራላችሁ::
- የምዕላድን ምንነት ታስረዳላችሁ::
- ከቃል ውስጥ የእርባታ ቅጥያዎችን እየለያችሁ ታሳያላችሁ::
- የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተል ጠብቃችሁ ሀሳብን ትገልጻላችሁ::
- ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ተጠቅማችሁ ጭውውት ታካሂዳላችሁ::
- ከገለጻ፣ ከማብራሪያ፣ ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች የምታገኙትን ሐሳብ በማስታወሻ ትይዛላችሁ::
- የግጥምና የዝርው ጽሑፍ አነባበብ ስልትን ጠብቃችሁ ታነባላችሁ::

## ቅድመንባብ ጥያቄዎች

፩. ተረት አውርታችሁ ወይም ሲወራ አዳምጣችሁ ታውቃላችሁ?

፪. ተረትን ማዳመጥ የሚሰጠው ጥቅም ምንድን ነው?

፫. ያወራችሁት ወይም ያዳመጣችሁት ተረት ደራሲው ይታወቃል? መልሳችሁ "አይታወቅም" ከሆነ ለምን ያልታወቀ ይመስላችኋል?

፬. ቀጥሎ ለቀረቡላችሁ ሦስት ቃላት ነጠላ ፍቻቸውን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

1. ተደራሲያን 2. ከዋኝ 3. አውድ

፭. ከዚህ በታች "ስነ-ቃል" በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦላችኋል፡፡ ንባብ ከመጀመራችሁ በፊት ከርዕሱ ተነስታችሁ "ከምንባቡ እናገኛለን" የምትሏቸውን ፍሬ ሀሳቦች በመገመት ተናገሩ፡፡

## ስነ-ቃል

ስነ-ቃል የሚለው ስያሜ ሁለት እሳቤዎችን ይወክላል፡፡ አንደኛው የልዩ ልዩ ኪነቃላዊ ቅርጾች ጥቅል መጠሪያነቱ ሲሆን፣ ሁለተኛው ራሱን የቻለ የጥናትና የእውቀት ዘርፍ መሆኑ ነው፡፡ ስነ-ቃል ራሱን እንደቻለ የጥናት መስክ መጠሪያነቱ ሲታይ፣ በጽሑፍ ያልሰፈሩ ነገር ግን፣ በቃል የሚከወኑ የቋንቋ ጥበቦችን የሚያጠና የስነጽሑፍ ዘርፍ ነው፡፡ እንደ ኪነቃላዊ ቅርጾች ጥቅል መጠሪያነቱ ደግሞ፣ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ ተረቶችን፣ ሐተታ ተፈጥሮዎችን፣ አፈታሪኮችን፣ ምሳሌያዊ ንግግሮችን፣ እንቆቅልሾችን ቃላዊ ግጥሞችንና ዝማሬዎችን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

ስነ-ቃል ከተጻፈው ስነጽሑፍ የሚለይበት የራሱ ባህርያት አሉት፡፡ ከነዚህ መካከል ክዋኔ፣ አውዳዊነት፣ ተደራሲያንና ተለዋዋጭነት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህን እርስ በእርሳቸው የተያያዙ ባህሪያት ለመረዳት

አንድ የስነ-ቃል ቅርጽ አንስተን መመልከቱ ጠቃሚ ስለሚሆን ተረትን በምሳሌነት በመውሰድ እንመልከት፡፡

ተረት በአንድ በተወሰነ ጊዜና ቦታ የሚከወን ነው፡፡ ስለዚህ ከዋኙና ተደራሲያን በአንድ ላይና በአንድ ቦታ ይገናኛሉ፡፡ ከዋኙ ሲጀምር "ተረት ተረት" ይላል፡፡ "የላም በረት" ወይም "የመሠረት" በማለት ተደራሲያን ይመልሳሉ፤ ይሳተፋሉ፡፡ ከዋኙ ሲናገር እንደአስፈላጊነቱ ድምጽ ይቀያይራል፤ የአካል እንቅስቃሴ ያደርጋል፤ የሚተርተውን ለመምሰል ይጥራል፡፡

ተደራሲያኑም በፊናቸው "እሺ!"፣ "ከዚያስ?"፣ "እንዴህ አልሆነም?" ወዘተ. እያሉ ይከተሉታል፡፡ በዚህ ዓይነት ተደራሲያን የአጃቢነት፣ የመላሽነትና የአድማጭነት ተግባርን ይወጣሉ፡፡ ከከዋኙ ጋርም ይራከባሉ፡፡

በአንፃሩ ከዋኙ ተረቱን ከወላጆቹ ወይም ከሌሎች ሰዎች የሰማው ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን፣ ልክ እሱ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደሰማው፣ ሳይጨምርና ሳይቀንስ እንዳለ አይተርክም፡፡ ከዚህ ይልቅ በራሱ አባባልና አንዳንዴም በዘነጋቸው የተረቱ ክፍሎች ምትክ የራሱን እየፈጠረና እየሞላ ይናገራል፡፡ ይህ ሁኔታ የስነ-ቃልን (የተረቱን) የተለዋዋጭነት ባህሪ ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተረቱ የሚነገርበት አውድ ይኖረዋል፡፡ ይኸውም፣ ተረቱ ማታ ማታ ወላጆች ለልጆቻቸው ይተረቱት ይሆናል፤ ወይም በትምህርት ቤት አንድ ተማሪ ለክፍል ጓደኞቹ የሚተርተው ሊሆን ይችላል፡፡ ብቻ የትም ይሁን የት፣ ተረቱ የሚነገርበት አውድ ይኖረዋል፡፡ ይህ ሁኔታ የስነ-ቃል አውዳዊነትን ያሳያል፡፡

ስነ-ቃል ግለሰብ ወይም ደራሲ የማንጠቅስለት የህዝብ፣ የቡድን አእምሮና የልማድ ውጤት ነው፡፡ ስለሆነም ፈጥሮ ለሚገለግልበት ማህበረሰብ የተለያዩ ተግባራትን ይወጣል፡፡ ከተግባራቱም መካከል የማስተማር፣

የመግታት (የመቆጣጠር)፣ የመግለጽ፣ የማምለጥና የመትከል (የማጠናከር) ተግባራት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል ከስነ-ቃል ቅርጾች ምሳሌያዊ ንግግሮችን በምሳሌነት ወስደን ስነ-ቃል የማስተማርና የመግታት (መቆጣጠር) ተግባርን እንዴት እንደሚወጣ እንመልከት፡፡

### *የማስተማር ተግባር፡-*

አንድ ማህበረሰብ ስለ ልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮችና ስለ አኗኗር ስርዓት ልጆቹን በስነ-ቃል አማካይነት ያስተምራል፡፡ ለምሳሌ፣ “ሞኝን እባብ ሁለት ጊዜ ነደፈው፣ አንድ ጊዜ ሳያይ፣ አንድ ጊዜ ሲያሳይ" የሚለውን ምሳሌያዊ ንግግር ብንመለከት "ሰው ከስህተቱ መማር አለበት፤ ደጋግሞ ስህተት መሥራት የለበትም" የሚል ትምህርት ያስተላልፋል፡፡

### *የመግታት (የመቆጣጠር) ተግባር*

ማህበረሰቡ በጎ ምግባርን ለማበረታት ፣መጥፎ ምግባርን ለማውገዝና ሰዎችን ከመጥፎ ተግባር ለመግታት በስነ-ቃል ይጠቀማል፡፡ ለምሳሌ፣ "ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል፣ ዘላለም ሲያለቅስ ይኖራል" የሚለውን ምሳሌያዊ ንግግር ብንወስድ፣ ከመጥፎ ሰው ጋር መቀራረብ ለስቃይ እንደሚዳርግና መጥፎን መራቅ እንደሚያስፈልግ በማሳሰብ በክፉ ሰውና በደህና ሰው መካከል መቀራረብ እንዳይፈጠር ይገታል፡፡

*(ብርሃኑ ገበየሁ፣ የስነ-ቃል ምንነት፣ ዘውጎችና ስተናተን፣ 1995፣ 1-12 ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የቀረበ)*

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ:- ንባብ

**፩. ከዚህ በታች ለቀረቡ ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ።**

1. ከሚከተሉት አንዱ ከስነ-ቃል ሊመደብ አይችልም።
   ሀ) ምሳሌያዊ ንግግር፣
   ለ) እንቆቅልሽ፣
   ሐ) የሥራ ላይ ግጥሞች
   መ) ልቦለድ መጻሕፍት።

2. ስለስነ-ቃል ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ) ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ይሸጋገራል።
   ለ) በጽሑፍ ባለመስፈሩ በስነጽሑፍ ስር አይመደብም።
   ሐ) የልዩ ልዩ ኪነቃላዊ ቅርጾች ጥቅል መጠሪያ ነው።
   መ) ራሱን የቻለ የጥናት መስክ ነው።

3. በክዋኔ ጊዜ የተደራሲያን ተግባር ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ) ከዋኙን ማጀብ፣
   ለ) መልስ መስጠት፣
   ሐ) የስነ-ቃል ቅርጹን በመከወን መምራት፣
   መ) ማዳመጥ፣

4. ለስነ-ቃል ግለሰብ ደራሲ የማንጠቅስለት ለምንድን ነው?
   ሀ) የህዝብ እእምሮና የልማድ ውጤት በመሆኑ፣
   ለ) ምድቡ ከስነጽሑፍ ባለመሆኑ፣
   ሐ) በተለያዩ ጊዜያት የሚከወን በመሆኑ፣
   መ) ደራሲው በሁሉም ዘንድ የሚታወቅ በመሆኑ፣

4. ከሚከተሉት ስለስነ-ቃል ክዋኔ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ) ክዋኔ ከዋና ዋና የስነ-ቃል ባህሪያት አንዱ ነው፤
   ለ) የሚከወንበት ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታን ይፈልጋል፤
   ሐ) ክዋኔ የተደራሲያንን መኖር አይፈልግም፤
   መ) ክዋኔ ማህበራዊ ባህርይ አለው።

**፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ።**

1. "በጽሑፍ ያልሰፈሩ ነገር ግን፣ በቃል የሚከወኑ የቋንቋ ጥበቦች" ሲል ምን ማለቱ ነው? በምሳሌ አብራሩ።
2. ቀደም ባለው ዘመን "የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ" እየተባለ ይተረት ነበር። ዛሬ ዛሬ ደግሞ "የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ብሎኬት" ተብሎ ሲተረት ይደመጣል። ይህ ሁኔታ ከስነቃል ባህሪያት የትኛውን ያመለክታል?
3. ከስነ-ቃል ተግባራት አንዱ የሆነውን የማስተማር ተግባር በምሳሌ አስረዱ።
4. ስነ-ቃል ያልተጻፈና በቃል ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ እንደመሆኑ የጽሑፍ መስፋፋትና ስልጣኔ ሊያጠፋው ይችላል ን? መልሳችሁን በማስረጃ አስደግፋችሁ ተናገሩ።

## ክፍል ሁለት፡- ንግግር

**፩. በጥንድ ሆናችሁ የምታውቋቸውን ሦስት ሦስት እንቆቅልሾች በየተራ ተጠያየቁ። መላሹ መልሱን ከሰጠ በኋላ፣ የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ ማብራሪያ ይስጥ።**

*ምሳሌ፡-*

***ጠያቂ፣*** "እንቆቅልህ(ሽ)"

***መላሽ፣*** "ምን አውቅልህ(ሽ)"

***ጠያቂ፣*** "የሰራኝ ይሸጠኛል፤ የገዛኝ አይጠቀምብኝም፤ የሚጠቀምብኝ አያየኝም። እኔ ማን ነኝ?"

**መላሽ፣** "የሬሳ ሳጥን"

"መልሱ የሬሳ ሳጥን የሆነበትን ልግለጽ፤ በመጀመሪያ ሰው ይሞታል፡፡ ከዚያ ለእድር መሪዎች ወይም ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ወገኖች ሞቱ ይነገራል፡፡ የሚመለከታቸውም አስቀድሞ የተሠራ የሬሣ ሳጥን ወደሚያገኙበት የእሬሳ ሳጥን መሸጫ ቤት ይሄዳሉ፡፡ እዚያም የሳጥኑን መጠን አይተውና የሚበቃ መሆኑን አረጋግጠው ይገዙታል፡፡ ሲገዙት ግን ለራሳቸው ሊጠቀሙበት ሳይሆን ለሟቹ መቀበሪያ እንዲሆን ነው፡፡ ሟቹም በድን በመሆኑ ለሱ መጠቀሚያ የተገዛውን የሬሣ ሳጥን አያየውም፡፡ ነገር ግን፣ በውስጡ ገብቶ ይቀበርበታል፡፡

**፬. ከዚህ በታች አጥንታችሁ የምትተውኑት ጭውውት ቀርቧል፡፡ ከዚያ በፊት፣**

1. የጾታ ስብጥሩን የጠበቀ ባለአራት አባላት ቡድን መስርታችሁ በጭውውቱ ሀሳብና የቋንቋ አጠቃቀም ላይ ተወያዩ፡፡
2. በጭውውቱ ጥቅም ላይ የዋሉ ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ ንግግሮችን ለዩ፡፡
3. በጭውውቱ የተሳተፉትን አራት ገፀባህርያት ተከፋፍላችሁ በመያዝ ድርሻ ድርሻችሁን አጥንታችሁ ለተከታዩ ክፍለ ጊዜ ቅረቡ፡፡
4. መምህራችሁ በሚመሯችሁ መሠረት ጭውውቱን በመማሪያ ክፍል አቅርቡ፡፡
5. ባቀረባችሁት ጭውውት ላይ አስተያየት ተቀበሉ፡፡ ሌሎች ባቀረቡት ላይ አስተያየት ስጡ፡፡

## ጭውውት

(እናት ወ/ሮ ታሪኳ እርጅና የተጫጫናቸው ከመሆኑም በላይ፣ አብዛኞቹ ጥርሶቻቸው ወልቀው ከቀሩት ጥቂት ጥርሶች መካከል የመንጋጋ ጥርሳቸውን አሟቸዋል፡፡ ዛሬ የሆስፒታል ቀጠሮ አላቸው፡፡ ልጃቸው አስማማው ባለቤቱን ዓለምነሽን ወደ እናቱ ቤት ልኮ እሱ ሐኪም ቤት የሚወስዳቸውን መኪና ለማፈላለግ ወደኋላ ቀርቷል፡፡ ዓለምነሽ አማቷ ቤት በደረሰች ጊዜ ወ/ሮ ታሪኳ ፊት ለፊት ተቀምጠው ከጎረቤታቸው ከአቶ ደሴ ጋር እየተጫወቱ ነበር)

*ዓለምነሽ*:- " ሰላም ለዚህ ቤት! እንደምን አደራችሁ!"

*አቶ ደሴ*:- " እግዚያብሔር ይመስገን እንዴት ሰነበትሽ?"

*ዓለምነሽ*:- "እማማ! እንዴት ነዎት ዛሬ?" አለች ከአቶ ደሴ ጋር የእጅ ሰላምታ ከተለዋወጠች በኋላ ወደ አማቷ ጠጋ ብላ፡፡

*ወ/ሮ ታሪኳ*:- "በጎ ነኝ ልጄ! መቼም ከትናንትናው ዛሬ መለስ ብሎልኛል" ካሉ በኋላ ወዲያውኑ "አስማምዬን የት ጥለሽው መጣሽ?" ብለው ጠየቋት፡፡

*ዓለምነሽ*:- " ከቤት አብረን ወጣንና ‘አንቺ ቀድመሽ እማማን አዘጋጃት እኔ መኪና አፈላልጌ ልምጣ’ ብሎኝ ነው የተለያየነው፤ አሁን ይመጣል፡፡" ካለች በኋላ፣ ፊታቸውን የተሸፋፈኑበትን ነጠላ ገልጣ ለማየት እየሞከረች፣ "እረ ተመስገን ነው፤ ዛሬማ እብጠቱንም ቀንሷል ‘ኮ!" አለች፡፡

*ወ/ሮ ታሪኳ*:- "እኔማ መቼም ሲይዘኝ ‘ኑሮ ኑሮ ከመሬት፣ ዞሮ ዞሮ ከቤት’ ነውና መሞቴ ካልቀረ ለምን እድሜ ሰጥተህ ታሰቃየኛለህ? እያልኩ፣ ፈጣሪዬን አማረርኩት፡፡ የሱ ቸርነት አያልቅም፤ አሁን ደግሞ ተንፈስ አደረገኝ"

*አቶ ደሴ*:- "አይ እሜቴ! ለምን ሆደባሻ ይሆናሉ? በትንሽ በትልቁ ፈጣሪን ማማረር የለብዎትም ‘እግዜር በትር ሲቆርጥ ቆላ አይወርድም’ ሲባል አልሰሙም?"

*ወ/ሮ ታሪኳ*:- "አይ ደስዬ! በጊዜ በሰበሰበኝ ምንኛ ደግ ነበር? አየህ! የሰጠኝን በሽታ ሁሉ ሆዴን አስፍቼ ችየው ነበር፡፡ አሁን ግን የማልችለውን እየሰጠኝ ነው፡፡ ‘ልጅ ከጠረው ጥርስ የጠረው’ ይባላል እኮ!” እንዳሉ አስማማው ወደ ቤት ይገባል፡፡

*አቶ አስማማው*:- "እንዴት አደራችሁ? ምነው ዓለሜ፣ እማማን አላዘጋጀሻትም እንዴ!?" ካለ በኋላ፣ መለስ ብሎ "እማማ! ተሽሎሽ አደረ?" አላቸው፡፡

*ወ/ሮ ታሪኳ*:- "በጎ ነኝ ልጄ! ምንም አልል፡፡ ና እንግዲህ መኪናውን ካመጣህ ደገፍ አድርገኝና እንሂድ"

***አቶ አስማማው፡-*** "እሺ! አይዞሽ እማማ ትድኛለሽ" እያለ ደግሮ ያነሳቸዋል፡፡ "አይዝዎት! አይዝዎት! ይድናሉ" እያሉ አቶ ደሴና ዓለምነሽም እየደጋገፏቸው ይወጣሉ፡፡

## ክፍል ሦስት፡- ጽሕፈት

**፩. ስለስነ-ቃል ተግባራት ከመጻህፍት፣ ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች በማንበብ በመትከል (ማጠናከር)፣ በመግለጽና በማምለጥ ተግባራት ላይ ማስታወሻ ያዙ፡፡ የያዛችሁትን ማስታወሻ ተመርኩዛችሁ ከአንድ ገጽ ያላነሰ ማብራሪያ በጽሑፍ አቅርቡ፡፡**

**፪. ቀጥሎ "የስነ-ቃል ዘውጎች" በሚል ርዕስ የተዘጋጀውን ጽሑፍ መምህራችሁ አንድ ጊዜ ያነቡላችኋል፡፡**

1. እያዳመጣችሁ ዋና ዋና ፍሬ ሐሳቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ፡፡
2. ቡድን መስርታችሁ በተናጠል የያዛችሁትን ማስታወሻ አስተያዩ፡፡
3. የተስማማችሁባቸውን ፍሬ ሐሳቦች የያዘ ማስታወሻ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

**፫. ቀደም ሲል በክፍል ሁለት ተራ ቁጥር 2 የከወናችሁትን ጭውውት መሠረት በማድረግ፣ ከሚከተሉት የጭውውት ተሳታፊ ገጸ-ባህርያት መካከል አንዱን መርጣችሁ፡-**

1. ከ፫-፭ ደቂቃ የሚረዝም አንድ ጭውውት ጻፉ፡፡ (በጭውውቱ እንደጭብጡ ሁኔታ ምሣሌያዊና ፈሊጣዊ አባባሎችን መጠቀም ይጠበቅባችኋል፡፡)
2. የጻፋችሁትን ጭውውት አጥንታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

***አማራጭ ርዕሶች***

ሀ) አባት፣ እናትና ልጅ
ለ) ርዕሰ መምህር፣ ተማሪና መምህር
ሐ) ሻጭ፣ ገዢና ደላላ
መ) በሽተኛ፣ ሐኪምና አስታማሚ
ሠ) ዳኛ፣ አቃቤ ህግና ጠበቃ

**፬. በቡድን ሆናችሁ በመወያየት:-**

1. በአካባቢያችሁ የሚዘወተሩ ባህላዊ ምግቦች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝሩ፡፡
2. ከዘረዘራችኋቸው ባህላዊ ምግቦች ውስጥ አንድ አንድ በመከፋፈል ስለአሠራሩ የሚያብራራና የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ መግለጫ ጽፋችሁ ለቡድናችሁ አባላት በማቅረብ ተወያዩበት፡፡
3. ከቡድናችሁ ሥራዎች "የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉ ተጠብቆ በሚገባ ተገልጧል" ያላችሁትን አንድ የባህላዊ ምግብ አሠራር መግለጫ መርጣችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሙ፡፡

## ክፍል አራት:- ሰዋስው

**፩. ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት በነፃ ምዕላድና በጥገኛ ምዕላድ ከለያችሁ በኋላ፣ በምሳሌው መሠረት በሰንጠረዡ ውስጥ አስፍሩ፡፡**

| ተራ ቁ. | ቃል | ነፃ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ፣ 1 | ቂመኛ | ቂም | -ኛ |
| 2 | ሴትነት | | |
| 3 | ቤቶች | | |
| 4 | ብልጠት | | |
| 5 | ልባም | | |
| 6 | ልጆች | | |
| 7 | ጓደኛ | | |
| 8 | ልግመኛ | | |

## ምዕላድ ምንድን ነው?

ምዕላድ የምንለው ትርጉም-አዘል የሆነና አነስተኛ ወደ ሆኑ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊሸነሸን የማይችል የመጨረሻው ንዑስ አሀድ ነው። [ልብ] የሚለውን ቃል ወስደን ምዕላድን በምሳሌ እንመልከት። [ልብ] በመጀመሪያ ትርጉም ያለው (አንድ የሰውነት ክፍልን የሚያመለክት) አሀድ ነው። ሁለተኛም ይህ አሀድ ወደ አነስተኛ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊከፋፈል አይችልም። አንክፈለው ብንል እንኳ የምናገኘው ትርጉም የሌላቸውን ድምጾች ነው። ስለዚህም ሁለቱን መስፈርት በማሟላቱ [ልብ] ምዕላድ ነው።

በተመሳሳይ አኳኋን [ልባችን] የሚለውን አሀድ ደግሞ እንውሰድ። ይህ አሀድ በመጀመሪያ ትርጉም-አዘል ነው። ይሁን እንጂ፣ ምዕላድ ለመባል ከሱ በታች አነስተኛ ወደሆኑ ትርጉም-አዘል ክፍሎች ሊከፈል አለመቻሉ መረጋገጥ አለበት። ይህንን ስናደርግ ቃሉ [ልብ] እና [-አችን] በሚል ሊከፋፈል የሚችል በመሆኑ ቃል እንጂ ምዕላድ አይደለም።

በአንፃሩ [ልብ] እና [-አችን] የሚሉት አሀዶች ትርጉም ኖሯቸው ከነሱ ወዳነሱ ትርጉም አዘል ክፍሎች ልንከፋፍላቸው ስለማንችል ምዕላድ ይሁኑ እንጂ፣ ልዩነት አላቸው። [ልብ] ራሱን ችሎ የሚቆም ምዕላድ ሲሆን፣ [-አችን] ግን እንደ [ልብ] ባሉ አሀዶች ላይ ካልተቀጠለ በስተቀር ትርጉም መያዝና እራሱን ችሎ መቆም አይችልም። ስለዚህም እንደ[ልብ] የመሳሰሉ ምዕላዶች ራሳቸውን ችለው ስለሚቆሙ **ነፃ ምዕላድ** ሲባሉ፣ (-ኣችን)ን… እራሳቸውን ችለው ሰለማይቆሙ **ጥገኛ ምዕላድ** ይባላሉ።

*(ባዮ ይማም፣የአማርኛ ሰዋስው ፣2000፣72-73)*

**፩. ከዚህ በላይ ስለምዕላድ የቀረበውን ገለጻ መሠረት በማድረግ በቃልና በምዕላድ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ግለጹ።**

**፪. በሰንጠረዡ በተዘረዘሩ ቃላት ውስጥ ያሉ የመደብ፣ የጾታና የቁጥር አመልካች ቅጥያዎችን በመለየት በተሰጠው ምሣሌ መሠረት ተግባራቸውን ግለጹ።**

ምሣሌ፡-

| ተራ ቁጥር | ቃል | ቃሉ በምዕላድ ሲተነተን | ቅጥያ ምዕላድ | የቅጥያ ምዕላዱ ተግባር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ትምህርት ቤታችን | ትምህርት ቤት-አችን | -አችን | መደብን |
| 2 | እርሳሶች | እርሳስ-ኦች | -ኦች | ቁጥርን ማመልከት |
| 3 | ልጂት | ልጅ-ኢት | -ኢት | ጾታን ማመልከት |

| ተራ ቁጥር | ቃል | ቃሉ በምዕላድ ሲተነተን | ቅጥያ ምዕላድ | የቅጥያ ምዕላዱ ተግባር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስነ-ቃሎች | | | |
| 2 | ምሳሌዎች | | | |
| 3 | ክብርት | | | |
| 4 | ስበሳችሁ | | | |
| 5 | ተግባራት | | | |
| 6 | መምህርት | | | |
| 7 | ግልገሏ | | | |
| 8 | ገበርን | | | |

፬. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተት በምሳሌው መሠረት የቁጥር፣ የጾታ፣ የመደብ በማለት ከለያችሁ በኋላ፣ ዓረፍተነገሮቹን አስተካክላችሁ እንደገና ጻፉ።

*ምሳሌ፡-*

ልጆች ታላላቆቻችንን ማክበራቸው ያስመሰግነናል።

ስህተቱ፡- የመደብ አለመስማማት

ዓረፍተነገሩ ሲስተካከል:-

ልጆች ታላላቆቻቸውን ማክበራቸው ያስመሰግናቸዋል።

ወይም

ልጆች ታላላቆቻችንን ማክበራችን ያስመሰግነናል።

1. መምህራኖች ስብሰባ ስላላቸው ለዛሬ ትምህርት እንደማይኖር ርዕሰ-መምህራችን ነገሩን።
2. አንዳንድ ጊዜ ለውበት የሚኳሉት ኩሎች ዐይንን ሊጎዱ ይችላሉ።
3. ህዝብ ለልማት ተባብረው ሲሠሩ ተጠቃሚነታቸው ያድጋል።
4. ሰው ለሰው አጥፊም አልሚም ናቸው።
5. ታዬ ጊደሩን ሽጦ ወይፈን ገዛ።

## ክፍል አምስት:- ስነ ጽሑፍ

**ቀጥሎ ንባብ የምትለማመዱባቸው በዝርውና በግጥም ከተደረሱ ስነጽሑፋዊ ሥራዎች የተወሰዱ ሁለት ጽሑፎች ቀርበውላችኋል።**

1. ቡድን መስርታችሁ አንዱ የቡድን አባል ጽሑፎቹን ሲያነብ፣ ሌሎቻችሁ በማዳመጥ በአነባበብ ስልቱ ላይ አስተያየት ስጡ።
2. ከመካከላችሁ የተሻለ ያነበበውን የቡድን አባል ምረጡ።
3. የተመረጠው ተማሪ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ቡድኑን ወክሎ ድምጹን ከፍ አድርጎ ያንብብ።

**ጽሑፍ አንድ:-**

## በሠርጉ ማግስት

“ጋሼ ፍሬ ነገሩ ይህ አይደለም፡፡ አስቀድሜ ሰርግና ድግስ የሚባል ነገር አልፈልግም ብየ ነግሬህ ነበር፡፡ ‘እኔ በህይወቴ እያለሁ ሉሊት የምትባል አታገባም’ ስትለኝ ከርመህ፣ ቆርጬ መነሳቴን ስታውቅ ‘ካልደገስኩ ሞቼ እገኛለሁ፤ ሆድና ጀርባ ሆነን እንቀራለን’ ብለህ ገንዘብ እንዳለው ሰው ደገስክ፡፡ ከቶ አይገባኝም፤ ጨርሶ አይገባኝም …”

“ምኑ ይገባሀል የናቴ ልጅ! አይገባህም፡፡ ባህላችንንና አስተሳሰባችንን አታውቀውማ! አንድ ታናሽ ወንድሜ፣ አበራ ሲያገባ እንዴት እንደባእድ ከዳር ቁጭ ብየ ልመልከት? ጎረቤት ምን ይለኛል? የፊታውራሪ ወርቁ ልጅ፣ የአባተ ወንድም፣ የእመት ባፈና ባንትይርጉ ልጅ ያለሠርግ፣ ያለድግስ እንዲሁ አገባ ቢባል ጎረቤት፣ እድርተኛውና የሚያውቀን ሰው ሁሉ ምን አይነት ትዝብት ላይ ይጥለናል? ምን አይነትስ ግምት ይወስድብናል? አባታችን በንፋግነት ተጠርተው ስማቸው በየመንደሩ የቡና ቁርስ ከሚሆን ሞቼ መቀበሬን እመርጣለሁ፡፡ አባታችን በህይወት ሳሉ በሰርግ ቀን ይቅርና በሌላውም ቀን ከሰው ተለይተው መብላትን አይወዱም ነበር፡፡ እስከ እለተ ሞታቸው በክብር ጠብቀው ያቆዩን ስም እንዴት በልጆቻቸው ምክንያት ይበላሽ? …”
አበራ፣ “ከእዳ ሌላ ምን ተረፈኝ?” ከማለት ሌላ በተጨማሪ የሚናገረው ነገር አልነበረውም፡፡

*(በሉሉ ግርማ፣ ከሎድማስ ባሻገር፣ 1962፣ 96-97 ለማስተማሪያ እንዲሆን ተሸሽሎ የቀረበ)*

**ጽሑፍ ሁለት፡-**

## የክፋት ተጋብኦት

ከሰል የሚሸጥ ሰው ልብስ አጣቢን አለው፣
ለቤት ኪራይ ብለህ ገንዘብ የምትከፍለው፣
ቀሪ እንዲሆንልህ አብረህ ከኔ ጋራ፣
ኪራይ ሳትከፍል ተቀምጠህ ብትሠራ፣
ቤቱም ይበቃናል አንድነት እንኑር፣
ልብስ አጣቢ ሰምቶ ይህንኑ ምክር፣
አመሰግናለሁ በማሰብህ ለኔ፣
ግን የማይጠቅመኝ ነው ካንተ ጋር መሆኔ፤
ታጥቦ ታጥቦ ጭቃ የሚባለው ተረት፣
እንደሚደርስብኝ አስበህ ተመልከት፣
እኔ የማጥበው ልብስ ካንተ ከሰል ጋራ፣
ይቆሽሽ የለም ወይ አብረን ስንሠራ፤
ከሰል ለነጭ ልብስ ነውና ጠላት፣
የማይሆን ሀሳብ ነው ሲል መለሰለት፡፡

ከሰል ለነጭ ልብስ እንዲሆነው አጥፊ፣
ከክፉም የዋለ ክፋትን አትራፊ፣
ከመሆን አይድንም ምን ቢጠነቀቅ፣
ዐመል ሳይበላሽ ጠርቶ እንዲጠበቅ፣
ከመጥፎ ጓደኛ ይገባል መራቅ፡፡

*(ከበደ ሚካኤል፣ የቅኔ ውበት፣ 1999፣ 28-29)*

## የዝርውና የግጥም አነባበብ ስልት

ግጥምና ዝርው ሀሣብን በጽሑፍ የማቅረቢያ ቅርጾች ናቸው። በግጥም ቅርጽ የቀረበን ጽሑፍና በዝርው ቅርጽ የቀረበን ጽሑፍ ስናነብ የምንከተለው ስልት የተለያየ ነው።

### ፩. የግጥም አነባበብ

1. በቅድሚያ ርዕሱን ተመልክተን የግጥሙ ትኩረት ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት፣
2. ድምፃችንን ከፍ አድርገን ከማንበባችን በፊት የግጥሙ ስንኞች ያላቸውን ምጣኔ ለመረዳት ከፊት ያሉትን ጥቂት ስንኞች ባለሆሳስ አንብቦ መሞከር፣
3. በየስንኙ የገቡትን ስርዓተ ነጥቦች አውቆ በዚያው መሠረት ማንበብ፣
4. በየስንኙ ተዘርዝረው የሚነበቡትን ሆሄያትና ተዘርዝረው የማይነበቡትን እየለየን በማንበብ የግጥሙ ዜማና ምት መጠበቁን ማረጋገጥ ይኖርብናል።

### ፪. የዝርው አነባበብ

1. ማንበብ ከመጀመራችን በፊት ርዕሱን በማየት ጽሑፉ ስለምን ሊነግረን እንደሚችል ማሰላሰል፣
2. በእያንዳንዱ ዓረፍተነገር ውስጥ የሚዘረዘር ነገር ሲኖር፣ ዓረፍተነገሩ ሲቋጭ፣ ከአንዱ ዓረፍተነገር ወደሌላው ዓረፍተነገር፣ ከአንዱ አንቀጽ ወደሌላው አንቀጽ የሀሣብ ሽግግር ሲደረግ አፍታ (ጊዜ) እየወሰዱ ማንበብ፣
3. የሀሣብ ፍሰቱን እየተከተልን ከተገቢው የድምጽ ቅላፄ ጋር ማዋሀድ፣
4. ስርዓተ ነጥቦች የሚይዙትን መልዕክት በሚገባ መረዳት ይጠበቅብናል።

## ማጠቃለያ

በምዕራፍ ሁለት ስለስነ-ቃል ምንነት፣ ባህርይና ተግባር ተመልክተናል፡፡ በዚህ መሠረት፣ ስነ-ቃል ባንድ በኩል የብዙ ኪነቃላዊ ቅርጾች ጥቅል መጠሪያ ሲሆን፣ በሌላ በኩል እራሱን የቻለ የእውቀት ዘርፍ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ ስለስነ-ቃል ዐበይት ባህሪያት ባየንበት ክፍልም ስለክዋኔ፣ ስለአውዳዊነት፣ ስለተደራሲያንና ስለተለዋዋጭነት እንዲሁም አንዳቸው ካንዳቸው ጋር በጥብቅ የተሳሰሩ መሆናቸውን በምሳሌ እያስደገፍን አይተናል፡፡ ስለስነ-ቃል ዋና ዋና ተግባራት አንስተንም የማስተማር፣ የመግታት (መቆጣጠር)፣ የመግለጽ፣ የማምለጥና የመትከል-ማጠናከር ተግባራትን ምንነት ዘርዝረናል፡፡

በሌላ በኩል የምዕላድ ምንነትን፣ ቃላት ለመደብ፣ ለጾታና ለቁጥር እንዴት እንደሚረቡ ቃላትን በመተንተን የቅጥያዎቹን ተግባር አሳይተናል፡፡ የሐሳብ የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን የጠበቀ ጭውውት በቡድን ጽፈን በመማሪያ ክፍል ከውነናል፡፡ ባዘጋጀነው ጭውውት ውስጥ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በተገቢው ቦታ ተጠቅመናል፡፡

በመጨረሻም ግጥምና ዝርው የራሳቸው የአነባበብ ስልትን እንደሚከተሉ ተገንዝበን፣ በዝርውና በግጥም የቀረቡ ጽሑፎችን በተገቢው ደረጃ ማንበብ ችለናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የስነ-ቃል የመትከልን (የማጠናከርን) ተግባር የሚያሳዩ ሦስት ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ጠቅሳችሁ እንዴት ተግባሩን እንደተወጡ መግለጫ ስጡ፡፡
2. ስለፍቅር የተገጠሙ ሦስት ቃላዊ ግጥሞችን ጠቅሳችሁ መልዕክታቸውን አብራሩ፡፡
3. ስነ-ቃል ከተጻፈው ስነጽሑፍ ከሚለይባቸው ዋና ዋና ባህርያት መካከል ሁለቱን በመጥቀስ በጽሑፍ አብራሩ፡፡
4. በነፃ ምዕላድና በእስር (ጥገኛ) ምዕላድ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በምሳሌ በማስደገፍ አስረዱ፡፡

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሁለት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል:: በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ /✓/፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ /?/፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ /x/ ምልክቶችን በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ::

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (✓) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለ ስነ-ቃል ምንነት ተረድቼ በትክክል ማብራራት ችያለሁ:: | | | |
| 2 | የምዕሳድን ምንነት ማስረዳት እችላለሁ:: | | | |
| 3 | ከቃላት የመደብ፣የጾታ፣የቁጥር አመልካች ቅጥያዎችን ለይቼ አመለክታለሁ:: | | | |
| 4 | ከተለያዩ ጽሑፎች የማገኘውን ሐሳብ የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቄ መግለጽ ችያለሁ:: | | | |
| 5 | የቀረበልኝን ጭውውት በስርዓት አከናውናለሁ:: | | | |
| 6 | የግጥምና የዝርው አነባበብ ስልትን አውቄ በተገቢው መንገድ አነባለሁ:: | | | |
| 7 | ካዳመጥኩት ገለጻና ማብራሪያ ላይ ማስታወሻ መውሰድ ችያለሁ:: | | | |
| 8 | በማዘጋጀው ጭውውት ውስጥ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን መጠቀም ችያለሁ:: | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ /?/፣ እና የ/X/ ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ ፣የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ::

# ምዕራፍ ሦስት

## ቤተ-መጻሕፍትና ስነ-ጽሑፍ

**የምዕራፉ ዓላማዎች:- ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ:-**

- ለቃላት ቀጥተኛና አገባባዊ ፍች ትሰጣላችሁ::
- ስርዓተ ነጥቦችን ተጠቅማችሁ ትጽፋላችሁ::
- ተራኪ ድርሰት ትጽፋላችሁ::
- የውይይት ስርዓትን ጠብቃችሁ ትወያያላችሁ::
- የቤተ መጻሕፍትና የውይይት መመሪያዎችን ተገንዝባችሁ ትገለገላላችሁ::
- አንቀጽ ትጽፋላችሁ::
- የስነ-ጽሑፍ ምንነትን ትገልጻላችሁ::

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

**፩. ስነ-ጽሑፍ ምንድን ነው?**

**፪. ደራሲያን ለምን ይጽፋሉ?**

**፫. በተጻፈውና ባልተጻፈው ስነ-ጽሑፍ መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?**

**፬. እስከ ዛሬ ካነበባችኋቸው የስነ-ጽሑፍ ውጤቶች (ልቦለዶች፣ ግጥሞችና ድራማዎች) የምታስታውሱትን ተናገሩ፡፡**

## ስነ-ጽሑፍ

ስነ-ጽሑፍ የሚለው ቃል በቁሙ ሲታይ በጽሑፍ የተቀረጸን የቋንቋ ጥበብ የሚመለከት ነው፡፡ ሆኖም ስነ-ጽሑፍ ከዚህ የቁም ፍችው ባለፈ የሰው ልጅ የጽሕፈት ባህል ከመጀመሩ አስቀድሞ ስሜቱን የገለጸባቸውንና ወደፊትም የሚገልጽባቸውን ቃላዊ ፈጠራዎችንም ያጠቃልላል፡፡ በምዕራፍ ሁለት ትምህርታችን ቃላዊ የሆነውንና ያልተጻፈውን ስነ ጽሑፍ ስነቃል በሚል ርዕስ ተመልክተናል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የተጻፈውን ስነ-ጽሑፍ ምንነት እንመለከታለን፡፡

ስለ ስነ-ጽሑፍ ምንነት ሲነሳ ቀድሞ የሚመጣው ጥያቄ ማንኛውም የተጻፈ ነገር ሁሉ ስነ-ጽሑፍ ሊባል ይችላል? ወይስ አይችልም? የሚለው ነው፡፡ ምላሹም ሁለት የአመለካከት አቅጣጫን የተከተለ ነው፡፡ አንደኛው አቅጣጫ፣ "ስነ-ጽሑፍ ለመባል ዋነኛ መለኪያው በጽሑፍ ተቀርፆ መገኘቱ ነው፡፡ ስለዚህም ደብዳቤ፣ የእለት ማስታወሻ፣ ታሪክ፣ ጂኦግራፊ፣ ወዘተ. ሁሉ በስነ-ጽሑፍ የሚካተቱ ናቸው" የሚለው ሲሆን፣ ሁለተኛው "በጽሑፍ በሚገባ ተቀነባብሮ በቃላት የተገለጸ ሁሉ ከስ-ነጽሑፍ ይቆጠራል ማለት አይደለም፡፡ አንድ ጽሑፍ 'ስነጽሑፋዊ ነው' ለመባል መጻፉ ብቻ ሳይሆን፣ ኪነጥበባዊ ብቃት ያለው መሆን

ይኖርበታል” የሚለው አቅጣጫ ነው፡፡ በዚህ የአመለካከት አቅጣጫ መሰረት፣ ስነ-ጽሑፍ የሚለው ቃል በትክክል የሚያመለክተው የተመሰ ከረለት የጥራት ደረጃ ያላቸውንና በዝርው ወይም በግጥም የተጻፉ ሥራዎችን ብቻ ነው፡፡

የዚህ ምዕራፍ ትኩረት በሁለተኛው የአመለካከት አቅጣጫ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በመሆኑም፣ ስነ-ጽሑፍ በአገላለጽ ትባቱ፣ በህይወት (ኑሮ) ማሳያነቱ፣ በሳቢነቱና የአንድ ደራሲ ወጥ ሥራ በመሆኑ የተዋጣለትና ኪነጥበባዊ ብቃቱ የተመሰከረለት የፈጠራ ሥራ ነው፡፡ ሰዎች ስለህይወት ያላቸውን ግንዛቤ (የሚሰማቸውን፣ የሚያስቡትንና የሚመኙትን) በቋንቋ አማካይነት የሚያንፀባርቁበት ኪነጥበብ ነው፡፡ ህይወትን፣ እውነትንና ፈጠራን ባንድ ላይ አጣምሮ በተወሰነ ቅርጽና መጠን የሚያቀርብ በመሆኑ ውበት አለው፤ ስሜትን ይነካል፤ ይማርካል፤ ያስደስታል፡፡

ስነ-ጽሑፍ ከሰው ልጅ ህይወት ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለው፡፡ የስነ-ጽሑፍ ዋነኛው ጉዳይ የሰው ልጅ ነው፡፡ ምንጩ ፈጣሪውም ተቀባዩም ሰው ነው፡፡ በመሆኑም  ስነ-ጽሑፍ የሰው ልጅ በህይወቱ ከሚያልፍበት ውጣ ውረድ ይቀዳል፤ በሰው ተፈጥሮም መልሶ ለሰው ይነገራል፡፡  ስነ-ጽሑፍ የሰውን ጉዳይ ይዞ መልሶ ለሰው የሚቀርብ መሆኑ ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ  ልዩ ቦታን እንዲይዝ አድርጎታል፡፡

**ተማሪዎች! እዚህ ላይ ንባባችሁን ቆም አድርጋችሁ ለሚከተለው ጥያቄ መልስ ስጡ፡፡ መልሳችሁን በማስታወሻችሁ በማስፈር ወደንባባችሁ ተመለሱ፡፡ ንባባችሁን እንደ ጨረሳችሁ የሰጣችሁትን መልስ ከምንባቡ ካገኛችሁት ፍሬ ነገር ጋር አመሳክሩ፡፡**
**ጥያቄ፣ ደራሲያን ለምን ይጽፋሉ? ወይም እንዲጽፉ የሚያነሳሳቸው ምክንያት ምንድን ነው?**

ለስነ-ጽሑፍ መኖር ምክንያት ናቸው የሚባሉ ሦስት ዋና ዋና ነጥቦች ይጠቀሳሉ፡፡ የመጀመሪያው፣ የሰው ልጅ ስለገጠመኙ ለመናገር ያለው ፍላጎት ነው፡፡ ሰው ስለህይወት የተገነዘበውን በጎም ሆነ ክፉ ነገር ለመሰሎቹ ማካፈል ይፈልጋል፡፡ ይህ ፍላጎት በሁሉም ሰዎች ዘንድ ያለና ተፈጥሮአዊ ባህሪ ቢሆንም በደራሲያን ዘንድ ያለው ግን ላቅ ያለ ነው፡፡ ደራሲያን ከሌላው ሰው በተለየና ከፍ ባለ ደረጃ ስለህይወት የመናገር ፍቅር አላቸው፡፡ ስለዚህም ህይወትን እነሱ እንደተመለከቷት ለሌላው ለማስተላለፍ ይተጋሉ፡፡

ሁለተኛው ምክንያት፣ ደራሲያን ለሰው ልጅ ጥልቅ ፍቅርና ሰውን ለማወቅ ጽኑ ፍላጎት ያላቸው መሆኑ ነው፡፡ ሰዎች ምን ዓይነት ፍጡሮች ናቸው? ከየት መጡ? ወዴትስ ይሔዳሉ? ባህሪዎቻቸው እንዴት ያሉ ናቸው? የአኗኗር ስርዓታቸው ምን ይመስላል?.... ለነዚህና መሰል አጓጊ ጥያቄዎች እውናዊና መሳጭ መልስ ለመስጠት ይጽፋሉ፡፡

ሦስተኛው ምክንያት፣ የሰው ልጅ ለውበት ያለው ፍቅር ነው፡፡ ሰው ማራኪና ሳቢነት ያለውን ነገር በአንድ ቅርጽ ተሰናድቶ ማየት ይፈልጋል፡፡ በእውኑ ዓለም ያየውንና የሰማውን ወይም በአእምሮው የዳሰሰውን ነገር አቀነባብሮ በአንድ ቅርጽ ሲያበጀው ደግሞ ውበትን ይጎናፀፋል፡፡ ያንን ውበት ያደንቃል፤ ያፈቅራል፡፡ እንዲህ ያለው የውበት ፍቅር ደግሞ ደራሲውን እንዲፈጥር ዘወትር ይቀሰቅሰዋል፡፡ እናም ሁል ጊዜ ይጽፋል፡፡

*(ዘሪሁን አስፋው፣ የስነ-ጽሑፍ መሠረታዊያን፣ 1992፣1-3 ለማስተማሪያ እንዲሆን ተሻሽሉ የቀረበ)*

## መልመጃዎች

## ክፍል አንድ:- ንባብ

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ግለፁ፡፡**

1. ስነ-ጽሑፍ የሚለው ቃል በቁሙ ሲታይ የሰው ልጅ ጽሕፈትን ከመፍጠሩ አስቀድሞ የተገለገለባቸውን ቃላዊ ፈጠራዎች ያመለክታል፡፡
2. አንድ ጽሑፍ ስነጽሑፋዊ ነው ለመባል በጽሑፍ መቅረቡ ብቻ በቂ አይደለም፡፡
3. በጽሑፍ በሚገባ ተቀነባብሮ በቃላት የተገለጸ ሁሉ ከስነ-ጽሑፍ ይቆጠራል፡፡
4. ስነ-ጽሑፍ በማህበረሰቡ ልዩ ቦታ እንዲይዝ ያደረገው መተላለፊያው በጽሑፍ መሆኑ ነው፡፡
5. የሰው ልጅ ሁል ጊዜም ገጠመኙን ለማውጋት ያለው ፍላጎት ለስነ-ጽሑፍ መኖር እንደ አንድ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ከቀረቡት አማራጮች መካከል ተስማሚውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ከሚከተሉት አንዱ የአንድ ጽሑፍ ኪነጥበባዊ ብቃት መመዘኛ አይደለም፡፡
   ሀ) በአገላለጹ የተባ መሆን፣
   ለ) በጽሑፍ አማካይነት መገለጽ፣
   ሐ) ሕይወትን ማሳየት፣
   መ) ማራኪና ሳቢ መሆን፣
2. ከሚከተሉት አንዱ "የተጻፈ ነገር ሁሉ ስነ-ጽሑፍ ነው" የሚሉ ወገኖችን ሀሳብ አያንጸባርቅም፡፡
   ሀ) የዕለት ውሎ ማስታወሻና የሥራ ደብዳቤዎች ከስነ-ጽሑፍ ይቆጠራሉ፡፡

ለ) በጽሑፍ ያልሰፈረ ነገር ስነ-ጽሑፍ ሊባል አይችልም።

ሐ) አንድ ጽሑፍ ስነጽሑፋዊ መሆኑ የሚረጋገጠው በጽሑፍ በመስፈሩ ነው።

መ) የአንድ ጽሑፍ ስነጽሑፋዊነት መለኪያው ኪነጥበባዊ ብቃቱ ነው።

3. ከሚከተሉት አንዱ ለስነ-ጽሑፍ መኖር ምክንያት አይደለም።

ሀ) ደራሲያን ለሰው ልጅ ያላቸው ጥልቅ ፍቅርና እሱን ለማወቅ የሚደረጉት ጥረት፣

ለ) የሰው ልጅ ገጠመኙን ለማካፈል ያለው ፍላጎት፣

ሐ) ድርሰትን ሸጦ ገንዘብ የማግኘት ፍላጎት መኖር፣

መ) የሰው ልጅ ለውበት ጥልቅ ፍቅር ያለው መሆን፣

4. "በጽሑፍ የተገለጸ ሁሉ ስነ-ጽሑፍ ነው" የሚሉ ወገኖች ለአባባላቸው ዋና መመዘኛ የሚያደርጉት ምንድን ነው?

ሀ) በጽሑፍ መስፈርና አለመስፈር፣

ለ) በፈጠራ መንገድ መጻፍና አለመጻፍ፣

ሐ) ህይወትን እውነትና ፈጠራን ባንድ ላይ መያዝ አለመያዝን፣

መ) ያልተጻፈ ስነ-ጽሑፍ መኖርን፣

5. "የስነ-ጽሑፍ ዋና ጉዳይ ሰው ነው" ሲባል፣ ምንን ለማመልከት ነው?

ሀ) ከሰው ልጅ ገጠመኝ የሚቀዳ መሆኑን፣

ለ) ፈጣሪው ሰው መሆኑን፣

ሐ) የሚጻፈው ለሰው መሆኑን፣

መ) ሁሉም መልስ ናቸው

**፫. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ እየተሰመረባቸው ለቀረቡ ቃላት አገባባዊ ፍች ከሰጣችሁ በኋላ፣ በሰጣችሁት ፍች መሠረት የራሳችሁን ዓረፍተነገር መስርቱ፡፡**

***ምሣሌ፡-***

በዚህ <u>ምዕራፍ</u> ደግሞ የተጻፈውን ስነ-ጽሑፍ ምንነትና የመኖር ምክንያት እንመከለታለን፡፡

አገባባዊ ፍች፣ <u>ክፍል</u>

ዓረፍተነገር፣ በዚህ <u>ክፍል</u> ደግሞ የተጻፈውን ስነ-ጽሑፍ ምንነትና የመኖር ምክንያት እንመለከታለን፡፡

1. ስነ-ጽሑፍ በጽሑፍ <u>የተቀረፀውን</u> የቋንቋ ጥበብ ይመለከታል፡፡
2. ሰዎች ስለህይወት ያላቸውን ግንዛቤ በቋንቋ አማካይነት <u>ያንፀባርቃሉ</u>፡፡
3. ስነ-ጽሑፍ በጽሑፍ መስፈር ብቻ ሳይሆን ኪነ ጥበባዊ <u>ብቃት</u> ሊኖረው ይገባል፡፡
4. ስነ-ጽሑፍ የህይወት <u>ገጠመኝ</u> ይንፀባረቅበታል፡፡
5. ሰው ስለህይወት <u>የተገነዘበውን</u> በጎም ሆነ ክፉ ነገር ለመሰሎቹ ማካፈል ይፈልጋል፡፡
6. ሕይወትን እነሱ እንደተመለከቷት ለሌላው ለማስተላለፍ <u>ይተጋሉ</u>፡፡
7. የስነ ጽሑፍ <u>ምንጩም</u>፣ ፈጣሪውም፣ ተቀባዩም ሰው ነው፡፡

**፬. ለሚከተሉት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ቀጥተኛ ፍቻቸውን ከሰጣችሁ በኋላ፣ ዓረፍተነገር ሥሩባቸው፡፡**

***ምሣሌ፡-***

በቁሙ = በህይወት እያለ

ዓረፍተነገር= አባቴ በቁሙ የተናዘዘልንን ሀብት ከእህቶቼ ጋር ተከፋፈልን፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. ፈጠራ | 5. ህይወት | 9. ቁርኝት |
| 2. ኪነጥበብ | 6. ዝርው | 10. ትኩረት |
| 3. አጓጊ | 7. ግንዛቤ | 11. መጋተር |
| 4. ቅርጽ | 8. መማረክ | 12. መትጋት |

**፫. ከዚህ በታች ከቀረቡላችሁ ርዕሰ ጉዳዮች አንዱን ምረጡና በአካባቢያችሁ ወደሚገኝ የህዝብ ቤተመጻህፍት ወይም ወደትምህርት ቤታችሁ ቤተመጻህፍት በመሔድ ከመጻህፍት ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች መረጃ ሰበስቡ፡፡**

***መረጃ የሚሰበሰብባቸው ርዕሰ ጉዳዮች፣***

ሀ) ከአስር ያላነሱ የልቦለድ መጻሕፍትን በማገላበጥ፡- የደራሲውን ስም፣ የመጽሐፉን ስም፣ የህትመት ስፍራ፣ አሳታሚ ድርጅቱንና የመጽሐፉን የገጽ ብዛት ዝርዝር አቅርቡ፡፡

ለ) ልዩ ልዩ መጽሔቶችን በማገላበጥ ከአስር ያላነሱ ጽሑፎችን መር ጣችሁ፡- የጽሑፉን ባለቤት ስም፣ የህትመት ዓመተ ምህረትና ወር፣ የጽሑፉን ርዕስ፣ የመጽሔቱን ስም፣ በመጽሔቱ የሰፈ ረበትን ገጽ (ከገጽ_ እስከ _በማለት) በመዘርዘር አቅርቡ፡፡

ሐ) የተለያዩ ጋዜጦችን በማገላበጥ የሚያጋጥሟችሁን ከአስር በላይ ተረትና ምሳሌዎች ከመዘገባችሁ በኋላ፡- ተረትና ምሳሌዎቹን ያገኛችሁባቸውን ጋዜጦች ስም፣ የታተሙበትን ዓመተ ምህረት፣ ወርና ቀን በመዘርዘር አቅርቡ፡፡

## የቤተ-መጻሕፍት አጠቃቀም መመሪያ

ቤተ-መጻሕፍት በዓይነቱ የህዝብ፣ የትምህርት ቤት፣ የኮሌጆችና የዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር፣ የመንግስትና ልዩ ቤተ-መጻሕፍት በሚል ሊከፋፈል ይችላል፡፡ በየትኛውም ዓይነት ቤተመጻሕፍት ውስጥ መጻሕፍት፣ የጥናትና ምርምር መጽሔቶች ጋዜጦች፣ ልዩ ልዩ መረጃዎችን የያዙ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ይገኛሉ፡፡ ቤተ-መጻሕፍት ውስጥ የምንፈለገውን መረጃ ለማግኘት በቅድሚያ የቤተ መጻሕፍት ስነ ስርዓትንና የመጻሕፍት አፈላለግን ማወቅ ይጠበቅብናል፡፡

**፩. የቤተ-መጻሕፍት ዋና ዋና ደንቦችንና ስነስርዓቶችን መጠበቅ**

1. ፀጥታን መጠበቅ
   - ሀ. ፀጥታን የሚያደፈርሱ ለምሳሌ ነጠላ ጫማን የመሳሰሉ ነገሮችን አለመጠቀም፣
   - ለ. ድምጽን ሳያሰሙ ማንበብ
2. የግል መጻሕፍትን ይዞ አለመግባት፣
3. መጽሐፍትን በተገቢው ስርዓት ይዞ መገልገል፣ (በመጻሕፍት ገጽ ላይ ማስታወሻ አለመጻፍ፣ ፍሬ ነገር በሚመስሉን ላይ አለማስመር፣ የመጻህፍት ገጾችን አለመቅደድ፣ የመጻሕፍት ንጽህናን መጠበቅ፣ እንዳይገነጠሉ በጥንቃቄ መግለጥ)

**፪. መጻሕፍት ተለይተው የተቀመጡበትን መንገድ አውቆ መጠቀም**

1. የምንፈልገውን መረጃ ከየት (ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶች፣ ከጋዜጦች፣ ወዘተ.) እንደሚገኝ አስቀድሞ በመወሰን ከማውጫው መፈለግ፣
   - ሀ. መጻሕፍት ለአፈላለግ እንዲያመች በደራሲው ስም፣ በአርዕስትና በይዘት ተከፋፍለውና ማውጫ ኮድ ተሰጥቷቸው ተመዝግበው ይቀመጣሉ፡፡
   - ለ. በተመሳሳይ አኳኋን ተገልጋዮች በቀላሉ እንዲያወጧቸው በደራሲው ስም ወይም በመጻህፍቱ አርዕስት በካርድ ላይ በፊደል ተራ ወይም በመለያ ቁጥር ተራ ገብተው ከነማውጫ ኮዳቸው ይቀመጣሉ፡፡
2. ማውጫ ካርዶቹን አገላብጠን የምንፈልገውን መጽሐፍ ስናገኝ፣ የመጽሐፉን ደራሲ፣ ርዕስና የማውጫ ኮድ መዝግበን መጽሐፉ የተቀመጠበትን ቦታ መፈለግና ማውጣት ወይም የቤተመጻሕፍት ሠራተኛው እንዲያቀርብልን መጠየቅ እንችላለን፡፡

**፫. ችግር ሲያጋጥመን በማንኛውም ጊዜ የቤተ-መጻሕፍት ሠራተኛው(ዋ)ን እርዳታ ጠይቀን ማግኘት እንችላለን፡፡**

## ክፍል ሁለት:- ማዳመጥ

፩. መምህራችሁ "ደራሲና የህይወት ልምዱ" በሚል ርዕስ አንድ ማብራሪያ ሁለት ጊዜ ያነቡላችኋል። ማብራሪያውን ከማዳመጣችሁ በፊት ከርዕሱ በመነሳት የርዕሱ ትኩረት ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ።

፪. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች አንብባችሁ በአእምሮአችሁ በመያዝ ማብራሪያውን እያዳመጣችሁ መልሶቻቸውን ስጡ።

1. ልምድ ምንድን ነው?
2. ደራሲ የሚጽፈው በተግባር በራሱ ደርሰው የተገለጡለትን ልምዶች ብቻ ነው?
3. የእውናዊውና የልቦለዳዊው ዓለም አካላዊና ስነልቦናዊ አካባቢዎች ፍጹም አንድ ሊሆኑ ይችላሉ? ለምን?
4. "በልቦለድ ዓለም ውስጥ የሚከሰቱ ስሜቶችና ድርጊቶች ከደራሲው ከራሱ ልምድ የሚመነጩ እንዲሆኑ መሻት አያዋጣም" የሚባለው ለምንድን ነው።
5. ባዳመጣችሁት መሠረት ለድርሰት ዋናው ቁም ነገር ምንድን ነው?

## ክፍል ሦስት:- ንግግር

፩. ከዚህ በታች ከቀረቡላችሁ መወያያ ርዕሶች አንዱን በመምረጥ የውይይት መመሪያን ተከትላችሁ ተወያዩ። ውይይታችሁን በተሳካ ሁኔታ ለማካሔድ የሚከተሉትን ተግባራት በጥንቃቄ ፈጽሙ።

1. ከመካከላችሁ አወያይ የሚሆን አንድ ተማሪ፣ ተወያይ የሚሆኑ አራት በድምሩ አምስት ተማሪዎችን ምረጡ።
2. በተወያይነት የተመረጣችሁ ተማሪዎች ከሦስቱ የመወያያ ርዕሶች አንዱን ምረጡ።
3. በመረጣችሁት ርዕስ ላይ ያተኮሩ ጽሑፎችን በማንበብና የሚመለከታቸውን ሰዎች በማነጋገር መረጃ ሰብስባችሁና ለተከታዩ ክፍለ ጊዜ ለውይይት ተዘጋጅታችሁ ቅረቡ።

4. ተወያዮች ሀሳባቸውን ሲሰነዝሩ የቀራችሁት የውይይቱ ታዳሚዎች ሀሳባቸውን በማስታወሻ መዝግቡ፡፡
5. ስለውይይቱ ሂደትና ስለተንጸባረቁ ሐሳቦች የሚያትት የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ አንድ ገጽ ጽሑፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

***የመወያያ ርዕሶች፡-***

ሀ) የትምህርት ቤታችን ተማሪዎች የንባብ ልምድ ያለበት ደረጃ፣ ችግሮቹና መፍትሄዎቹ፤
ለ) በትምህርት ቤታችን የ"ሚኒሚዲያ" አገልግሎት ያለበት ደረጃና የሚጠናከርባቸው መንገዶች፤
ሐ) በትምህርት ቤታችን የስነ-ጽሑፍ ክበብ አስፈላጊነትና አሁን ያለበት ደረጃ፤

## የውይይት መመሪያ

ውይይት ዓላማ ያለው ክንውን ነው፡፡ ሰዎች ጊዜና ቦታ ወስነው በመገናኘት አንድና ከአንድ በላይ በሆኑ ርዕስ ጉዳዮች ዙሪያ ሐሳብ የሚለዋወጡበትና ከጋራ መግባባት ላይ የሚደርሱበት ተግባር ነው፡፡

**፩. የውይይት ዝግጅት**

1. ርዕሱን በተመለከተ መረዳት
2. ርዕሱን በተመለከተ ጽሑፎችን አፈላልጎ ዋና ዋና ፍሬ ሐሳቦችን ማገናዘብና መያዝ፣
3. "ስለ ርዕሱ የጠለቀ እውቀት አላቸው" የሚባሉ ሰዎችን ጠይቆ ፍሬ ሐሳቦችን መዝግቦ መያዝ፣
4. የተገኙትን ፍሬ ሐሳቦች ለማካሔድ ለታቀደው ውይይት ተሳታፊዎች የሚመጥኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
5. ነጥቦቹ የርዕሱን የተለያዩ ጎኖች ሊያሳዩ መቻላቸውንና ወቅታዊነታቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡

**፪. የውይይት አቀራረብ**

1. አለባበስን አስተካክሎና ንጽህናን ጠብቆ በውይይቱ ቦታ መገኘት፣
2. ተራ ጠብቆ መናገር፣
3. የሌሎችን ሐሳብ ማክበር፣
4. ያልተንዛዛና ምጥን አስተያየት መሰንዘር፣
5. የውይይቱን ርዕስና ዓላማ ባጭርና ግልጽ ቋንቋ ማስቀመጥ፣
6. ሲናገሩ ድምጽን መመጠን፣
7. ፍርሃትንና ግዴለሽነትን ማስወገድ፣
8. የውይይቱን ጭብጦች በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣
9. ፍሬ ሐሳቦችን በበቂ ማስረጃ እያስደገፉ ማቅረብ፣
10. ተገቢ የአገላለጽ ስልትን መከተል፣
11. ከታዳሚዎች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን መመዝገብ፣ ተራ ሲደርስ ተጨባጭ መልሶችን መስጠት፣ በውይይት አቀራረብ ጊዜ ልንፈጽማቸው ከሚገቡ ነጥቦች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

**፫. ባለፈው ሳምንት ያሳለፋችሁትን የእሑድ ቀን ውሎ የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉን ጠብቃችሁ ከ፫-፭ ደቂቃ የሚረዝም ንግግር አድርጉ፡፡**

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

**፩. ከዚህ በታች ስለአንቀጽ ምንነት የቀረበውን ማስታወሻ በማንበብና የተሰጠውን ምሳሌ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ ከተሰጡት ርዕሰ-ጉዳዮች አንዱን በመምረጥ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡**

1. ማርፈድ
2. ከትምህርት ቤት መቅረት
3. የጥናት መርሐ-ግብር

**፪. በጥንድ በመሆን የጻፋችሁትን አንቀጽ ከተለዋወጣችሁ በኋላ፡-**

1. የጓደኞቻችሁን አንቀጽ ኃይለ-ቃልንና መዘርዝር ዓረፍተነገሮችን ለዩ፡፡
2. አንቀጹ የያዛቸው ዓረፍተነገሮች የሐሳብ ዝምድናቸውን የጠበቁና በኃይለ-ቃሉ ከሰፈረው ዋና ሐሳብ ያልወጡ መሆናቸውን አረጋግጡ፡፡
3. ዐረፍተ ነገሮቹ ሰዋሰዋዊ ስህተት የሌለባቸው መሆናቸው መርምሩ፡፡
4. ጓደኞችሁ ተገቢ ስርዓተ ነጥቦች መጠቀሙን አረጋግጡ፡፡
5. ስለመረመራችሁት አንቀጽ ለጓደኞችሁ አስተያየት ስጡ፡፡

## አንቀጽ

አንቀጽ ማለት አንድ ነጠላ ሐሳብን ለመግለጽ ሲባል፣ በቁጥር አንድ ወይም ከአንድ የበለጡና የሐሳብ ተዛምዷቸውን የጠበቁ ዓረፍተነገሮች የሰፈሩበት የድርሰት ቅርጽ ነው፡፡ አንቀጽ ብዙውን ጊዜ አንድ ኃይለ ቃል (መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር) እና ከአንድ በላይ መዘርዘር ዓረፍተነገሮችን ሊይዝ ይችላል፡፡ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት፡-

ምሳሌ፡-

የትምህርት ቤታችን የስፖርት እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡ ከሁለት ዓመት በፊት በእግር ኳስና በመረብ ኳስ ስፖርቶች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል በነበሩ ተማሪዎች መካከል ውድድሮች ተካሂደው ነበር፡፡ ባሳለፍነው የትምህርት ዘመንም የውድድር ዓይነቶቹን ከሁለት ወደአራት በማሳደግ በእግር፣ በመረብ፣ በእጅና በቅርጫት ኳስ የውስጥ ውድድሮችን አካሂዷል፡፡ በያዝነው የትምህርት ዘመን ደግሞ በአራቱም የውድድር ዓይነቶች የውስጥ ውድድሮች ከማካሔዱም በላይ፣ የከተማው ባህልና ስፖርት መምሪያ ባዘጋጀው የዘመኑ ውድድር ላይ በእግር ኳስና በመረብ ኳስ በመሳተፍ አመርቂ ውጤት በማስመዝገብ ላይ ይገኛል፡፡

በዚህ ምሳሌ እንደሚታየው በአንቀጹ ኃይለ ቃል "የትምህርት ቤታችን የስፖርት እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡" በሚል የሰፈረው ዋና ሐሳብ ከሱ በኂላ በመጡት መዘርዝር ዓረፍተነገሮች ተብራርቷል፡፡ በመዘርዝር ዓረፍተነገሮቹ በመጀመሪያ የስፖርት እንቅስቃሴው በሁለት የውድድር ዓይነቶችና በውስጥ ውድድር ጀምሮ፣ በየጊዜው ባደረገው መሻሻል የውድድር ዓይነቶቹን ወደአራት እንዴት እንዳሳደገና ከውስጥ ውድድሮች በተጨማሪ የውጪ ውድድሮችንም መሳተፍ እንደጀመረ ደረጃ በደረጃ ተብራርቷል፡፡

**፫. ከዚህ በታች በቀረበው አንቀጽ ውስጥ በተጓደሉ ስርዓተ ነጥቦች ምትክ ቁጥሮች ሰፍረዋል፡፡ በቁጥሮቹ ቦታ መግባት ያለበትን ስርአተ ነጥብ ግለጹ፡፡**

መጠጥ አካልና መንፈስን ያዳክማል፡፡ በአኗኗሩ ጠንቃቃ 1__ በአስ ተሳሰቡ በሳል 2__ በሥራውም ክቡር የሆነ ሰው በጠጣ ጊዜ መንፈሱ ይደክማል፤ አካሉ ይዝላል 3__ ምላሱ ይተሳሰራል፡፡ ስካሩ የፀና ከሆነም እግሩ እየከዳው … እግሮቹ ተሳስረው እየወደቀ 4__ ለመነሳት እየቧጠጠ 5__ ባለበት ይዳክራል፡፡ "6__ ያለበት ዝላይ አይችልም" እንዲሉ፣ ሳይጠይቁት ይመልሳል 7__ ሳያናግሩት ያናግራል፡፡

## ነጠብጣብና ድርብ ሰረዝ

በጽሑፉ ውስጥ የስርዓተ ነጥቦች ዋነኛ ተግባር የጽሑፉ መልእክት ሳይድበሰበስ በአፍታ እይታ ለአንባቢው እንዲከሰት ማገዝ ነው፡፡ በጽሑፍ ውስጥ ጥቅም ላይ ከሚውሉ የስርዓተ ነጥብ ዓይነቶች መካከል ነጠብጣብና ድርብ ሰረዝ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

### (…) ነጠብጣብ

1. ከጽሑፍ ወይም ከጥቅስ ውስጥ የተወሰነውን ቃል ወይም ክፍል ያስቀረነው መሆኑን ለማመልከት፣
   ምሳሌ፣ "አባቷን አታውቅ…." እንዲሉ
   "አባቷን አታውቅ፣ አያቷን ትናፍቅ፡፡"
2. በፈጠራ ድርሰት ውስጥ አንባቢ የቀረውን በሀሣቡ እንዲሞላና የሚሆነውን እንዲረዳ ሲፈልግ፣
   ምሳሌ፣
   አልቀመጥም፤ እኔ የመጣሁት ካንተ አንዲት ቃል ተንፈስልኝ፡፡ ስትለው…

*(ሲሳይ፣ ሰመመን፣1996፣153)*

### (፤) ድርብ ሰረዝ

የሐሳብ ቁርኝት ያላቸውን ዓረፍተነገሮች አጣጥሞ ለማቅረብ ያገለግላል፡፡ ድርብ ሰረዝ ለዓረፍተነገር መቋጫነት ከምንጠቀምበት አራት ነጥብ የሚለየው ደግሞ፣ አራት ነጥብ ዓረፍተነገሩ ማለቁን ከሚጠቁመን በስተቀር በሱና ከኋላው በተሰለፉት ሌሎች ዓረፍተነገሮች መካከል ያለውን የሐሳብ መያያዝ አያመለክትም፡፡

**፩. ቀጥሎ "ፈሪው ወታደር" በሚል ርዕስ አንድ ተራኪ ድርሰት ቀርቦላችኋል፡፡ ድርሰቱን በጥንቃቄ ካነባባችሁ በኋላ፣ በስተመጨረሻ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፡፡**

## ፈሪው ወታደር

"አንድ ትልቅ ጦርነት ሲካሄድ ተካፋይ የነበረ አንድ ፈሪ ወታደር ነበር፡፡ በጦርነቱ አብረውት የተሰለፉ ጓደኞቹ ደረታቸውን ለጥይት ሰጥተው በጀግንነት ተዋጉ፤ እየተመቱም አንዳቸው ባንዳቸው ላይ እየተደራረቡ ወደቁ፡፡ ይህንን ያየው ቡቡው ወታደር ሆዱ ተሸበረበት፤ ጉልበቱም ቄጤማ ሆነበት፡፡ ከዚያ ስፍራ ከሬሳ በስተቀር አንድም የሚያውቀው ወታደር ማየት አልቻለም ነበር፡፡

ጦርነቱ እሱ ባለበት በኩል እያደር እየተፋፋመና እየተጋጋለ መጣ፡፡ በዚህ ጊዜ መክቶ መቋቋም፣ እሩጦም ማምለጥ እንደማይችል ተገነዘበ፡፡ "እንግዲህ ከዚህ በቀር ሌላ ነገር የሚያድነኝ የለም" አለና፣ የተደራረቡትን እሬሳዎች ፈነቃቅሎ ገባ፡፡ አንዱን እሬሳ በላዩ ላይ ጭኖ ትንፋሹን አሳጥሮ ተኛ፡፡

የወዲያኛውም የወዲህኛውም ወገን በሾተል እየተጠማዘዘ፣ በፎቄ እየተጓመደ፣ እያወካ፣ እየተዋጋ፣ እየተተራመሰ እሱ ወደተሸሸገበት በጣም እየቀረበ መጣ፡፡ አጠገቡ በደረሰ ጊዜ "የፈረስ አጓዳ ከአሁን አሁን ያደበየኛል" ሲል ሲፈራ ቆይቶ እንደምንም እግሩን ይሰበስባል፡፡ ወዲያው አንድ ተዋጊ ፈረሰኛ አየው፡፡ ከፈረሱ ላይ እንደሆነም የዚያን ሳይቆስል የሞተ ሰው እግር በቀጭን ሹል ጦሩ ጠቆም ጠቆም እያደረገ "ይሄስ የሞተ አይመስልም" አለ፡፡ በዚህ ጊዜ ያ በውሸት የሞተ ፈሪ ወታደር "አይ! አይ!" እያለና እግሩን እያንፈራገጠ፣ "እሽ ተወኝ ሞቻለሁ" አለ አፉን በእጁ እየተመተመ፡፡

*(ዳኛቸው፣የድሁፍ ጥበብ መመሪያ፣1977፣178-179 ተሻሽሎ የቀረበ)*

1. በትረካው የተገለጹት ድርጊቶች የተከናወኑት የት ነው?
2. በትረካው የተከናወኑትን ድርጊቶች በጊዜ ቅደም ተከተል ባጭር ባጭሩ ዘርዝሩ፡፡ በመጀመሪያ ምን ሆነ? ከዚያስ?
3. ትረካውን የተረከልን ማን ነው?

## ተራኪ ድርሰት

ተራኪ ድርሰት በጣም ከተለመዱት አራት ዋና ዋና የድርሰት ዓይነቶች አንዱ ነው፡፡ የቀሩት ሦስቱ ስዕላዊ ድርሰት፣ ገላጭ ድርሰትና አመዛዛኝ ድርሰት በመባል ይታወቃሉ፡፡

ተራኪ ድርሰት ድርጊቶችንና ሰንሰለታዊ አውነቶችን የድርጊት የጊዜ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቆ "እንዲህ እንዲህ ሆነ፤ እንዲህ እንዲህ ተደረገ፡፡" እያለ የሚተርክልን ጽሑፍ ነው፡፡ ታሪኩን የሚነግረንም እራሱ የድርጊቱ ተካፋይ ሊሆን ይችላል፡፡ አለበለዚያም ድርጊቱን የተመለከተ፣ የደረሰበት፣ በልምድ ያገኘው፣ ከሌላ ሰምቶ የሚያቀርበው ሊሆን ይችላል፡፡ ከላይ በጥያቄ ቁጥር ፬ ሥር የቀረበው ተራኪ ድርሰትም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል፡፡

**ፎ. የሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ቅደም ተከተላቸው ቢስተካከል አንድ ተራኪ አንቀጽ ይወጣቸዋል፡፡ ዓረፍተነገሮቹን በጥንቃቄ መርምራችሁ ቅደም ተከተላቸውን አስተካክሉ፡፡ ለድርሰቱም ርዕስ ስጡ፡፡**

1. በክረምት ለእረፍት ትምህርት ቤት ሲዘጋ እንደምጠይቃት አስቀድሜ ለአክስቴ ቃል ገብቼላት ነበር፡፡
2. በዚያው ሰሞን እናቴ አክስቴን ጠይቃ ስትመለስ፣ አክስቴ ብቻዋን እንደምትኖር የነገረችኝ ትዝ አለኝና ምናልባት የሚሰማኝ ያጣሁት ደህና ባትሆን ይሆናል ብዬ አሳብ ገባኝ፡፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝም ማሰላሰል ቀጠልኩ፡፡
3. በልጅነቴ የምወዳትን አክስቴን ለመጠየቅ ወደ ፍቼ ከተማ በሄድኩ ጊዜ ያጋጠመኝ ነገር መቼም አይረሳኝም፡፡
4. ለግማሽ ሰዓት ያህል ከቆየሁ በኋላ፣ ባረጀውና ቁመቱ በጣም ከፍ ባለው የፍልጥ አጥር ላይ ተንጠልጥዬ አክስቴን ለመጥራት ወሰንኩ፡፡

5. የአክስቴን ዐይን ለማየት ብቸኩልም ወደ ቤቷ አጥር ግቢ ከመድረሴ በፊት ጥቅጥቅ ባለው የባህርዛፍ ጫካ ውስጥ ጥቂት መጓዝ ነበረብኝ፡፡
6. እኔም ከታች አግጥጦ ከሚጠብቀኝ ጉቶ ላይ አረፍኩ፡፡ ከዚያ በኋላማ ሁለት የጎድን አጥንቶቼ ተሰብረው አክስቴ አልጋ ላይ እንደተኛሁ ከመንቃቴ በስተቀር በመካከል የሆነውን ነገር ሁሉ አላስታውስም፡፡
7. ድካሜን ሁሉ ረስቼ ጫካውን በሩጫ በማለፍ እውጪው በር እንደ ደረስኩ በሩን ቆሎ ቆሎ አንኳኳሁ፡፡ ነገርግን፣ “ማን ነህ?” የሚለኝ አጣሁ፡፡
8. እንደምንም ብዬ በመውጣት አጥሩ ጫፍ እንደደረስኩ የጨበጥኩት የበሰበሰ ፍልጥ ተሰበረ፡፡
9. የሐምሌን ጭጋግና ዝናብ ችዬ በልጅ እግሬ እየገሰገስኩ ከምኖርባት የገጠር መንደር ከአዲስጌ ግማሽ ቀን ተጉዤ ስድስት ሰዓት ገደማ ፍቼ ከተማ ደረስኩ፡፡
10. እንደገናም በሩን ደጋግሜ ደበደብኩት፤ ምንም መልስ የለም፡፡

**፮. በቡድን ሆናችሁ አንድ ተራኪ ድርሰት መጻፍ እንድትችሉ የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም ተከተል አከናውኑ:-**

1. እየተወያያችሁ ርዕስ ምረጡ፡፡
2. በርዕሱ ሊካተቱ የሚገባቸውን ነጥቦች በአስተዋጽኦ መልክ ዘርዝሩ፡፡
3. በሐሳብ የሚቀራረቡ ዝርዝሮችን እየለያችሁ ባንድ ላይ መድቡ፡፡
4. ስለአንቀጽ በተማራችሁት መሠረት፣ የድርሰቱን የመጀመሪያ ረቂቅ ጻፉ፡፡
5. የጻፋችሁትን የድርሰት ረቂቅ አንብባችሁ የስርዓተ-ነጥቦችና የሰዋስው ግድፈቶችን በማረም እንደገና ጽፋችሁ አቅርቡ፡፡
6. ድርሰታችሁን ከሌላ ቡድን ጋር በመለዋወጥ ከሐሳብ ፍሰቱ፣ ከድርጊትና ጊዜ ቅደም ተከተል አጠባበቁ፣ ከስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀሙ አንጻር መርምራችሁ የቡድናችሁን አስተያየት ስጡ፡፡

## ማጠቃለያ

ምዕራፍ ሦስት በዋናነት ያተኮረው በስነ-ጽሑፍ ምንነትና የመኖር ምክንያቶች ላይ ነበር:: በዚሁ መሠረት ስነ-ጽሑፍ በአገላለጽ ትባቱ፣ በህይወት ማሳያነቱ፣ በሳቢነቱና በግለ ወጥነቱ የተዋጣለትና ኪነ-ጥበባዊ ብቃቱ የተመሰከረለት የፈጠራ ሥራ እንደሆነ አይተናል:: ለስነ-ጽሑፍ መኖር ሦስት ምክንያቶች እንዳሉ አንስተን በዝርዝር አብራርተናቸዋል:: በዚህም ደራሲው ስለገጠመኙ ለመናገር ያለው ፍላጎት፣ለሰው ልጅና ለውበት ያለውን ጥልቅ ፍቅር ተመልክተናል:: ከዚህ በተጨማሪም ለቃላት ቀጥተኛ አገባባዊ ፍች ሰጥተናል::

ስለ ቤተ-መጻሕፍት በተወያየንበት ክፍልም በቤተ-መጻሕፍት ውስጥ የምንከተላቸውን ዋና ዋና ደንቦችና ስርዓቶች ለይተናል:: መጻሕፍት ተለይተው የተቀመጡበትን አውቀን መጠቀም ስለማያስችሉን መንገዶችም ተረድተናል:: በቤተመጻህፍት ባግባቡ መገልገልና የምንፈልገውን መረጃ ማግኘት ችለናል:: በአንድ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ማብራሪያን አዳምጠን በማብራሪያው ይዘት ላይ ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን መመለስ ችለናል:: ከዚህም ሌላ የውይይት መመሪያን ጠንቅቀን አውቀን መወያየት ችለናል:: በተጨማሪም የውይይታችንን ፍሬ ሀሣብ ጨምቀን አውጥተናል:: በተሰጠን ርዕስ የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን የጠበቀ ንግግር አድርገናል::

በሌላ በኩል ስለአንቀጽ ምንነት ባየንበት ክፍል አንቀጽን በማዋቀር ሂደት ልናውቃቸው የሚገቡ ነጥቦች ለይተናል:: አንቀጽ ጽፈንም እርስ በእርስ ተራርመናል:: በጽሑፋችን ውስጥ የስርዓተ ነጥቦችን ጠቀሜታ በተለይም በድርብ ሰረዝና በነጠብጣብ ላይ አትኩረን ተመልክተናል:: በጽሑፋችንም ተገቢ ስርዓተ ነጥቦችን መጠቀም ችለናል:: በመጨረሻም የተራኪ ድርሰት ምንነትን አውቀን ተራኪ ድርሰት መጻፍ ችለናል::

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በውይይት ጊዜ ማስታወሻ የምንይዝባቸው ሁኔታዎችን ዘርዝሩ፡፡
2. አንድ አንቀጽ መንደርደሪያ ሐሳብ ሊኖረው የሚገባው ለምንድን ነው?
3. ስለ አንቀጽ ምንነትና ባህሪ በተማራችሁት መሠረት በመረጣችሁት ርዕስ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡
4. ከዚህ ቀደም በራሳችሁ ወይም በጓደኞችሁ የደረሰ አንድ ገጠመኝ በማስታወስ አንድ ተራኪ ድርሰት ጻፉ፡፡
5. ለጻፋችሁት ድርሰት ርዕስ ስጡ፡፡

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሦስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በአያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ /✓/፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ /?/፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ /x/ ምልክቶችን በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳረከሪያ ነጥቦች | (✓) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ለቃላት ቀጥተኛ ፍች መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 2 | ለቃላት አገባባዊ ፍች መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 3 | በጽሑፍ ውስጥ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታቸው ላይ መጠቀምን አውቄአለሁ፡፡ | | | |
| 4 | የውይይት መመሪያን ተረድቼ በውይይት መሳተፍ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 5 | የአንቀጽ ምንነትን ተረድቼ አንቀጽ ጽፌአለሁ፡፡ | | | |
| 6 | የተራኪ ድርሰትን ምንነት አውቄ ተራኪ ድርሰት መጻፍ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 7 | የስነ-ጽሑፍ ምንነትና የመኖሩን ምክንያት በትክክል ማስረዳት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 8 | የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም መመሪያን ተረድቻለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ/?/ እና የ /x/ ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ደረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ልቦለድ

**የምዕራፉ ዓላማዎች:- ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ:-**

- ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ትሰጣላችሁ::
- የመሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትን ምንነትና ተግባር ትገልጻላችሁ::
- ቃላትን በየቃል ክፍላቸው ትመድባላችሁ::
- የግሦችን ቅርጽ በመለዋወጥ ሌሎች ግሦችን ትመሰርታላችሁ::
- የሐረጋትን ምንነት ትገልጻላችሁ::
- ያዳመጣችሁትን ፍሬ ሀሳብ ትጽፋላችሁ::
- በስርዓት ትከራከራላችሁ::
- ከተለያዩ ንግግሮችና ጽሑፎች ማስታወሻ ትይዛላችሁ::
- ለምትጽፉት ጽሑፍ አስተዋጽኦ ታዘጋጃላችሁ::
- የልቦለድን፣ የአጭር ልቦለድንና የልቦለድ አላባውያንን ምንነት ታብራራላችሁ::
- የዘይቤዎችንና የፈሊጣዊ አነጋገሮችን ምንነት ትገልጻላችሁ::

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. አጭር ልቦለድ ከረጅም ልቦለድ ተለይቶ የሚታወቀው በምንድን ነው?

፪. ካነበባችኋቸው ወይም ካዳመጣችኋቸው ልቦለዶች መካካል ከሌሎቹ በበለጠ የምታስታውሱት የትኛውን ነው? ይህን ልቦለድ እንድታስታውሱ ያደረጓችሁን ምክንያቶች ግለጹ፡፡

፫. ከዚህ በታች አንድ አጭር ልቦለድ ቀርቦላችኋል፡፡ የልቦለዱን ርዕስና የልቦለዱን የመጀመሪያ አንቀጽ በማንበብ ስለምን እንደሚተርክ ገምቱ፡፡

፬. ጽሑፉስ ከጽሑፍ ዓይነቶች ውስጥ በየትኛው ይመደባል? ለምን?

## ወንድማማቾቹ

ጊዜው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሃያ ዓመት በኋላ ነው፤ ቦታው "ጃኑዳ" የሚባል ውብ ከተማ፡፡ የከተማው ት/ቤት ዳይሬክተር ስም ዘነበ ሲሆን፣ በልዩ የሚባል ወንድም ነበረው፡፡ ወንድማማቾቹ ለወላጆቻቸው **እንደአህያ ጡት ሁለት ሲሆኑ**፣ በልጅነት እድሜያቸው እርስ በርሳቸው በጣም የሚተሳሰቡና የሚሠሩትን ሥራ ሁሉ በአንድነት የሚያከናውኑ ነበሩ፡፡ ወታደር ለመሆን በአንድነት ተመዘገቡ፣ ወደ ጦርነት በአንድነት ዘመቱ፤ በአንድ የጦር ክፍል ውስጥ በአንድነት አገልግለው በአንድ ጊዜ የአስር አለቅነት ማዕረግ አገኙ፡፡ ከጦርነት ሲመለሱም የከተማዋ ነዋሪ «ቁም ነገረኛ ወጣቶች» እያለ **ያሞካሻቸው** ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ አባታቸው ሞቱ፡፡ የአባታቸው ንብረት እኩል ለሁለት ለመካፈል የማይመች ነበር፡፡ ስለዚህም እቃው ለጨረታ ቀርቦ እያንዳንዱ የፈለገውን ከገዛ በኋላ፣ ገንዘቡን ለሁለት ለመካፈል ተስማሙ፡፡ በዚህ መልክ ንብረቱ ተሸጦ ተካፈሉ፡፡ ነገር ግን፣ አባትየው በአካባቢው አንድም ሰው ያላደረገው ዓይነት ትልቅ የወርቅ ሰዓት ነበራቸው፡፡ ሰዓቱ ለጨረታ በቀረበ ጊዜ ሁለቱ ወንድማማቾች መጫረት ሲጀምሩ፣ ሌላው ተጫራች ህዝብ ለቆላቸው ከጨረታው ወጣ፡፡ በዚህ ጊዜ ዘነበ ያሰበው፣ በልዩ ይለቅልኝና እኔ እወስዳለሁ የሚል ነበር፡፡ በልዩም በበኩሉ እንዲሁ ይመኝ

ነበር፡፡ ጨረታው ቀጥሎ አንድ ሺ አምስት መቶ ብር ደረሰ፡፡ በዚህ ጊዜ ዘነበ፣ «ወንድሜ የሚሠራው ሥራ ጥሩ አይደለም» ብሎ አሰበ፡፡ ስለዚህም አንድ ሺ ስድስት መቶ ብር እስኪደርስ ድረስ እሱም በበኩሉ ዋጋውን ከፍ አደረገ፡፡ በልዩ አሁንም ከጨረታው እንዳልወጣ ባየ ጊዜ፣ ‹‹በውነቱ ጥሩ ሥራ አይሠራም፣ እንዴት እኔ የዋልኩለትን ውለታ ሁሉ ቸል ብሎ ጨረታውን **ያንርብኛል**፤ ወዲያውም እኮ ታላቅ ወንድሙ ነበርኩ›› ብሎ አሰበ ፡፡ ከዚህ በኋላ የሰዓቱ ዋጋ ከአንድ ሺ ስምንት መቶ ብር በላይ ወጣ፡፡ በልዩ ከፍ አድርጐ መስጠቱን አላቋረጠም፡፡ ከዚያም ዘነበ በአንድ ጊዜ ሁለት ሺ ብር አደረሰውና ወደ ወንድሙ ዘወር ብሎ እንኳ አልተመለከተም፡፡ በጨረታው አዳራሽ ፀጥታ ሰፈነ ፡፡ አጫራቹ ብቻ የተጠራውን ዋጋ እየመላለሰ ይናገር ነበር፡፡ እዚያ ቦታ ብዙ ሰዎች ቆመው ይመለከቱ ስለነበር፣ በልዩም፣ ‹‹ወንድሜ በነዚህ ሰዎች መካከል መሳቂያ ሊያደርገኝ አይችልም›› በማለት፣ አሁንም ጨረታውን በመቶ ብር ከፍ አደረገ፡፡ ዘነበ ድንገት በሳቅ ፈንድቶ፣ ‹‹ሶስት ሺ ብር እና የኔንም ወንድምነት ከዚሁ ጋር›› ካለ በኋላ፣ እየሮጠ ካዳራሹ ወጥቶ ሄደ፡፡

ዘነበ ፈረሱን እየጫነ ለመሔድ በሚዘጋጅበት ጊዜ፣ አንድ ሰው ካዳራሹ ወጥቶ ወደርሱ ቀረበና ‹‹ሰዓቱ ያንተ ነው፤ በልዩ ተሸንፏል›› አለው፡፡ ይህንን እንዳወቀ፣ ወዲያው የፀፀት ስሜት ተሰማው፡፡ በዚህ ወቅት ስለወንድሙ እንጂ ስለሰዓቱ አላሰበም ነበር፡፡ "ወደ ቤቴ ልሂድ? ወይስ ልቅር?" እያለ ግራ ተጋብቶ ቆመ፡፡ የጨረታው **ታዳሚዎች** ካዳራሹ ወጡ፤ በልዩም በመካከላቸው ነበር፡፡ ወንድሙ ለመሄድ ተዘጋጅቶ ባየው ጊዜ፣ ሐሳቡን እንደለወጠ ተረዳና፣ "ስለሰዓቱ አመሰግንሃለሁ ዘነበ፣ ከእንግዲህ በኋላ ወንድምህ አንተን እየተከተለ የሚሄድበትን ጊዜ ደግመህ አታየውም!›› በማለት፣ ጮሆ ተናገረ፡፡ “አንተም! ሁለተኛ እኔ ላንተ እሠራ የነበረውን ሁሉ ፈጽሞ ደግመህ አታየውም!” ብሎ ሲመልስለት፣ **ነብር ሆኖ** ነበር፡፡ ወዲያውም ፈረሱ ላይ እመር ብሎ ወጥቶ እየጋለበ ሄደ፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ሁለቱም ከአባታቸው ጋር አብረው ይኖሩበት የነበረውን ቤት እግራቸው ረግጦት አያውቅም፡፡

በልዩ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የአንድ ድሃ  ገበሬ ልጅ አገባ:: ነገር ግን ወንድሙን ለሰርግ አልጋበዘውም:: ባገባ በአንድ ዓመቱ፣ ከቤቱ ራቅ ብላ ታስራ ሳር ትበላ የነበረች አንድ  ላሙ ሞታ ተገኘች:: የአሟሟቷንም እንቆቅልሽ ማንም ሊፈታው አልቻለም:: ተመሳሳይ መጥፎ እድሎች ተከታትለው ደረሱበት:: ይባስ ብሎም፣ በክረምት ወቅት  የድርቆሽ ዳሱ ከበርካታ ንብረቱ ጋር ተቃጠለ:: እሳቱ ከየት እንደተነሳ ያወቀ ግን አልነበረም:: "ይህ ሁሉ የተደረገው እኔን ለመጉዳት ባሰበ ሰው ነው::" በማለት፣ ስቅሰቅ ብሎ አለቀሰ:: **ሰማዩ በላዩ ተደፋበት**:: ድሃ እየሆነ ስለሄደም የመሥራት ፍላጎቱ ተዳከመ:: ´ቤቱ ውስጥ ቁጭ ብሎ ሲተክዝ መዋል አበዛ::

ከእሳቱ ቃጠሎ በኋላ አንድ ቀን ምሽት ላይ፣ ዘነበ ወደ ወንድሙ ቤት ሄደ:: በልዩ አልጋው ላይ ጋደም ብሎ ነበር :: "ምን ልትፈልግ ነው እዚህ የመጣኸው?" ብሎ፣ ከመኝታው ብድግ በማለት ወንድሙ ላይ አፈጠጠ:: "ልረዳህ ነው የምፈልገው በልዩ! በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ነህ" በማለት መለሰለት:: "አዎ! የኔ ደግ ሰው¡ ልትረዳኝ መጣህ¡" አለና "አንተ ከምትመኝልኝ የበለጠ አልደረሰብኝም፤ ከፊቴ ወግድልኝ፤ አለዚያ ምን እንደሚሆን እግዜር ነው የሚያውቀው!" ሲል ዐይኑን አጉረጠረ ጠበት:: ዘነበ ወንድሙ **ደሙ መፍላቱን** ባየ ጊዜ፣  ወደ ኋላ አንድ ርምጃ ፈቀቅ በማለት ከንፈሩ እየተንቀጠቀጠ፣ "ሰዓቱን ከፈለግክ መውሰድ ትችላለህ " አለው:: በልዩ ግን አሁንም "ወግድልኝ!"  ሲል **አምባረቀበት**:: ዘነበም ከዚህ በኋላ መቆየቱ ዋጋ የሌለው መሆኑን ስላወቀ፣ ወንድሙን ትቶት ሄደ::

ከዚህ ቀን በፊትም ቢሆን ዘነበ በየጊዜው ስለወንድሙ ያስብ ነበር:: በተለይ አደጋ ከደረሰበት በኋላ አስተሳሰቡ ተለውጦ ነበር:: ቤተክርስቲያን ሄዶ ግንኙነታቸውን ለማሻሻል ቃል ገብቷል:: ነገር ግን ይህንን ለመፈጸም **ልብ አላገኘም**::

አንድ እሁድ ቀን ቤተክርስቲያን በሄደ ጊዜ፣ ወንድሙ በልዩም እዚያው ነበር:: ገርጥቶና ከስቶ፣ ያረጀና የተጣጣፈ ልብስ ለብሶ ተመለከተው::

በዚህ ጊዜ ወንድሙ ለርሱ እንዴት ያለ ርህሩህና ጨዋ ልጅ እንደነበረ ማስታወስ ጀመረ:: «የመጣው ቢመጣ ዛሬ ከወንድሜ ጋር እታረቃለሁ» ብሎ ለፈጣሪው ቃል ገባ:: ከወንድሙ ጐንም ለመቆም ቆረጠ:: ይሁን እንጂ፣ በመካከላቸው የሚከልል ነገር መኖሩን ዘነበ ልብ አላለም:: ከቅዳሴውም በኋላ ሚስቱ ልትሆን ትችላለች ብሎ የጠረጠራት ሴት አጠገቡ እንዳለች አስተውሏል:: በርካታ ሰዎች በአካባቢው ስለነበሩም "እቤቱ ሄጄ ረጋ ብዬ ባናገረው ይሻላል" ብሎ ወሰነና ወደ ቤቱ ተመለሰ::

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ታሪኩን ከማንበባችሁ በፊት የገመታችሁት ትክክል ሆነ ወይስ አልሆነም? ለምን? በማስረጃ ግለጹ::
2. በልቦለዱ የእስካሁን ክፍል ምን ምን ነጥቦች ተነሱ?
3. በቀጣዩ የልቦለዱ ክፍል በሁለቱ ወንድማማቾች መካከል ምን ምን ክስተቶች የሚፈጠሩ ይመስላችኋል?
4. ታሪኩ በምን መልኩ ይቋጫል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ማስረጃችሁስ ምንድን ነው?

ቀኑ ሲመሽ ወደ ወንድሙ ቤት አመራ:: በሩ አጠገብ ሲደርሰም ትንሽ ቆም ብሎ እንደማሰብ ሲል፣ ከቤት ውስጥ የእርሱ ስም ሲጠራ ሰማ:: የወንድሙ ሚስት ነበረች፣ ስሙን እያነሳች የምትናገረው::" ወንድምህ ዛሬ ቀረበ እኮ! እርግጠኛ ነኝ ስላንተ ያስብ ነበር" አለች:: "እባክሽ ስለኔ አይደለም፤ ስለራሱ ነው የሚያስበው "አለ፣ በልዩ:: ከዚህ በኋላ ለረጅም ጊዜ ድምጽ አልተሰማም:: ጥቂት ቆየና ዘነበ እዚያው እንደቆመ፣ ላብ አጠመቀው:: የምድጃው እሳት እየተንጣጣ የነበልባሉ ድምጽ ይሰማል:: በልዩ ወደ ውጭ ለመውጣት ከተቀመጠበት ተነሳ:: ዘነበ ቶሎ ብሎ ዛፍ ስር መደበቅ ነበረበት፣ ተደበቀ:: በልዩ አንድ እቅፍ እንጨት ለማስገባት፣ ወንድሙ ወደተደበቀበት ዛፍ አመራ:: የዘነበ የልብ ምት ጨመረ:: አሁንም እየተጠጋው መጣ:: ዘነበ ትኩር ብሎ አየው:: በልዩ የጥንት የደንብ ልብሱን (የወታደር) ለብሷል:: "እነዚህን ልብሶች ሁለተኛ

አንለብሳቸውም፤ ለልጆቻችን እናወርሳቸዋለን" ተባብለው፣ ቃል ተግባብተው እንደነበር አስታወሰ። ከልቡ ምት መጨመር ጋር፣ በኪሱ የያዘው የወርቅ ሰዓት ቲክቲክታም ይሰማ ነበር። በልዩ፣ "እህህ!" በማለት ተነፈሰና፣ ተዘዋውሮ ሳይመለከት እቅፍ ሙሉ ጭራሮውን ይዞ ሲመለስ፣ ወንድሙን በጣም ተጠግቶ ያልፍ ስለነበር፣ በጭራሮው ጫፍ ፊቱን ቧጭሮት አለፈ።

ከአስር ደቂቃ ቆይታ በኋላ ከዛፉ ስር በመውጣት፣ የወንድሙን ወደቤቱ መግባት እንዳረጋገጠ ሌላ ዘዴ መፈለግ ያዘ። ከአመድ ማጠራቀሚያው በርሜል ከሰል በመውሰድና ጭራሮ ለቃቅሞ ወደ ድርቆሹ ዳስ በመግባት እሳት አነደደ። በእሳቱ ብርሐንም ወንድሙ ፋኖስ የሚሰቅልበትን ሜንጦ ስላየ፣ ሰዓቱን በሜንጦው ላይ አንጠልጥሎ ፍሙን በማጥፋት ወደ ቤቱ አመራ። ጭንቀቱ ስለተቃለለለትም፣ በዚያ ቅዝቃዜ ሲሮጥ የወጣትነት ኃይል ይሰማው ነበር።

በሚቀጥለው ቀን የድርቆሹ ዳስ ተቃጥሎ ማደሩን ሰማ። ምናልባት፣ ማታ ያነደደው እሳት ፈጽሞ ሳይጠፋ ቀርቶ ሳያቃጥለው አልቀረም ይሆናል። ይህም ሁኔታ ዘነበን በጣም አሳዘነው፤ **ሀፍረትም ለበሰ**። ከዚያም የጸሎት መዝሙሩን መጽሐፍ አውጥቶ ጮህ ብሎ ዘመረ። ይኸንን የሰሙ የአካባቢው ሰዎች፣ የሆነ ነገር እንደደረሰበት ጠረጠሩ። ቀኑ በጨለማ ሲተካ፣ ዘነበ በጠፍ ጨረቃ ወደ ወንድሙ ቤት በመሄድ፣ ከቃጠሎው መካከል አንድ ቦታ ቆፍሮ አንድ ነገር አወጣ ፤ ከዚያ ሰዓት የቀረው አንድ የተጨባበጠ ወርቅ ነበር። ይህንን በመያዝና ወደ ወንድሙ ዘንድ በመሔድ፣ ሁሉን ነገረ ለመግለጽና እንደገና ለመታረቅ ፈለገ።

ነገር ግን "እንዴት አድርገህ ዛሬ ደፍረህ ትሄዳለህ?" ብለው፣ ሰዎች አስጠነቀቁት። ምክንያቱም፣ አንዲት ትንሽ ልጅ ቃጠሎው መካከል ቆሞ ሲቆፍር ማየቷን ተናግራለች። የአካባቢው ነዋሪ ወጣቶችም፣ ዳሱ የተቃጠለ እለት ዘነበን ወደ ወንድሙ ቤት ሲሄድ እንዳዩት ተናግረዋል። በማግስቱ ሰኞም፣ የጠባይ ለውጥ ማሳየቱን ሁሉም ሰዎች ያውቁ ነበር። የአካባቢው ባለስልጣኖችም ይህ መረጃ ስለደረሳቸው ለማጣራት

ወስነዋል፡፡ በልዩ ደግሞ እነዚህ ሁሉ ወሬዎች ደርሰውት ስለነበር፣ ድርጊቱን የፈጸመው ወንድሙ እንደሆነ አምኖ ተቀብሏል፡፡

በዚህ ሁኔታ እያለ ነበር፣ ጉዳዩን ለማጣራት ለሁለቱም ጥሪ የደረሳቸው፡፡ ዘነበ ጥሩ ልብሱን፣ በልዩ ደግሞ **ጭርንቁሱን** ለብሰው ሁለቱም ምርመራው ቦታ ተገኙ፡፡ ዘነበ ወንድሙን ተመለከተው፡፡ በልዩም አስተዋለው፡፡ በልዩ፣ ወንድሙ ይቅርታ እየጠየቀው መሆኑን ዓይኑ እንደሚናገር አመነ፡፡ “ስለ´ርሱ ምንም ነገር እንድናገር አይፈልግም ማለት ነው” ብሎ አሰበ፣ በልዩ፡፡ ስለዚህም በድርጊቱ ወንድሙን የሚጠረጥረው እንደሆነ ሲጠየቅ፣ ድምጹን ከፍ አድርጐ በመጮኽ "አልጠረጥረውም" አለ፡፡ ከዚያን ቀን በኋላ፣ በልዩ አልኮል በብዛት መጠጣት ጀመረ፡፡ ሁኔታዎች ሁሉ ተበላሹ፡፡ ዘነበም ቢሆን፣ ምንም እንኳን መጠጥ ባይጠጣ፣ መልኩ ስለተለዋወጠና ስለተጐሳቆለ፣ እሱ መሆኑን ለማወቅ አዳጋች ሆኖ ነበር፡፡

አንድ ቀን ማታ ዘነበ ወደ ተከራያት ትንሽ ክፍል አንዲት ድሃ ሴትዮ ገብታ ከርሷ ጋር እንዲሄድ ጠየቀችው፡፡ የወንድሙ ባለቤት ነበረች፡፡ ምንም ሳይናገር ተከትሏት ሄደ፡፡ በሩ መግቢያ ላይ ሲደርስ፣ የሚያንገሸግሽ ሽታ ሸተተው፡፡

በልዩ አልጋ ላይ ሆኖ፣ ያለ የሌለው የልብስ ዓይነት ተጭኖበት፣ ገርጥቶ፣ ከስቶ፣ ዓይኖቹ ጐድጉደውና **ከሰውነት ጐዳና ወጥቶ** ሲመለከተው የዘነበ ጉልበት **ነፋስ እንደነካው ቄጤማ አረገደ፡፡** ከአልጋው ታች ተቀምጦም **እርር ብሎ አለቀሰ**፡፡ ከዚህ በኋላ ሁለቱ ወንድማማቾች መነጋገር ጀመሩ፡፡ ከጨረታው በኋላ፣ አሁን እስከተገናኙበት ጊዜ ድረስ የሆነውን ነገር ሁሉ ገላልጠው አወሩ፡፡ ዘነበ የቀለጠውን የወርቅ ሰዓት አወጣና ለወንድሙ አሳየው፡፡ ይህንን ያህል ጊዜ ተለያይተው ሲኖሩ፣ አንዳቸውም እንኳ የተደሰቱበት ጊዜ እንዳልነበረ ተገላለጡ፡፡

በልዩ አቅሙ ደክሞና ታሞ ሰለነበር፣ ዘነበ ከአልጋው አጠገብ ሳይለይ አስታመመው፡፡ አንድ ቀን ጧት በልዩ ከእንቅልፉ ሲነቃ፣ "ዛሬ ፍጹም ድኛለሁ፤ ከእንግዲህ ወንድሜ ሁልጊዜ ሳንለያይ እንደ ቀድሟችን አብረን እንኖራለን"  አለው፡፡ ሆኖም በዚያው ቀን **አረፈ**፡፡

ዘነበ የወንድሙን ባለቤትና ልጇን ወደ ቤቱ ይዞ በመሄድ፣ ተንከባክቦ አኖራቸው፡፡ እሱም በአካባቢው ሰው የተከበረ፣ **ምራቁን የዋጠ** ሰው ሆነ፡፡

ሽማግሌው የአስር አለቃ የትምህርት ቤት ዳይሬክተር የሆነውም፣ ለአካባቢው ህዝብ አንድ ውለታ ጥሎ ለማለፍ ስለፈለገ ነበር፡፡ በህጻናቱ ጠባይ ላይ እንዲቀረጽ የሚፈልገው ነገር ቢኖር፣ መጀመሪያውም መጨረሻውም ፍቅር ነበር፡፡ እናም፣ ሰው ማፍቀርን ለታዳጊዎች አስተማረ። ህጻናት፣ እየመጡ እንደጓደኞቻቸውና እንደአባታቸው ያጫውቱት፣ ችግራቸውንም ያወያዩት ነበር፡፡

*(በአለም የታወቁ አጫጭር ልቦለዶች፣ ትርጉም አምሳሉ አክሊሉ) ለትምህርቱ እንዲመች መጠነኛ ለውጥ ተደርጐበት የቀረበ።*

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ:- ንባብ

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በልቦለዱ የመጀመሪያ ክፍል መሰረት ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ፤ የመልሳችሁንም ምክንያት ከጽሁፉ ውስጥ በመፈለግ ግለጹ፡፡**

1. የውርስ ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ የሆነው፣ በሁለቱ ወንድማማቾች አለመስማማት ምክንያት ነበር፡፡
2. በወርቅ ሰዓቱ ጨረታ ብዙ ሰዎች ተሳትፈዋል፡፡
3. ለዘነበ የጨረታ አሸናፊነቱን ያበሰረው የጨረታው መሪ አልነበረም፡፡
4. የበልዩን ላም የገደላት ዘነበ ለመሆኑ ማረጋገጫ አለ፡፡
5. ጨረታውን ሁለት ሺ አንድ መቶ ብር ያደረሰው በልዩ ነበር፡፡
6. ዘነበ ማሸነፉ ሲነገረው የተጸጸተው፣ ለሰዓቱ የሚከፍለው ገንዘብ በመብዛቱ አልነበረም፡፡
7. ዘነበ ወንድሙ ቤት ድረስ በመሄድና "ሰዓቱን ከሆነ የፈለግህ መውሰድ ትችላለህ" በማለት ሲናገር ከንፈሩ የተንቀጠቀጠው ሰዓቱን ለመስጠት ስለጨነቀው ነበር፡፡
8. ዘነበ የተጐሳቆለው አልኮል በብዛት በመጠጣቱ ነበር፡፡
9. ወንድማማቾቹ ተጣልተው በነበሩባቸው ዓመታት ሁለቱም ደስተኞች አልነበሩም፡፡
10. የበልዩ ባለቤት ወንድማማቾቹ እንዲስማሙ ከፍተኛ ፍላጎት ነበራት፡፡

**፪. ልቦለዱን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. የውርስ ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?
2. ዘነበ ከሳቀ በኋላ፣ "ሶስት ሺ ብርና የኔንም ወንድምነት ከዚሁ ጋር" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ አብራሩ፡፡
3. ለበልዩ ድሃ መሆን "ምክንያቶች ናቸው" የምትሏቸውን ዘርዝሩ፡፡
4. የአካባቢው ባለስልጣኖች ዘነበን በቃጠሎው የጠረጠሩት ከምን ተነስተው ነው?

**፫. በልቦለዱ ባለታሪኮች ላይ የተከሰተው ችግር ከመነሻው እንዳይፈጠር፣ ችግሩ ከተፈጠረም በኋላ በቀላሉ እንዲፈታ ምን መደረግ ነበረበት ብላችሁ ታስባላችሁ? በቡድን በቡድን ሆናችሁ ተወያዩበትና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በየቡድን መሪያችሁ በክፍል አቅርቡ፡፡**

**፬. ዋና ዋና የሆኑትን የልቦለዱን ድርጊቶች በቅደም ተከተል አስቀምጡ፡፡ ይህንን ስታደርጉ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመወያየትና የሚከተለውን ምስል ደብተራችሁ ላይ በመጠቀም ይሁን፡፡**

ድርጊት 1. የአባታቸው ንብረት በጨረታ ተሽጦ ለመካፈል መስማማታቸው

ድርጊት 2.

ድርጊት 3.

ድርጊት 4.

ድርጊት 5.

. . .

## ክፍል ሁለት:- ማዳመጥ

፩ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ /በቡድን/ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ማጠቃለያ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ::

1. ፊት ለፊት ከሚደረግ የሀሳብ ልውውጥና በስልክ ከሚደረግ ንግግር በቀላሉ አዳምጦ ለመረዳት የሚያስችለው የትኛው ነው? ለምን?
2. አንድን ንግግር ወይም ውይይት አዳምጦ ለመረዳት የሚጠቅሙና የማይጠቅሙ ነጥቦችን በሚከተለው ስእላዊ መግለጫ አሳዩ::

**ለአዳምጦ መረዳት**

- **የሚጠቅሙ**
  - ንግግርን በሙሉ ስሜት ማዳመጥ
- **የማይጠቅሙ**
  - የሚያደምጡትን ሁሉ በማስታወሻ ለመያዝ መሞከር

፪ መምህራችሁ አንድ አጭር ጽሑፍ ያነቡላችኋል:: በጥሞና አዳምጡና በ«ሀ» ስር የተገለጹትን ገለጻዎች በ«ለ» ስር ከተዘረዘሩት ተገላጮች ጋር አዛምዱ::

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. በፊት ለፊትና በስተጓዳ አለ | ሀ. ሶፋ |
| 2. ድንክዬ ጠረጴዛ | ለ. ከዘራ |
| 3. ጠየም ያለ | ሐ. በር |
| 4. ወጪ ገቢውን የሚታዘብ አዛውንት የሚመስል | መ. ስልክ |
| 5. እንደ ጅብራ የተገተረ | ሠ. አልጋ |
| 6. የተሞሸረ | ረ. መስኮት |
| | ሰ. ቁምሳጥን |

## ክፍል ሦስት፡- ንግግር

፩. ከልቦለድ ወይም ከሌሎች የፈጠራ ሥራዎች ጋር በተያያዘ የተደረጉ ውይይቶችን፣ የተሰነዘሩ አስተያየቶችን ወዘተ. ከሬዲዮ ወይም ከቴሌቪዥን አዳምጣችሁ «ጠቃሚ ሐሳብ ነው» የምትሉትን በራሳችሁ አባባል ጽፋችሁ ለክፍል አቅርቡ፡፡

**ጽሑፋችሁ** - የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን የጠበቀ፣
- መንስኤና ውጤትን ያገናዘበ መሆኑን አረጋግጡ፡፡

**ምሳሌ**

- መጸነስ፣ ማርገዝ፣ መውለድ (የድርጊት ቅደም ተከተልን የጠበቀ፣)
- ባለፈው ዓመት፣ ባለፈው ወር፣ ባለፈው ሳምንት፣ ዛሬ፣ ነገ (የጊዜ ቅደም ተከተልን የጠበቀ)
- ታሞ ሞተ (መንስኤና ውጤትን ያገናዘበ)

፪. በአጭር ልቦለዱ እንደታየው በሁለቱ ዋና ገፀባህርያት መካከል ከፍተኛ ያለመግባባት ተፈጥሯል፡፡ ለዚህ ተጠያቂው ማነው? ዘነበ ወይስ በልዩ? እንደኛ ውን ደገፋችሁ ሌላውን በመቃወም ተከራከሩ፡፡ በክርክሩ ያልተሳተፋችሁ ደግሞ በተከራካሪዎች የሚሰነዘሩ ሃሳቦች የቱን ያህል ምክንያታዊ መሆን አለመሆናቸው ላይ አስተያየት በመስጠት ተሳተፉ፡፡

**በክርክር ጊዜ ለእነዚህ ነጥቦች ትኩረት ስጡ፣**

- በቂ ዝግጅት ማድረግ፣
- ከርእሱ ጋር የተየያዙ ሐሳቦችን ማቅረብ፣
- የሚቀርቡ ሐሳቦች በማስረጃ የተደገፉ መሆኑን ማረጋገጥ
- ተራን ጠብቆ መናገር፣
- የሌላውን ሰው ሐሳብ አለማንቋሸሽ፣
- ለተቃዋሚ ሐሳብ ተገቢ መልስ መስጠት፡፡

## ክፍል አራት:- ጽሕፈት

**፩. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሐረጋት፣ በልቦለዱ ውስጥ ያላቸውን ፍች የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ፡፡**

1. ያንርብኛል
2. ታዳሚዎች
3. አምቧረቀ
4. ጭርንቁስ
5. እርር ብሎ
6. አሞካሻቸው

### አያያዦችና የመሸጋገሪያ ቃላት

አያያዥ ወይም የመሸጋገሪያ ቃላት በብዙ ዓረፍተነገሮች የሚገለጹ ሐሳቦችን እርስ በርስ ተቀናጅተውና ተዋህደው እንዲቀርቡ የሚያግዙ ቃላት ናቸው፡፡ አያያዦች፣ ቃላት ብቻ ሳይሆኑ ቅጥያዎች ወይም ሐረጋት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አገልግሎታቸውም በዓረፍተነገር፣ በአንቀጽ ወይም በድርሰት ውስጥ እየተገኙ የሐሳቦችን ውህደትና ጥምረት መፍጠር ነው፡፡ ከአንዱ ሐሳብ ወደ ሌላው ሐሳብም ያሸጋግራሉ፡፡

አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት በርካታ ናቸው፡፡ የሚከተሉትን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ እና፣ ግን፣ ሆኖም፣ እርግጥ፣ እንጂ፣ ስለዚህ፣ ያህል፣ እንደገና፣ የሆነው ሆኖ…፡፡

**ምሳሌ** ሀ) አበበ ተማሪ እና ነጋዴ ነው፤ ይሁን እንጂ፣ በሁለቱም ውጤታማ አይደለም፡፡

- እና፡- ሐረግን ከሐረግ
- ይሁን እንጂ፡- ዐረፍተ ነገርን ከዐረፍተ ነገር አያይዘዋል፡፡

ለ) የተዘረዘሩ ዓረፍተ ነገሮች በአያያዥ ቃላት ተያይዘው ሲቀርቡ፡-

- የሰው ልጅ ለምግቡ ብዙ ገንዘብ ያስፈልገዋል፡፡
- የሰው ልጅ ለልብሱ ብዙ ገንዘብ ያስፈልገዋል፡፡
- የሰው ልጅ ለመጠለያው ብዙ ገንዘብ ያስፈልገዋል፡፡

- የሰው ልጅ ለምግቡ፣ ለልብሱ <u>እንዲሁም</u> ለመጠለያው ብዙ ገንዘብ ያስፈልገዋል፡፡

**፪. ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች መሠረት አያያዥ ቃላትን በመጠቀም የተዘረዘሩ ዓረፍተነገሮችን አያይዙ፣**

1. ሀ. መበለጸግ የሚቻለው ጠንክሮ በመሥራት መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል፡፡
   ለ. መበልጸግ የሚቻለው በወሬ አለመሆኑን ማወቅ ይኖርብናል፡፡
2. ሀ. እውቀት የሚዳብረው በሒደት ነው፡፡
   ለ. ክሂል የሚዳብረው በሒደት ነው፡፡

**፫. የሚከተሉትን አጣማሪዎች (አያያዦች) በመጠቀም የተጣመሩ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ**

1. ነገር ግን
2. ስለዚህ
3. በዚህም ሳቢያ

**፬. ወንድማማቾቹ ከሚለው ልቦለድ ውስጥ በአያያዥ ቃላት ወይም በሐረጋት የተጣመሩ አምስት ያህል ዓረፍተነገሮችን (ሐሳቦችን) አውጡ፡፡**

## አስተዋፅኦ

አንድን ድርሰት መጻፍ ከመጀመራችን በፊት ሶስት ዋና ዋና ተግባራትን እናከናውናለን፡፡ እነዚህም ተግባራት ርዕስ መምረጥ፣ የተመረጠውን ርእስ መወሰን ወይም ማጥበብና አስተዋፅኦ (ቢጋር) ማዘጋጀት ናቸው፡፡

አሰተዋፅኦ ዋናውን ጽሑፍ ለመጻፍ፣ መንገድ ቀያሽ ወይም ትልም ነው፡፡ በተለይም ለልቦለዶችና ለሌሎች ረጃጅም ጽሑፎች በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ነው፡፡

### የአስተዋፅኦ ጥቅሞች

- ዓላማን ግልፅ ለማድረግና ሐሳብን ከአላማ ጋር ለማዛመድ ያግዛል፡፡
- ድርሰቱ ከመጻፉ በፊት የሐሳቡን ቅንጅት ለማየትና ለማስተካከል ይጠቅማል፡፡
- መልዕክትን ለማስተላለፍ ራሱን የቻለ መሳሪያ በመሆን ያገለግላል፡፡
- ጽሑፍ በሚጻፍበት ጊዜ ከዋናው ሐሳብ ላለማፈንገጥ ይረዳል፡፡

- አስተዋፅኦ እንዴት ሊነደፍ /ሊፃፍ/ ይቻላል? የሚከተለውን ምሳሌ በጥሞና ተመልከቱ፡፡
- ጸሐፊው "መስከረም ሲጠባ " በሚል ርዕስ ድርሰት ለመጻፍ አሰበና በቅድሚያ የሚከተለውን አስተዋፅኦ ነደፈ፡፡

## መስከረም ሲጠባ

1. አካባቢው አስደሳች ይሆናል፡፡
   - 1.1 አበቦች ያብባሉ፡፡
   - 1.2 የደፈረሱት ጅረቶች ይጠራሉ፡፡
   - 1.3 በክረምት ተደብቀው የነበሩ አዕዋፍ ብቅብቅ ይላሉ፡፡
   - 1.4 ሰማዩ ይጠራል፣ ደመና ይወገዳል፡፡
2. ሰዎች መልካም ምኞታቸውን ይገልጻሉ፡፡
   - 2.1 በዘፈን፣
   - 2.2 ስጦታ በመለዋወጥ፣
   - 2.3 እርስ በርስ በመመራረቅና በመመሰጋገን፣
   - 2.4 በአምልኮ ቦታዎች በመገኘትና ፈጣሪያቸውን በማመስገን፡፡
3. ተለያይተው የከረሙ ሰዎች ይገናኛሉ፡፡
   - 3.1 ውሃ ሙላት የለያያቸው ይገናኛሉ፡፡
   - 3.2 በትምህርት ቤት መዘጋት የተለያዩ ተማሪዎች ይገናኛሉ፡፡
4. ሰዎች በአዲሱ ዓመት አዲስ እቅድ ተልመው ለመተግበር ይዘጋጃሉ፡፡
   - 4.1 ሠራተኛው የተሻለ ለመሥራት ያቅዳል፡፡
   - 4.2 ገበሬው የተሻለ ለማምረት ይዘጋጃል፡፡
   - 4.3 ነጋዴው የተሻለ ለማትረፍ ያልማል፡፡
   - 4.4 ተማሪው የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ቃል ይገባል፡፡

4.5 ወንደላጤው ትዳር ለመያዝ ይቆርጣል፡፡

4.6 ሱሰኛው ከሱሱ ለመላቀቅ ይምላል፡፡

*(ከቀድሞው የ9ኛ ክፍል አማርኛ የተማሪው መጽሐፍ የተወሰደ)*

**፫. መምህራችሁ ከሚሰጧችሁ ርዕሶች አንደኛውን መርጣችሁ፣ የሳይኛውን ምሳሌ መነሻ በማድረግ የራሳችሁን አሰተዋፅኦ ነድፋችሁ አቅርቡ፡፡**

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች

አንዳንድ የአማርኛ ቃላት እምሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችዎች አሏቸው፡፡ እማሬያዊ ፍች የሚባለው የቃሉ ቀጥተኛ ወይም መዝገበ ቃላዊ ፍች ነው፡፡ ፍካሬያዊ ፍች ደግሞ ቃሉ ከቀጥታ ፍችው ባሻገር የሚሰጠው ሌላ ትርጉም ነው፡፡

*ምሳሌ፡-* ቤት የሚለው ቃል በእማሬያዊ ፍችው ግድግዳና ጣሪያ ያለው የሰው ልጅ መኖሪያ ማለት ሲሆን፣ ፍካሬያዊ ፍችው ደግሞ የአንድ ሰው ጠቅላላ ኑሮ፣ ትዳር ወዘተ. ማለት ነው፡፡

**፬. የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች በሰንጠረዡ በቀረበው ምሳሌ መሠረት አስቀምጡ፡፡**

| | ቃል | እማሬያዊ ፍች | ፍካሬያዊ ፍች |
|---|---|---|---|
| | አባብ | በደረቱ የሚሳብ መርዘኛ ፍጡር፡፡ | መሠሪ፣ ተንኮለኛ |
| | ተልባ | ለምግብነት የሚውል የቅባት እህል፡፡ | በወዳጅነቱ የማይዘልቅ፣ ጊዜ አይቶ የሚከዳ |
| 1 | ንብ | | |
| 2 | ቋንጣ | | |
| 3 | ምስጥ | | |
| 4 | ርግብ | | |
| 5 | ድንጋይ | | |
| 6 | ጉቶ | | |
| 7 | አህያ | | |

፪. የሚከተሉትን ቃላት እማሪያዊና ፍካሬያዊ ፍችዎች፣ በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ፣ በዓረፍተነገሮች ውስጥ አስገብታችሁ አሳዩ፡፡

1. ድንቁርና
2. እሳት
3. ባህር
4. እስስት
5. እንቁ
6. ንብ

፫. እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍች ያላቸውን አምስት ቃላት ሰብስባችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በሚከተለው ሰንጠረዥ መሰረት አቅርቡና፣ በፍችዎቻቸው ላይ ተወያዩ፡፡

| | ቃሉ | የቃሉ | |
|---|---|---|---|
| | | እማሪያዊ ፍች | ፍካሪያዊ ፍች |
| ሀ | | | |
| ለ | | | |
| ሐ | | | |

## የቃል ክፍሎች

ከዚህ ቀጥሎ በየምድባቸው የተዘረዘሩና በስራቸው የተሰመረባቸው ቃላት ቀርበዋል፡፡ በጥሞና አስተውሉና ተመሳስሏቸውን ለመገንዘብ ሞክሩ፡፡

| | |
|---|---|
| 1.<br>- <u>ሰው</u><br>- <u>መሐመድ</u><br>- <u>መጸሐፍ</u><br>- <u>አዲስ አበባ</u><br>- <u>ዜና</u><br>- <u>ህልም</u><br>- <u>ጠረጴዛ</u><br>- <u>ሕዝብ</u><br>} መጠሪያዎች ናቸው ፤<u>ስም</u> ይባላሉ፡፡ | 2.<br>- <u>አስተዋይ</u> ሰው<br>- <u>አሮጌ</u> መጽሐፍ<br>- <u>ወቅታዊ</u> ዜና<br>- <u>መጥፎ</u> ህልም<br>- <u>ትልቅ</u> ጠረጴዛ<br>- <u>ታታሪ</u> ሕዝብ<br>} ሰው፣ መጽሐፍ፣ ዜና፣ ህልምና ጠረጴዛ ስሞች ናቸው፡፡ የተሰመረባቸው ቃላት ደግሞ የስሞቹ ገላጮች ናቸው፤ ፤<u>ቅፅል</u> ይባላሉ፡፡ |
| 3. - አበበ ምሳውን <u>በላ</u>፡፡<br>- ማሰብ የሚችል ሰው <u>ነው</u>፡፡<br>- እንዲያጠና <u>መከርኩት</u>፡፡<br>- ተግቶ <u>ሠራ</u>፣ ስለዚህም <u>ከበረ</u>፡፡ | } "በላ፣ ነው፣ መከርኩት ፣ ሠራ፣ ከበረ" የሚሉት ቃላት፣ የዓረፍተነገሮች ማሰሪያዎች ሲሆኑ ድርጊትንና መሆንን ያመለክታሉ፡፡ ስለዚህ ድርጊት አመልካች ቃላት ተብለው ይጠራሉ፡፡ <u>ግስ</u> ይባላሉ፡፡ |
| 4. - መኪናው <u>እዚህ</u> መጣ፡፡<br>- አትሌቱ <u>ዛሬ</u> አሸነፈ፡፡<br>- በቀስ <u>ክፉኛ</u> ታመመ፡፡ | } "መጣ፣ አሸነፈና ታመመ" ግሶች ናቸው፡፡ ከግሶቹ ቀድመው በመግባት ግሶችን የገለጹት "እዚህ፣ ዛሬ፣ ክፉኛ" የሚሉት ቃላት <u>ተውሳከግስ</u> ይባላሉ፡፡ |
| 5. - <u>ከ</u> ሰማይ<br>- <u>ስለ</u> ትምህርት<br>- <u>ከ</u> ሰው <u>ጋር</u><br>- <u>ለ</u> ህይወት | } የተሰመረባቸው ከስም ጋር የሚገቡ ምዕላዶች (ቅጥያዎች) ናቸው፡፡ <u>መስተዋድድ</u> ይባላሉ፡፡ "ስለ ፣ እንደ፣ እስከ፣ ወደ፣ ከ..." መስተዋድዶች ናቸው፡፡ |

**፬. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ከየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመደቡ (የቃል ክፍላቸውን) ግለጹ፡፡**

1. አየለ መኪና <u>ገዛ</u>፡፡
2. መንኮራኩሯ <u>ጨረቃ</u> ላይ አረፈች፡፡
3. <u>ሰነፍ</u> ሰው ሥራን አይወድም፡፡
4. ወደ ትምህርት ቤት <u>እየሮጠ</u> ሄደ፡፡
5. ዛሬ <u>ስለ</u> መሬት ተማርን፡፡

6. በመንኮራኩር <u>ወደ</u> ጠፈር ሄደ።
7. ሥራን ሠርቶ ማደር <u>ያስከብራል</u>።
8. መጽሐፉን "<u>በፍጥነት</u>" መለሰ።
9. ተሾመ <u>ጐበዝ</u> ተማሪ ነው።
10. <u>ፍቅር</u> ረቂቅ ነገር ነው።

**ፎ. በሚከተለው ሰንጠረዥ በተራ ቁጥር አንድ የቀረበውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ፣ ባዶ ቦታዎችን በተስማሚ ግሶች አሟሉ ። በዚህ ተግባር ግሶችን ከግስ እየመሰረታችሁ መሆኑን ልብ በሉ።**

| 1 | በተነ | ተበተነ | አስበተነ | አባተነ | በታተነ | ተበታተነ | አስበታተነ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | ገደለ | | | | | | |
| 3 | መታ | | | | | | |
| 4 | ገሰጠ | | | | | | |
| 5 | ጠረበ | | | | | | |
| 6 | ከፈተ | | | | | | |
| 7 | ነደሰ | | | | | | |
| 8 | ጠበሰ | | | | | | |
| 9 | ገመጠ | | | | | | |
| 10 | ወሰቀ | | | | | | |

## ሐረግ

የሚከተሉትን መዋቅሮች ተመልከቱ:-

- ፈጣኑ አበበ
- ከወንድሙ ጋር
- በጣም ጉበዝ
- የብርድ ልብስ
- ወደ ባህር ዳር
- ተግቶ አጠና

} እነዚህ በሙሉ ሐረጎች ናቸው፡፡

**ሐረግ:-** ቃላት እርስ በርስ በስርዓት በመቀናጀት የአንድ ዓረፍተነገር አካል ሆነው የሚፈጥሩት መዋቅር ነው፡፡ አንድ ሐረግ ምን ዓይነት ሐረግ እንደሆነ የሚወሰነውም በሐረጉ ውስጥ መሪ ሆኖ(ከሐረጉ በስተቀኝ) የቀረበው ቃል በሚመደብበት የቃል ክፍል ነው፡፡

**የሐረጉ መሪ ቃል:-** ስም ከሆነ፣ ሐረጉ ስማዊ ሐረግ፣
- ግስ ከሆነ፣ ሐረጉ ግሳዊ ሐረግ፣
- ቅፅል ከሆነ፣ ሐረጉ ቅፅላዊ ሐረግ ይባላል፡፡

***ምሳሌ :-***

- የብር ቀለበት → ስማዊ ሐረግ
- ጉበዝ ተማሪ → ስማዊ ሐረግ
- በጣም ብርቱ → ቅፅላዊ ሐረግ
- በድንገት መጣ → ግሣዊ ሐረግ

**፮. ከላይ በቀረበው መግለጫና ምሳሌ መሠረት በየዓረፍተነገሮቹ ውስጥ የተሰመረባቸው ሐረጎች፣ ከየትኛው የሐረግ ዓይነት እንደሚመደቡ (የሐረግ ዓይነታቸውን) ግለጹ፡፡**

1. ሰፊ ብርድ ልብስ አለው፡፡
2. ዘገየ በጣም ታታሪ ሰው ነው፡፡
3. ደራሲው ጥሩ ጽሑፍ ጻፈ፡፡
4. የወንድሜ ልጅ ከክፍሉ አንደኛ ወጣ፡፡
5. ያልሠራ ሰው ሁልጊዜ ይራባል፡፡
6. አበበ ክፉኛ ታሟል፡፡

**፯. በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ሐረጎችን እየመሰረታችሁ፣ ሐረጎቹ ምን ዓይነት ሐረግ እንደሆኑ ተወያዩ፡፡ ግልጽ ባልሆነላችሁ ላይ መምህራችሁን አነጋግሩ፡፡**

## ክፍል ስድስት፡- ስነጽሑፍ

### ልቦለድ

ልቦለድ ከደራሲው ምናባዊ ፈጠራ የሚመነጭ የሰውን ህይወት ልዩ ልዩ መልኮች በተመሳስሎ ለመቅረጽ የሚችል በቁሙ ግን እውነት ያልሆነ የኪነጥበብ ሥራ ነው፡፡ በቁሙ እውነት ያልሆነ ሲባልም፣ በታሪኩ የተገለጸው የገፀባህርያት ህይወት በእውኑ ዓለም በእርግጥ የተፈጸመ ወይም ታሪኩ በሚያቅፈው ዘመንና ቦታ እንዳለ የታየ አይደለም ለማለት ነው፡፡

የልቦለድ ዝርያ የሚባሉት ዋናዎቹ አጭር ልቦለድና ረጅም ልቦለድ ናቸው፡፡

## አጭር ልቦለድ

አጭር ልቦለድ፣ ሰብሰብ ያለ ወይም የታመቀ፣ ጥብቅ ትስስር ያለው፣ ፈጣንነት ጐልቶ የሚታይበትና የሁሉም ነገር መቋጫ የሆነ አንድ ብቸኛ የትኩረት ነጥብ ያለው የልቦለድ ዓይነት ነው፡፡

*(ዘሪሁን አስፋው፣ 1992፣153 እና 229)*

አጭር ልቦለድ ከረጅም ልቦለድ የሚለይበት አንዱ በመጠን ነው፡፡ ረጅም ልቦለድ መጠኑ ረጅም ሲሆን የአጭር ልቦለድ መጠን አጭር ነው፡፡ አጭር ነው ሲባልም ታሪኩ አጭር፣ ባለታሪኮቹ ጥቂት፣ ድርጊቱ የሚፈጸምበት ቦታና ጊዜም ጠባብና አጭር ጭብጡ ነጠላ ነው፡፡ በሁለቱም የልቦለድ ዝርያዎች ውስጥ በመገኘት፣ ልቦለዶቹን ልቦለድ እንዲሆኑ የሚያደርጓቸው ደግሞ የልቦለድ አላባውያን (የልቦለድ ፍሬ ነገሮች) በመባል ይታወቃሉ፡፡

## የልቦለድ አላባውያን

የልቦለድ አላባውያን ወይም ፍሬ ነገሮች በመባል የሚታወቁት ታሪክ፣ ገፀባህሪ፣ መቼት፣ ግጭት፣ ትልም፣ አንፃርና ጭብጥ እንዲሁም ቋንቋ ናቸው፡፡ እነዚህ አላባውያን ምንነታቸውን ለማጥናት ሲባል ተለያይተው ይቅረቡ እንጂ፣ በልቦለዱ ውስጥ በተናጠል የሚታዩ አይደሉም፡፡ ልቦለድ የሚኖረውም እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት አላባውያን (ፍሬ ነገሮች) ተጣምረው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡ ከእነዚህ መካከልም በዚህ የክፍል ደረጃ ታሪክና ገፀባህሪን እናያለን፡፡

**ታሪክ፡-** የልቦለዱ መሰረት ነው፡፡ ልቦለዱን ካነበብን በኋላ ላላነበበ ሰው ስንገልጽ፣ መጀመሪያ እንደዚህ ሆነ፣ ከዚያም እንደዚህ ሆነ፣ በመጨረሻም እንዲህ ሆነ ብለን የምንተርከው የልቦለድ ታሪክ ይባላል፡፡ ታሪክ፣ የጊዜ ቅደም ተከተልን መሠረት አድርገው በመቀናጀት የሚቀርቡትንና በገፀባህሪያቱ የሚፈጸሙ ድርጊቶችን፣ አነሳስ፣ አካሄድና የመጨረሻ ውጤት የሚይዝ የልቦለድ ህይወት ወይም የመጻፉ ሰበብና የህልውናው መሠረት ነው፡፡

**ገፀባህሪ፡-** በገሀዱ ዓለም ያሉ ሰዎችን ወክለው በታሪኩ ውስጥ የሚንቀሳቀሱና በደራሲው የተፈጠሩ የፈጠራ ሰዎች ናቸው፡፡ "በአንድ ልቦለድ ውስጥ ያለው ታሪክ የማን ነው?" ብለን ስንጠይቅ "የእነ እገሌ ታሪክ ነው" የሚል መልስ እናገኛለን፡፡ እነ እገሌ ተብለው የተጠቀሱት ደግሞ፣ በታሪኩ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ፣ ደራሲው የፈጠራቸው የፈጠራ ሰዎች ናቸው፡፡

**፩. በዚህ የትምህርት ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ "ወንድማማቾቹ" የሚል አጭር ልቦለድ አንብባችኋል፡፡ አሁንም እንደገና ተመልሳችሁ በማንበብ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በልቦለዱ መሠረት መልሱ፡፡**

1. ልቦለዱን አጭር ልቦለድ ያሰኙት ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
2. በልቦለዱ ውስጥ ያሉ ገፀባህርያትን ዘርዝሩ፡፡ ዋና ዋናዎቹ ገፀባህርያትስ ማን ማን ናቸው?

**፪. በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ በየተራ ታሪኩን በቃል ተርኩ፡፡ እርስ በርስም ስህተታችሁን ተራረሙ፡፡**

**፫. በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ ጨረታው እንደተከፈተ፣ የወርቅ ሰዓቱን አንደኛው ለሌላኛው ወንድሙ በፈቃደኝነት ቢሰጠው ኖሮ፣ ልቦለዱ ምን መልክ ይኖረዋል ብላችሁ ታስባላችሁ? በቡድን ተወያዩበትና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍል አቅርቡ፡፡**

**፬. አንድን አጭር ልቦለድ ወይም የአንድን ደራሲ የህይወት ታሪክ አንብባችሁ ማስታወሻ ከወሰዳችሁ በኋላ፣ በራሳችሁ አባባል ጽፋችሁ ለክፍል በማቅረብ ተወያዩበት፡፡ (ማስታወሻ አያያዝን በተመለከተ በሌሎች ምዕራፎች የተሰጠውን ማስገንዘቢያ አስተውሉ!)**

## ዘይቤዎችና ፈሊጣዊ ንግግሮች

ዘይቤዎችና ፈሊጣዊ ንግግሮች ሁለት የተለያዩ የሐሳብ ማስተላለፊያ መንገዶች ናቸው። ፈሊጥ፣ እያንዳንዱ ቃል፣ በተናጠል ከሚሰጠው የተለየ ፍች የሚያስገኝበት የቃላት ቅንጅት ነው። ለምሳሌ "ቀለም ያዘ፣ ሆዱ ቆረጠ፣ አደብ ገዛ" የመሳሰሉት ፈሊጦች ናቸው።

### ዘይቤ

ዘይቤ፣ የምናስተላልፈው መልዕክት ምስል በመፍጠር መልዕክቱ ጎልቶ፣ ቦግ ብሎ፣ አምሮና ደምቆ እንዲታይ ለማድረግ የምን ጠቀምበት አባባል ወይም የአነጋገር ስልት ነው። ዘይቤ በባህርይው ከተለመደው የቃላት ፍች የሚያፈነግጥ የአንዱን ባህርይ ከሌላው በማወዳደር ወይም ለሌላው በመስጠት እንዲሁም አንድን ነገር በሌላ በመወከል ወዘተ. የሚፈጠር የአገላለጽ ዓይነት ነው።

***ምሳሌ:-*** "ቤቱ ሰፊ ነው" ከሚለው ገለጻ ይልቅ፣ "ቤቱ ፈረስ ያስጋልባል" የሚለው ዘይቤያዊ አገላለጽ የቤቱን ስፋት በጥሩ ሁኔታ ይገልጸዋል።

### ልዩ ልዩ ዘይቤያዊ አነጋገሮች

- "እንደአንበሳ ጠንካራ ነው"
- "ልጅቷ ንብ ናት።"
- "ለሰው ሞት አነሰው" አለች ቀበሮ
- "ቤቱ ባህር ነው"
- "መቼስ ሲሮጥ ኤሊ ነው፣ የሚደርስበት የለም¡"
- "አባቴ እናቴ ነው"

**፫. ከዚህ ቀጥሎ ዘይቤዎችና ፈሊጣዊ ንግግሮች ተቀላቅለው ቀርበዋል። በየምድባቸው በመለየት በሰንጠረዥ አሳዩ።**

ሀ. ይልቃል እንደበግ የዋህ ነው።
ለ. አንቺ ምድር ፍረጅ!
ሐ. ልብ ገዛ።
መ. ይናገር ሐውልቱ!
ሠ. ራሷን ቻለች።
ረ. ልጁ አንበሳ ነው።
ሰ. በሬ ወለደ
ሸ. ሆድና ጀርባ

| ፈሊጥ | ዘይቤ |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |

**፯ በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ "ወንድማማቾቹ" ከሚለው ልቦለድ ውስጥ የሚገኙትን ፈሊጣዊ ንግግሮች በአንድ በኩል፣ ዘይቤያዊ ንግግሮችን ደግሞ በሌላ በኩል ለይታችሁ አውጡ። ከሌሎች ጥንዶች ሥራ ጋርም በማስተያየት ተወያዩ።**

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ በርካታ ርዕሰ ጉዳዮች ተነስተዋል፡፡ በመነሻው አንድ አጭር ልቦለድ ቀርቦ አንብባችኋል፡፡ በልቦለዱ የተለያዩ መልመጃዎችን ሠርታችኋል፡፡ የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች እንዲሁም የመሸጋገሪያና የአያያዥ ቃላት ምንነትም ተረድታችኋል፤ በተረዳችሁት መሠረት ልዩ ልዩ መልመጃዎችን አከናውናችኋል፡፡ የቃል ክፍሎችን አስመልክቶ ማብራሪያ ተሰጥቷችኋል፡፡ ከግሥ ሌሎች ግሦችን መመስረት እንደሚቻል በሠራችሁት መልመጃ አማካይነት አሳይታችኋል፡፡

በምዕራፉ ትምህርታችሁ አዳምጦ ፍሬ ሐሳብን መጻፍና ከተለያዩ መረጃዎች ማስታወሻ መያዝ ትኩረት የተሰጣቸው ነበሩ፡፡ እንዲሁም ስለ ሐረግ፣ ልቦለድ፣ አጭር ልቦለድ፣ የልቦለድ አላባውያንና አስተዋፅኦ ምንነታቸው ተገልፆላችሁ፣ ተያያዥ መልመጃዎችን ሠርታችኋል፡፡ በመጨረሻም፣ ዘይቤያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮች ምን እንደሆኑ በምሳሌ የተደገፈ ማብራሪያ የተሰጣችሁ ከመሆናችሁም በላይ፣ በማብራሪያዎቹ መነሻነት የቀረቡላችሁን መልመጃዎች አከናውናችኋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. “የመኝታ ክፍሉ በቂ <u>ብርሃን</u> ስላላገኘ ጨልሟል።” በሚለው ዓረፍተ ነገር፣ ብርሃን የሚለው ቃል አገልግሎት ላይ የዋለው በእማሬያዊ ወይስ በፍካሬያዊ ፍችው ነው? ለምን?
2. በሚከተሉት አያያዥ ቃላት ተጠቅማችሁ ዓረፍተነገር ሥሩና አገልግሎታቸውን በተግባር አሳዩ።
   1.1 ሳይሆን  2.2 ስለዚህ
3. የሚከተሉት ቃላት ከየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመደቡ ግለጹ።
   3.1 በፍጥነት  3.4 ወደ …
   3.2 ውቅያኖስ  3.5 ታታሪ
   3.3 አነበበ
4. የሚከተሉት ሐረጎች ከየትኛው የሐረግ አይነት ይመደባሉ?
   4.1 በትኩረት ተመለከተኝ
   4.2 ቀይ መስቀል ማህበር
   4.3 እጅግ ብርቱ
5. የልቦለድ አላባውያንን በዝርዝር ግለጹና ስለታሪክና ገፀባህርይ ማብራሪያ ስጡ።
6. አስተዋፅኦ ለአንድ ድርሰት ጸሐፊ የሚሰጠውን ጥቅም ግለጹ።
7. ሶስት ሶስት ፈሊጣዊና ዘይቤያዊ ንግግሮች ጻፉ።

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አራት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል:: በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመገንዘባችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✓)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ (?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተገነዘባችሁ የ(×) ምልክቶችን በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ::

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (✓) | (?) | (x) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የቀረበውን ልቦለድ አንብቤ መልእክቱን ተረድቻለሁ:: | | | |
| 2 | የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መለየት ችያለሁ:: | | | |
| 3 | የአያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት ምንነትና አገልግሎት ግልፅ ሆኖልኛል:: | | | |
| 4 | ቃላትን በየቃል ክፍሎቻቸው መመደብ ችያለሁ:: | | | |
| 5 | ቀርጽን እየለዋወጥኩ ከግስ ግስን መመስረት ችያለሁ:: | | | |
| 6 | ሐረጋትን ምን ምን አይነት ሐረግ እንደሆኑ ለይቼ አገልጻለሁ:: | | | |
| 7 | ከአዳመጥኩት መካከል ፍሬ ሀሳብን ለይቼ አጽፋለሁ:: | | | |
| 8 | የልቦለድ አላባውያንን ከልቦለድ ውስጥ ለይቼ ማመልከት ችያለሁ:: | | | |
| 9 | የድርሰት አስተዋፅኦ መንደፍ ጠቃሚ መሆኑን ተረድቻለሁ:: | | | |
| 10 | ፈሊጣዊና ዘይቤያዊ ንግግሮችን በንግግር ወይም በጽሑፍ ውስጥ የመጠቀም አስፈላጊነትን አገልፃለሁ:: | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠዥ የ(?) እና የ/x/ ምልክቶችን ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ::

# ምዕራፍ አምስት

## ሥነ-ግጥም

**የምዕራፉ ዓላማዎች:- ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- ዜማውን ጠብቃችሁ ግጥም ታነባላችሁ::
- የግጥም ሙያዊ ቃላትን ለይታችሁ ትጠቀማላችሁ::
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ትሰጣላችሁ::
- ጅምር ስንኞችን ታሟላላችሁ::
- የግጥምን መልዕክት ታብራራላችሁ::
- ከግጥም ዘይቤዎችን ለይታችሁ ታወጣላችሁ::
- የዓረፍተነገሮችን ባለቤት፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ለይታችሁ ትገልጻላችሁ::
- በቃል በማጥናት ንግግር ታደርጋላችሁ::
- ግጥምን እንደ ድምጹ ባህርይ (መርዘም ማጠር፣ መጥበቅ መላላት) ታነባላችሁ::
- ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን በማስታወሻ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ይዛችሁ ታቀርባላችሁ::

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. ከግጥምና ከዝርው (ስድ ጽሑፍ) አንባቢውን ወይም አድማጩን ይበልጥ የሚስበው የትኛው ነው? ለምን ይመስላችኋል?
፪. በግጥምና በዝርው ጽሑፍ መካከል ያሉ ልዩነቶች ምን ምን ናቸው?
፫. «ግጥም ሙዚቃዊ ቃና ወይም ዜማ አለው» ሲባል ምን ማለት ነው?
፬. ግጥም በሚነበብበት ጊዜ ዜማውን ለመጠበቅ ጥንቃቄ መደረግ አለበት ትላላችሁ? ለምን ?

### ዳግመኛ ቃልኪዳን

ባለ ብዙ ልሳን፣
እናት የብዙሀን፣
አንቺ ኢትዮጵያዬ፣
የነፃነት ቀንዲል ሰንደቅ ዓላማዬ፣
የቆራጥ ጀግኖች ምንጭ የአንድነት አርማዬ፡፡

በአጭር ታጥቄ፣
ወገቤን አጥብቄ፣
ክንዴን አፈርጥሜ፣
ስለተነሳሁኝ እልል በይ እማዬ፣
የመኖሬ ተስፋ አንቺ ህልውናዬ፣
የእድገት መሰላል፣
ብርኩማዬ'ኮ ነሽ የአፍታ ማረፊያዬ፣
መንደላቀቂያዬ ምቹ መከዳዬ፡፡

እና በመሆንሽ ቃሌን አድሻለሁ፣
ሁሉ ያንቺ ሆኖ፣
ሁሉን ማድረግ ችለሽ፣
መቼም ቢሆን ከየትም፣

ምኑንም ከማንም፣
ከመለመን ድነሽ፣
ምንጊዜም ከምንም፣
ራስሽን ችለሽ፣
ካላየሁ በስተቀር ክንዴን ሳላዝለው፣
ፊቴን ሳልመልሰው፣
ዳግመኛ ቃል ኪዳን ገብቸልሻለሁ፡፡

የደፈረሽ ጠላት፣
ረሃብና ጥማት፣
እጦትና እርዛት፣
ጠብና ጦርነት፣
ምንጬ ማይምነት፡፡

ያን ስምሽን ፍቆ ያሰኘሽ ኋላቀር፣
በፅኑ ተመትቶ እሱ ኋላ ሳይቀር፣
ፍፁም ተወግዶ በእርግጥ ተደምስሶ፣
የጎደፈው ስምሽ ዳግመኛ ታድሶ፣
የቀደመው ክብርሽ ሳላይ ተመልሶ፣
ቅስሜ አይሰበርም፣
ክንዴ አይታጠፍም፣
እያልኩኝ ደግሜ፣
እስከሚሳካልኝ ተፈ'ቶ እስካይ ህልሜ፣
ቃል 'ገባልሻለሁ ይኸው ፊትሽ ቆሜ፡፡

*(ዓለማየሁ ዘውዴ፣ ንስሀና ሌሎች ግጥሞች፣ 2003፣ ገጽ 116-117)*

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ:- ንባብ

**፩. ግጥሙን መሰረት በማድረግ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. እንደ ግጥሙ ከሆነ ባለታሪኩ ቃል ሲገባ የመጀመሪያ ጊዜው አይደለም፡፡
2. ባለ ብዙ ልሳን ሲል ንግግር ታበዣለሽ ማለቱ ነው፡፡
3. “ያን ስምሽን ፍቆ” የሚለው ኋላ ቀርነትን ነው፡፡
4. ባለ ታሪኩ ሀገሩን ለማልማት ሥራ ውስጥ ገብቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡
5. “መከዳዬ ነሽ” የሚለውን ሐረግ የተጠቀመው ሀገሩ መኖሪያው መሆኗን ለማመልከት ነው፡፡

**፪. በግጥሙ መሠረት ለተከታዮቹ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ኢትዮጵያን ለደፈራት ጠላት መነሻ ምክንያት የሆነው የትኛው ነው?
   - ሀ) ረሐብ
   - ለ) ጦርነት
   - ሐ) እርዛት
   - መ) አለመማር
2. ባለታሪኩ “ፊቴን ላልመልሰው” ሲል ምን ማለቱ ነው?
   - ሀ) ያለፈውን ላልመለከት
   - ለ) ላላፈገፍግ
   - ሐ) ከኋላዬ ያለውን ላልመለከት
   - መ) የልጅነት መልኬን ላልመለከት
3. “ያን ስምሽን ፍቆ” የሚለው የትኛውን ስሟን ነው?
   - ሀ) የጥንት ስልጣኔና ክብሯን
   - ለ) ለምለም ሀገር መሆኗን
   - ሐ) ኢትዮጵያ የሚለውን
   - መ) ኋላ ቀርነቷን
4. እንደ ተራኪው አገላለጽ ኢትዮጵያን የማይመለከተው የትኛው ነው?
   - ሀ) ተረጅነት
   - ለ) ቅኝ ተገዢነት
   - ሐ) የጥንት ገናናነት
   - መ) ኋላ ቀርነት

5. ገጣሚው ሃገሩን "ብርኩማዬ ነሽ" ሲል ምኑ መሆኗን ለማመልከት ነው?

ሀ) መኖሪያው　　ሐ) ትውልድ ቦታው

ለ) መመገቢያው　　መ) መመኪያው

6. "ክንዴን አፈርጥሜ" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ) ክንዴን አወፍሬ　　ሐ) ክንዴ አፈር ተጠምቶ

ለ) ክንዴን ተማምኜ　　መ) ክንዴን አጠንክሬ

**፫. ግጥሙን መሠረት አድርጋችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡**

1. ጸሐፊው ኢትዮጵያን «ባለብዙ ልሳን፣ እናት የብዙሐን" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ አብራሩ፡፡
2. ገጣሚው "እልል በይ እማዬ" የሚልበት ምክንያት ምንድን ነው?
3. "የጐደፈው ስምሽ ዳግመኛ ታድሶ" የሚለው ስንኝ ምንን ያመለክታል?
4. ገጣሚው ክንዱን የሚያዝለውና ከትግል ፊቱን የሚያዞረው መቼ ነው?
5. በገጣሚው እምነት ራስ መቻል በምን ይገለጻል?

## ክፍል ሁለት፡- ንግግር

1. "ዳግመኛ ቃል ኪዳን" በሚል ርዕስ በቀረበው የገጣሚው ሀሳብ ላይ ትስማማላችሁ? ወይስ የሌለ ችግር ነው የተነሳው? በጥንድ በጥንድ ተወያዩና አቋማችሁን ከምክንያቶቻችሁ ጋር አቅርቡ፡፡
2. የመረጣችሁትን አንድ ግጥም ወይም ዝርው (ስድ ጽሑፍ) አጥን ታችሁ በቃል (ጽሑፉን ሳትመለከቱ) ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡ መልዕ ክቱንም ተናገሩ፡፡

**ጽሑፍን አጥንቶ በቃል ለማቅረብ የማያግዙ ነጥቦች:-**

- በጽሑፍ የቀረበን ሐሳብ በቃል ለማጥናት በቅድሚያ ጽሑፉን ለመረዳት ማንበብ፣
- በጽሑፍ በተያዘው ሐሳብ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ነጥቦችና ዝርዝር ነጥቦችን መለየት፣
- ዋናና ዝርዝር ነጥቦች የተያያዙበትን ተጠየቅና ቅድም ተከተላቸውን መረዳት፣
- ወደ ትናንሽ ክፍሎች በመከፋፈል ለአጠናን ማመቻቸት፣
- የቀረበው ጽሑፍ ሀሳብ በቃል እስኪያዝ ድረስ ከፍላጎት ጋር ሀሳብን ሰብስቦ ደጋግሞ ማንበብ፣
- በቃል ለሚቀርብ ንግግር የሚጠና ሐሳብ የሚጠናው፣ ሐሳቡ ብቻ ሳይሆን በንግግር የሚቀርብበት ሁኔታ ጭምር እንደሆነ መረዳት፣

1. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን የቀረቡ ገለጻዎችን፣ ማብራሪያዎችን ወይም ጥያቄና መልሶችን ተከታትላችሁ ማስታወሻ በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

*(ማስታወሻ አያያዝ በተመለከተ በሌሎች ምዕራፎች የተነሱ ነጥቦችን አስታውሱ፡፡)*

## ክፍል ሶስት፡- ጽሕፈት

**፩. የሚከተለውን ግጥም ዜማውን ጠብቃችሁ በጥሞና አንብቡና «እሱ» የተባለው ሰው ምን ዓይነት ባህርይ እንዳለው፣ እንዲህ ዓይነት ባህርይ የቱን ያህል ጎጂ እንደሆነ ጽፋችሁ ለክፍል አቅርቡ፡፡ ባቀረባችሁት ሳይም ተወያዩ፡፡**

**እሱነው እሱ**

እሱነው እሱ
ዐይን ባይኖረው
ለምን ብርሃን ኖረ የሚለው፤
እግር ባይኖረው
ለምን መንገድ ኖረ የሚለው ፤
እሱነው እሱ
ከቀናቴ
ፀሐይቱን የሰረቀ
በመንገዴ
አሜከላ ያፀደቀ፡፡

*(ደበበ ሰይፉ፣ 1980፣55)*

## ክፍል አራት፡- ሰዋሰው

### የዓረፍተነገር ክፍሎች

በአንድ የተሟላ ዓረፍተነገር ውስጥ የሚገኙት ዋና ዋና ክፍሎች ባለቤት ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ናቸው፡፡

**ባለቤት፡-** በአንድ ዓረፍተነገር ውስጥ ድርጊት ፈጻሚው ነው፡፡

**ተሳቢ፡-** በዓረፍተነገሩ የተፈጸመው ድርጊት የተፈጸመበት ነው፡፡

**ማሰሪያ አንቀጽ፡-** የዓረፍተነገሩ መቋጫ (ማሰሪያ) ነው፡፡

- ባለቤትን ለማግኘት ማሰሪያ አንቀጹን ይዘን፣ ማን አደረገ? ማን ምን ሆነ ማን ምንድን ነው? ለእንስሳትና ለነገሮች ደግሞ "ማን?" የሚለውን «ምን» በሚል በመተካት መጠየቅ ይኖርብናል፡፡
- ተሳቢን ለማግኘት "ማንን" ወይም "ምንን" በማለት መጠየቅ ይጠበቅብናል፡፡
- ዓረፍተነገሩ የተጠቃለለበት ቃል የዓረፍተነገሩ ማሰሪያ አንቀፅ ነው፡፡
- **ምሳሌ፡-** ገበሬው መሬቱን አረሰው፡፡

| ባለቤት | ተሳቢ | ማሰሪያ አንቀጽ |
|---|---|---|
| ገበሬው | መሬቱን | አረሰው |

**፩. ከላይ በተገለጸው ምሳሌ መሠረት፣ በሚከተሉት ዐረፍተነገሮች ውሰጥ ያሉትን ባለቤት፣ ተሳቢና ማሠሪያ አንቀፃች አውጡና በሰንጠረዥ አሳዩ፡፡**

1. ግንበኛው ድንጋዩን ፈለጠ፡፡
2. ጎርፉ ዛፉን ገነደሰው፡፡
3. መቅደስ በሩን ቀጠቀጠችው፡፡
4. መምህራኑ ቤት ገዙ፡፡
5. ዶሮዎቹ እንቁላል ጣሉ፡፡
6. አክስቴ የጠላውን አተላ ደፋችው፡፡

**፪. የየራሳችሁን ዓረፍተነገሮች ጻፉና ከጓደኞቻችሁ ጋር በመቀያየር የየዐረፍተ ነገሮቹን ባለቤት፣ ተሳቢና ማሠሪያ አንቀፅ አውጡ፤ በመልሶቻችሁም ላይ ተነጋገሩ።**

## ክፍል አምስት፡- ስነ-ጽሑፍ

### የግጥም ሙያዊ ቃላት

ስለ ግጥም ሲነሳ ስፊ አገልግሎት የሚሰጡ ሙያዊ ቃላትና ሐረጋት አሉ። ከነዚህ መካከል የሚከተሉትን እናገኛለን።

1. **ስንኝ፡-** ሐረጐችን ያካተተ የግጥሙ አንድ መስመር ነው።
2. **ሐረግ፡-** በአንድ ትንፋሽ የሚነበብ የስንኝ ክፍል ነው። ሐረጉ በስንኙ መጀመሪያ ላይ ካለ መነሻ ሐረግ፣ በስንኙ መጨረሻ ላይ ከተገኘ መድረሻ ሐረግ ይባላል።
3. **ቤት፡-** በስንኝ መጨረሻ ላይ ያለው ቃል የመጨረሻ ሆሄ ወይም ድምጽ ነው።
4. **ቤት መታ፡-** አንድ ስንኝ በምጣኔ ተሳክቶ ሲጨርስ፣ ቤት መታ ይባላል።
5. **ቤት ደፋ፡-** ግጥሙ ባለ ሁለት ስንኝ ከሆነ፣ የሁለተኛው ስንኝ ቤት ከመጀመሪያው ጋር ተጣጥሞ (ተመሳስሎ) ሲጨርስ ቤት ደፋ ይባላል።
6. **ቤት መምቻ ቃል፡-** በተመሳሳይ ሆሄ /ድምጽ/ በሚጨርሱ ስንኞች የተመሰረተ ግጥም፣ የመጀመሪያው ስንኝ መጨረሻ ቃል ነው።
7. **ቤት መድፊያ ቃል፡-** በተመሳሳይ ሆሄ/ድምጽ/ በሚጨርሱ ስንኞች የተመሰረተ ግጥም የመጨረሻው ስንኝ መጨረሻ ቃል ነው።
8. **አንጓ /አርኬ/፡-** በአንድ አይነት ቤት የተደረደሩ ስንኞች ስብስብ ሲሆን፣ በአራት ነጥብ ይዘጋል።

**፩. የሚከተለውን ግጥም ዜማውን ጠብቃችሁ አንብቡና ከስሩ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ።**

ድምር ቅራቅንቦ፣ ስንክሳር ኮረጆ፣
ትንሽ ሆና ትልቅ፣ ጓዘ ብዙ ጎጆ።

ምላጭ፣ መርፌ፣ ስኳር ፣ እጣን፣ ከርቤ፣ ሰንደል፣
ሰዓት ፣ ሬዲዮ፣ ሁሉንም በጥቅል፣
አምቃ የያዘች፣ትልቅ ትንሽ ሳትል።
ድንቡሎ ላመጣ፣ “ኖትም” ለመዘዘ፣
በወር ላይ ክፍያ፣ በዱቤ ላዘዘ።
ከድሃውም ድሃ፣ “ከቱጃሩም ቱጃር፣”
እንደ ሁሉ ሆና፣ ሁሉን የምትኖር።
በየጉራንጉሩ፣ በየበራፉ ላይ፣
ይቺ ትንሿ ቤት፣ ያፍንጫ ስር ተባይ።

*(አሰራት ዳምጠው፣ 1977፣ ፅጌረዳ ብዕር)*

1. የመጀመሪያው ስንኝ ስንት ሐረጎች አሉት?
2. የሁለተኛው ስንኝ መነሻ ሐረግ ምን የሚለው ነው?
3. የሶስተኛው ስንኝ መድረሻ ሐረግ የትኛው ነው?
4. በመጨረሻዎቹ ሁለት ስንኞች የተመሰረተው ግጥም ቤት ምንድነው?
5. ግጥሙ በጠቅላላ ስንት ስንኞች አሉት?
6. የግጥሙ ሐረጎች ብዛት ስንት ነው?
7. በመጀመሪያዎቹ ሁለት ስንኞች የተገነባው ግጥም፣ “ቤት መታ” የምንለው የት ላይ ነው?
8. በሶስተኛ በአራተኛና በአምስተኛ ስንኞች የተመሠረተው ግጥም “ቤት ደፋ” የምንለው የት ላይ ነው?
9. የግጥሙ ሁለተኛ አንጓ ስንት ስንኞች አሉት?
10. የግጥሙ ርዕስ ምን ሊሆን ይችላል?

**፱. የሚከተሉት ቃላት ከዚህ በላይ ከቀረበው ግጥም የወጡ ናቸው፤ ተመሳሳይ ፍቻቸውን ፈልጉ።**

| | | |
|---|---|---|
| 1. ቅራቅንቦ | 3. ስንክሳር | 5. ኖት |
| 2. ኮረጆ | 4. ድንቡሎ | 6. ቱጃር |

**፫. በግጥሙ መሠረት ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ተቃራኒ ፍች ፈልጉላቸው፡፡**

1. ጓዘ ብዙ
2. በጥቅል
3. አምቃ
4. ዱቤ
5. አፍንጫ ስር
6. ጉራንጉር

## የግጥምና የዝርው (ስድ ጽሑፍ) ልዩነት

### ግጥም

- ስንኞቹ በአንድ በአንድ መስመር እየተጻፉ ወደታች ይደረደሩበታል፡፡
- ያልተሰለቹና ሰፊ መልእክትን ማስተላለፍ የሚችሉ ቃላት ተመርጠው ጥቅም ላይ ይውሉበታል እንጂ፣ እንደተገኙ አይደረደሩበትም፤ "ቁጥብ ነው" የሚያሰኘውም አንዱ ምክንያት ይሄው ነው፡፡
- ቃላቱ ጥቂት ሆነው ሰፊ ሀሳቦችን የሚያስተላልፉ፣ እምቅነትና ክረት ያላቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም አንብቦ ለመረዳት ከባድ ነው፡፡
- በሚነበብበት ጊዜ ምቱ የተስተካከለ በመሆኑ ዜማዊ ነው፡፡
- ምት አለው፤ ማለትም አንዱን ሐረግ ለማንበብ የሚወስደው ጊዜ ቀጣዩን ሐረግ ለማንበብ ከሚወስደው ጊዜ ጋር ተመጣጣኝ ነው፡፡

### ዝርው (ስድ ጽሑፍ)

- ዓረፍተነገሮች በመስመሮቹ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ገጽ ተከታትለው ይጻፋሉ፡፡
- ቃላትን ስመምረጥ ጭንቀት አይታይበትም፤ ቃላት እንደተገኙ ተዝናንቶ ይጠቀማል፡፡
- አንብቦ ለመረዳት ከግጥም ይልቅ ቀላል ነው፡፡
- የግጥምን ያህል ዜማዊ አይደለም፡፡
- ምት የለውም፡፡

**፬. በቡድን በቡድን ተከፋፍላችሁ፣ አንድ ግጥምና አንድ ዝርው ጽሑፍ በመያዝ ከላይ የተገለፁትን የግጥምና የዝርው ልዩነቶች በተግባር አገናዝቡ፡፡**

## የዘይቤ ዓይነቶች

የዘይቤ ዓይነቶች ብዙ ናቸው፡፡ በስፋት የተለመዱትን ብንጠቅስ፣ አነፃፃሪ ዘይቤ፣ ለዋጭ ዘይቤ፣ ሰውኛ ዘይቤ፣ እንቶኔ ዘይቤ፣ ተምሳሌት ዘይቤ፣ አያዎ ዘይቤ ወዘተ የሚባሉ አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ሶስቱን እንመለከታለን፡፡

1. **አነፃፃሪ ዘይቤ፡-** ሁለት በአፈጣጠራቸው (ዝርያቸው) የማይመሳሰሉና የተለያዩ ነገሮችን በመውሰድ በማንፀሪያ ቃላት (እንደ፣ ያህል፣ ይመስላል ወዘተ) እየተጠቀመ የሚያነፃፅርና የሚያወዳድር የዘይቤ አይነት ነው፡፡

   ***ምሳሌ፦*** - ብሩክ እንደ እርግብ የዋህ ነው፡፡

   - ሰውየው ጅብ ይመስል በልቶ አይጠግብም፡፡

2. **ለዋጭ ዘይቤ፡-** ይህ ዘይቤ ሁለት የተለያዩ ነገሮችን ወስዶ የአንዱን ባህርይ ለሌላው በመስጠት የሚያቀርብ የዘይቤ አይነት ነው፡፡

   ***ምሳሌ፡-*** አበበ አንበሳ ነው፡፡

   - ሰውነቱ እሳት ሆነ፡፡

3. **ሰውኛ ዘይቤ፡-** የሰውን ልዩ ልዩ ባህርያት፣ ድርጊትና ችሎታ ሰው ላልሆኑ ነገሮች በመስጠት የሚፈጠር ዘይቤ ነው፡፡

   ***ምሳሌ፡-*** ቀኑ እያለቀሰ ነው፡፡

   - "ለሰው ሞት አነሰው" አለች ቀበሮ!

**፭. የሚከተሉት ግጥሞች የተጠቀሙባቸውን የዘይቤ አይነቶች አነፃፃሪ፣ ለዋጭ ወይም ሰውኛ በማለት መልሱ፡፡**

እንደ እንጉዳይ ፍላ፣ እንዳደይ አበባ፣
እንደ ችበሃ ለምልም፣ እንደዘመን ጥባ፡፡

______________________________

1. ለኔ አንበሳዬ ነህ፣ ከሁሉም የበላይ፣
   አንተኑ እሻለሁ፣ ከቶ ሌላም አላይ፡፡

______________________________

2. በዱልዱም ቢቀርፁት፣ ብዕር አለቀሰ፣
 ጥቁር ቀለም ሳይሆን፣ ደም እያፈሰሰ፡፡

______________________________

3. እኔማ ፈጀሁት፣ ብርቱ ጫማ ሆኜ፣
 ሲረማመዱብኝ፣ ዘለዓለም ባክኜ፡፡

______________________________

4. በኔ ይወደዳል፣ ጥርስ ከንፈርሽ፣
 አንገትሽ ብርሌ፣ አንቺ ልጅ ማርነሽ፡፡

______________________________

5. ነፋሱም ይናገር፣ አይኔን ያበሳጨው፣
 ካፋፉ ላይ ቆሜ፣ ቀልቤን ያታለለው፤
 ምሽቱ ይናገር፣ አይኔን የጋረደው፣
 የቅርቤን የሩቁ፣ አድርጎ ያሳየው፤
 ውርጩም ይተርከው፣ አንጀቴን የበላው፣
 አገኝህ ይመስል፣ ልቤን ያማለለው፡፡

______________________________

## ጅምር ስንኞችን ማሟላት

ጅምር ስንኞችን የማሟላት ሥራ ሲሠራ የሚተኮርባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ ከእነዚህም አንዱ የሀሳብ ቁርኝት ነው፡፡ ለምሳሌ ግጥሙ ባለሁለት ስንኝ ግጥም ቢሆን ሁለቱ ስንኞች የሀሳብ ተያያዥነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ አንደኛው ስንኝ ስለ አንድ ጉዳይ፣ ሌላኛው ስንኝ ደግሞ ስለ ሌላ ጉዳይ ሊያተኩሩ አይገባም፡፡

ምጣኔውም፣ ሌላው ሊተኮርበት የሚገባ ነጥብ ነው፡፡ የመጀመሪያው ስንኝ የሐረጉና የስንኙ መጠን፣ ከሁለተኛው ስንኝ የሐረግና የስንኝ መጠን ጋር የተመጣጠነ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሌላው የቤት ጉዳይ ነው፡፡ የመጀመሪያው ስንኝና የሁለተኛው ስንኝ የመጨረሻ ሆሄ ወይም ድምጽ ተመሳሳይነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

**፯ የሚከተሉትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ ጅምር ስንኞችን በማሟላት ግጥሙን አስተካክሉ፤ ከዚያም የግጥሙን መልዕክት አብረሩ::**

***ምሳሌ*** ሀ. ተወደው የኖሩ ተወደው ያለፉ፣
ከህዝቡ ህሊና____________::
ማሟያ፡- ምንጊዜም አይጠፉ

***መልዕክት፡-*** በመልካም ሥራቸው የተወደዱ ሰዎች ሞተውም ቢሆን አይረሱም::

ለ. አንቺ ልጅ ሞኝ ነሽ፣ ሞኝነሽ ይላሉ፣
እውነት ይመስልሻል_____________::
ማሟያ፡- የነገሩሽ ሁሉ::

***መልዕክት፡-*** አንቺ ልጅ ሞኝ በመሆንሽ ሰዎች የሚሉሽን ሁሉ እውነት የሆነ አድርገሽ ትወስጃለሽ ::

1. ሁሉም በሒደት ላይ መለወጡ አይቀርም፣
   የኖረ ይሞታል፣ ይጨልማል ________::
2. አኩርፌሽ ስቀመጥ ያው እንደ ባላንጣ፣
   ይኸው በጋው አልፎ ሌላው _______::
3. ሰውን የሚያስርበው ምንድነው? ቢሉት፣
   በማለት መለሰ _________________::
4. ተረከብ ሞፈሩን፣ ተሸከም ቀንበሩን፣
   እረስና አብላ መላ________________::
5. ጥላ ከለላዬ ብዬ ስመካብህ፣
   _______________________________::

## ማጠቃለያ

ምዕራፍ አምስት ያተኮረው ግጥም ሳይ ነው፡፡ የግጥም ምንባብ አንብባችሁና፤ የተወሰኑ የግጥም ሙያዊ ቃላትም ምንነታቸው በምሳሌ ተደግፈው ቀርበውላችሁ ስለ ግጥም ከዚህ በፊት በነበራችሁ እውቀት፣ ተጨማሪ ግንዛቤ አግኝታችኋል፡፡ ጅምር ስንኞችን የማሟያ ዘዴዎች፣ የባለቤት፣ የተሳቢና የማሠሪያ አንቀጽ ምንነት፣ የዘይቤ አይነቶች (አነፃፃሪ፣ ተለዋጭና ሰውኛ)፣ እንዲሁም የግጥምና የዝርው ልዩነት ማብራሪያዎች ተሰጥተዋችሁ፣ ስለ እነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች የነበራችሁን ግንዛቤ አስፍታችኋል፡፡ ከእነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ያላቸው መልመጃዎችም ቀርበውላችሁ ሰርታችኋል፡፡

ለተለያዩ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ሰጥታችኋል፤ የድምጽ መጥበቅና መላላት ስለሚያሳዩ ቃላት፣ ከተለያዩ ምንጮች ማስታወሻ ስለ ማቅረብም፣ እንዲሁ በተሰጧችሁ ማብራሪያዎችና መልመጃዎች አማካይነት ግንዛቤያችሁን አስፍታችኋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ከግጥም ሙያዊ ቃላት መካከል ሐረግ፣ ስንኝ፣ ቤት፣ አንጓ፣ ምን እንደሆኑ ግለጹ፡፡
2. በዓረፍተነገር ውስጥ ባለቤትና ተሳቢ የሚሆኑት ስሞች፣ ማሠሪያ አንቀጽ የሚሆኑት ደግሞ ግሦች መሆናቸውን አጢናችኋል? እስኪ ዓረፍተነገር ሥሩና ከላይ የተገለፀውን ሀሳብ አገናዝቡ፡፡
3. "ግጥምን ይበልጥ ውብና መልዕክቱንም ብሩህ የሚያደርጉት፣ የሚመረጡ ቃላትና የሚጠቀምባቸው ዘይቤዎች ናቸው፡፡" የሚለውን አባባል ትክክለኛነት የሚያሳይ ግጥም ምረጡና አብራሩ፡፡
4. ንግግር የሚያዳምጥ ሰው፣ ከንግግር ማስታወሻ ለመያዝ ቢፈልግ፣ ምን ማድረግ አለበት?
5. አንድ ሰው የቃል ጥናት ንግግር ለማዘጋጀት የሚጠቅሙት ምን ምን ተግባራት ናቸው?

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አምስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘባችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል:: በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመገንዘባችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√) ፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?) ሙሉ ለሙሉ ካልተገነዘባችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሚሉ::

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (x) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ግጥምን ዜማውን ጠብቄ ማንበብ ችያለሁ:: | | | |
| 2 | የግጥም ሙያዊ ቃላትን በተግባር ለይቼ መጠቀም ችያለሁ:: | | | |
| 3 | ጅምር ስንኞችን በተገቢ ሐረጋት አሟልቼ መልዕክቱን አገልፃለሁ:: | | | |
| 4 | አጭር ግጥምን ወይም ዝርው ፅሑፍን በቃል አጥንቼ የማቅረብ አቅም አግኝቻለሁ:: | | | |
| 5 | በግጥም ውስጥ ያሉ ዘይቤዎችን ለይቼ ማውጣት ችያለሁ:: | | | |
| 6 | ከዓረፍተነገር ባለቤት ተሳቢና ማሠሪያ አንቀፅ ለይቼ ማውጣት ችያለሁ:: | | | |
| 7 | ከተለያዩ ምንጮች መረጃዎችን በማስታወሻ እንዴት መያዝ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ:: | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(x) ምልክቶችን ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ::

# ምዕራፍ ስድስት

## ተውኔት

**የምዕራፉ ዓላማዎች:- ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- የተውኔትን ምንነት ትናገራላችሁ።
- የተውኔት አላባውያንን ትዘረዝራላችሁ።
- የአንድን ተውኔት ታሪክ በድርጊትና በጊዜ ቅደም ተከተል ታቀርባላችሁ።
- ውይይት ታካሄዳላችሁ።
- በምትጽፉት ጽሑፍ ውስጥ መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትን ትጠቀማላችሁ።
- ከቃላት ውስጥ የመነሻና የመድረሻ ቅጥያዎችን ትለያላችሁ።
- ቃላትን እንደ ባለቤት፣ ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ተጠቅማችሁ ዓረፍተነገር ትመሰርታላችሁ።
- በቃላት ላይ የተቀጠሉ የእርባታ ቅጥያዎችን ታመለክታላችሁ።
- ማመልከቻ ትጽፋላችሁ።
- ለዋጭ፣አነፃፃሪና ሰውኛ ዘይቤዎችን ለይታችሁ ታሳያላችሁ።

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. ተውኔት ምንድነው?
፪. ካነበባችኋቸው የልቦለድ መጻሕፍት ውስጥ የምታስታውሷቸውን ገጸ-ባህርያት ጥቀሱ፡፡
፫. በሬዲዮ እና በቴሌቪዥን እንዲሁም በመድረክ ቀርበው ከተከታተላችኋቸው ተውኔቶች ውስጥ የምታስታውሷቸዉን ገጸ-ባህሪያት ዘርዝሩና ገፀባህ ርያቱን ለምን እንደምታስታውሷቸው ግለጹ፡፡
፬. ገጸ-ባህርያት ማለት ምን ማለት ነው? መቼትስ?
፭. ስለተውኔታዊ ቃላት የምታውቁትን ጥቀሱ፡፡

## የተውኔት አላባውያን

የተውኔት አላባውያን ገጸ-ባህርያት፣ ታሪክ፣ መቼት፣ ትልም (ምክንያትና ውጤት) እና ግጭት ናቸው፡፡ እነዚህ የተውኔት አላባውያን በአንድ ተውኔት ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ሊገለጹ ይችላሉ፡፡ በሚከተለው ተውኔት ውስጥ የተውኔት አላባውያን የሚባሉት በክዋኔ ይገለጻሉ፡፡

### ትእይንት አንድ

(በመጀመሪያው ትእይንት መድረኩ ሲከፈት፣ ከብቶች ሳር እየጋጡ የሚስተዋሉበት መስክ ይታያል፡፡ ከብቶች ሳር እየጋጡ በሚታዩበት ፊት ለፊት ባለው አንድ ዛፍ ስር ሁለት ሰዎች ተቀምጠዋል፡፡ ከሁለቱ ሰዎች አንደኛው በራሳቸው ላይ ነጭ ሻሽ ጠምጥመዋል፡፡ ጋቢ ለብሰው በሚታዩት ሁለተኛው ሰው ትከሻ ላይ በአንደኛው ጫፍ መሬት የነካ ብትር ተጋድሟል)፡፡

**ቄስ ታምሩ፡-** «ብርቱ ጉዳይ አለኝ እፈልግዎታለሁ» ካሉኝ ሰነበቱ አይደል አያ ቦጋለ?

**ሕያ ቦጋስ:-** «አዎ! ሰንበት ብሏል፤ እስካሁን ከቆየሁት አይበልጥም፤ እታገሳቸዋለሁ፤ ፋታ የማይሰጥ ጉዳይ አጋጥሟቸው ይሆናል» ብዬ ነው።

**ቄስ ታምሩ:-** አይ የኔ ነገር! አንዳንዴ እዘነጋለሁ፤ አንዳንዴ ደግሞ እርስዎም እንደሚያውቁት የንሰሐ ልጆቼ ከዚያም ከዚህም ይጠሩኛል። አሁን ዛሬ ትዝ ሲለኝ ጊዜ «አያ ቦጋስን ከብቶች የሚያግዱበት ቦታ አላጣቸውም» ብዬ ነው ደንግጬ የመጣሁት፤ ለመሆኑ የፈለጉኝ በደህና ኖሯል?

**ሕያ ቦጋስ:-** ደህናስ ደህና ነኝ፤ እንዲያው ብቸኝነት ሲከብደኝ ጊዜ "ለምን አንድ ውሃ አጣጬን አልፈልግም" የሚል ሀሳብ ከታየኝ ሰንበት ብሏል።

**ቄስ ታምሩ:-** የማንን ልጅ አሰቡ? የትኛዋን ልጃገረድ አዩ?

**ሕያ ቦጋስ:-** ኧረ እንዲያም አይደል፤ በዚህ እድሜዬ የማንንም ልጅ ለጋብቻ መጠየቅ አልሻም።

**ቄስ ታምሩ:-** ታዲያ በየትኛዋ ፊት ላይ ነው ቀልብዎ ያረፈዉ?

**ሕያ ቦጋስ:-** ኧረ ሩቅም አይደል የሄድኩት! ከዚሁ ከጎረቤቴ አንዲት ሴት አይቻለሁ።

**ቄስ ታምሩ:-** ማንን ነው ያዩት? እመት ውድነሽን ወይስ ሌላ ሴት?

**ሕያ ቦጋስ:-** (እያቅማሙ…) እንዴት ባንዴ ደረሱባት! እንዴት ባንዴ አገኙኝ!

**ቄስ ታምሩ:-** ነገሩ ጥሩ ነው። እመት ውድነሽ ባሎቿ በተራ ሞተውባት የለ!…

**ሕያ ቦጋስ:-** አዎ! እሱንማ አውቃለሁ… ሀሳቤን በውስጤ ደብቄ ከርሜያለሁ። አሁን አሁን ብቻዬን ከምሆን ሰው ይሻለኛል፤ ከወዲህም ለቁንጅናዋ ምንም አይወጣላት! ሞት እንግዲህ ለሁሉም አይቀር፤ እጣ ፈንታችን አይደል! የአንድዬ ፈቃድም ከሆነ ዘር ማትረፍም ደግ ነው።

**ቄስ ታምሩ:-** ነገሩማ ደግ ነው፤ ነገር ግን እመት ውድነሽ «ከእንግዲህ ትዳር አላስብም፤ የተቀረውን እድሜዬን ብቻዬን እገፋለሁ» ትላለች አሉ።

**አያ ቦጋለ:-** እስዎን መፈለጌ ለዚህ አይደል! በአንድ በኩል የንስሐ ልጃዎ ናት፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሀይማኖት አባት እንደመሆንዎ በአካባቢያችን ከእርሶ ቃል ማንም አይወጣም ብዬ ነው። እና ሀሳቤን ለእርስዎ ከነገርኩ ጭንቀቴ የቀለለኝ መሰለኝ። ውለው ሳያድሩ ይጠይቁልኝ፤ ይጠይቁልኝ ብቻም አይደለም፤ እሺ ያሰኙልኝ።

**ቄስ ታምሩ:-** እስቲ እሱ ይጨመርበት! እኔማ እንደዚህ ላለ ጉዳይ ቀጠሮም አልሰጥ፤ ደግሞ እሺ ላሰኛት እሞክራለሁ፤ ከቃሌ የምትወጣ አትመስለኝም።

**አያ ቦጋለ:-** ባዶ አፍዎን እንዲያው ዝም ብዬ... በደረቁ...

**ቄስ ታምሩ:-** እድሜ ይስጠን፤ ለወደፊት እንደርስበታለን፤ ደህና ይዋሉ አያ ቦጋለ።

**አያ ቦጋለ:-** ደህና ይዋሉ፤ የምትልዎን ቶሎ ያድርሱኝ።...

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

ቄስ ታምሩ ይሳካላቸው ይሆን?

«ይሳካላቸው ይሆናል» ወይም «አይሳካላቸውም» የምትሉ፤ ካነበባችሁት ውስጥ ማስረጃ በመጥቀስ አብራሩ።።

## ትእይንት ሁለት

(ትዕይንት ሁለት የሚፈጸመው በእመት ውድነሽ በጣሙ ቤት ውስጥ ነው። ጊዜው ምሽት ላይ ነው። በቤት ውስጥ እመት ውድነሽ ከንስሐ አባታቸው ከቄስ ታምሩ ጋር ሲነጋገሩ ይታያል)።

**ቄስ ታምሩ:-** አያ ቦጋለን ያውቋቸው የለ? ቦጋለ መብራቱን?

**እመት ውድነሽ:-** አያ ቦጋለን እንዴት አጣዋለሁ? አንድ አካባቢ ሁነን!

**ቄስ ታምሩ:-** «አንድ ክቡር ሃሳብ አለኝ» ይላሉ አያ ቦጋለ!

**እመት ውድነሽ:-** ምንድር ነው ክቡር ሃሳብ ደግሞ በአንድ አካባቢ እየኖርን?

**ቄስ ታምሩ:-** አያ ቦጋለ እስዎን «ለጋብቻ አስቤያታለሁ» ይላሉ።

**እመት ውድነሽ:-** (እንደማፈርም እንደ ማዘንም ብለው፣ ቄስ ታምሩንም ለማየት አፈር እያሉ፣ ዓይናቸውን መሬት ላይ ተክለው ዝም ይላሉ።)

**ቄስ ታምሩ:-** ወይዘሮ ውድነሽ! የከነከነዎ ነገር ምንድነው?

**እመት ውድነሽ:-** (ትንሽ እንደማፈርም እያሉ፣ አፋቸውም እየተሳሰረባቸው እንደምንም ብለው ራሳቸውን እያጠናከሩ) አያ ቦጋለ ሦስት ባሎች በተራ ካገባሁኝ በኋላ ሦስቱም በተራ እንደሞቱብኝ እዚሁ በአካባቢው ተቀምጦ እያወቀ እኔን «ላግባ» ብሎ መጠየቁ ማዘኔን ስለተረዳ፣ "ደስ ላሰኛት፣ ልጽደቅባት" ብሎ ነው? ወይስ... ምንድ ነው?

**ቄስ ታምሩ:-** (መልስ ለመስጠት ፈጠን እያሉ) የለም! የለም! እንደዚያ አይደለም፤ "ደስ አሰኝቻት ደስ ታሰኘኛለች" ብለው ነው እንጂ "ልጽደቅባት" ብለው አይደለም።

**እመት ውድነሽ:-** (በመገረም ይጠይቃሉ) እንዴት!?

**ቄስ ታምሩ:-** *(ረጋ ደፈር በማለት መልስ ይሰጣሉ)* እስዎም ባሎችዎ በመሞታቸው ምክንያት፣ አያ ቦጋለም በልዩ ልዩ ምክንያት ብቸኝነት የሚያስከትለውን መከፋት ደኅና አድርጋችሁ ያወቃችሁ ስለሆናችሁ፣ ሁለታችሁ ብትገናኙ ተስማምታችሁ እንደምትኖሩ በማመን ነው። አያ ቦጋለ ቆዳቸው ሞኝ ቢመስል የዋዛ ሰው አይምሰሉዎ! ጥልቅ አሳቢ ናቸው።

(እመት ውድነሽ የንስሐ አባታቸውን መልስ ከሰሙ በኋላ፣ አንገታቸውን ደፍተው ዝም ብለው ብቻቸውን የሆኑ በሚመስል

ካሳባቸው ጋር መሟገት ስለጀመሩ፣ ቄስ ታምሩ ይቀጥላሉ፡፡) ይበሉ! እሺ ይበሉኝና አሳርጌ ልሂድ!

***እመት ውድነሽ፡-*** (በዚህ ጊዜ፣ እመት ውድነሽ ሳንባቸው እስኪሞላ ጠለቅ አድርገው አየር ስበው በረዥሙ ይተነፍሱና) እሺ አባቴ እስዎ የመከሩኝን አልቀበልም ብዬ ወዴት እደርሳለሁ!? እሺ!

(እመት ውድነሽ የእሽታ መልስ ሰጥተው የንስሐ አባታቸውን ካሰናበቱ በኋላ፣ ስለ አያ ቦጋለ የሚከተለውን በሀሳባቸው ማመላለስ ይጀምራሉ፡፡ እመት ውድነሽ በሀሳባቸው ለራሳቸው ይናገራሉ፡፡)

"አያ ቦጋለ መብራቱ መልከመልካም ነው፤ ነገር ግን ምንም ሀብት የለውም፡፡ እኔ ደግሞ የሞቱት ባሎቼ ሀብት አለኝ፡፡"
(እመት ውድነሽ ከሀብታቸው በተጨማሪ መልካቸውም ለብዙ ሰዎች የሚደነቅ መሆኑን በማሰብ፣ ሙዳያቸውን ከጉሽጉሽ ላይ አውርደው ይዘው ይቀመጡና የመጨረሻ ባላቸውን ብላታ ብዙነህን ሲያገቡ የገዘዋትን ክብ መስተዋት አውጥተው ቦግ አድርገው ይከፍታሉ)፡፡

በመስታዋቱ ውስጥ፣ አንዷት እንደመስተዋቱ ክብብ ያለች ፊት ከመስታዋቱ ውስጥ ብቅ ትላለች፤፡፡ እመት ውድነሽ መስታወቲቱን ትኩር ብለው ሲያይዋት፣ እስዋም ትኩር ብላ ታያቸዋለች፡፡ አንገታቸውን ወደግራ ዘንበል አድርገው ወደመስታወቲቱ ቀረብ ሲሉ፣ እስዋም አንገትዋን ዘንበል አድርጋ ወደሳቸው ቀረብ ትላለች፡፡ እመት ውድነሽ ያቺን የምታምር ክብ ፊት እየተመለከቱ ለራሳቸው ይናገራሉ፡፡

*(አዲስ አለማየሁ 1958፣ለማስተማሪያነት እንዲገለግል ሀሳብ ተጨምሮበት የቀረበ)*

## ክፍል አንድ:- ንባብ

**፩. ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል መርጣችሁ በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ:: ስምትሰጡት መልስ ማብራሪያ አቅርቡ::**

1. ጽሑፈ-ተውኔቱ ውስጥ የቀረቡት ቄስ ታምሩ፣ አያ ቦጋለ እና እመት ውድነሽ በስነ-ጽሑፍ ቋንቋ ምን ተብለው ይጠራሉ?
   ሀ) ግለሰቦች　　　　　　ሐ) ዋና ዋና ሰዎች
   ለ) ገጸባህርያት　　　　　መ) ተዋንያን
2. በመጀመሪያው ትዕይንት ከሁለቱ ገጸባህርያት ጋር የሚታዩት ነገሮች ምንድን ናቸው?
   ሀ) ሰፊ መስክ
   ለ) ሳር የሚግጡ ከብቶች
   ሐ) በመስኩ ፊት ለፊት የሚታይ ዛፍ
   መ) የተጠቀሱት ሁሉ መልሶች ናቸው::
3. አያ ቦጋለ እመት ውድነሽ በጣሙን ለሚስትነት የፈለጉበት ምክንያት _______ስለሆኑ ነው?
   ሀ) ሀብታም　　　　　　ሐ) ቆንጆ
   ለ) አግብቶ ፈት　　　　　መ) ብቸኛ
4. እመት ውድነሽ በጣሙ አያ ቦጋለን ለማግባት ያቅማሙት በምን ምክንያት ነው?
   ሀ) ቀደም ሲል ያገቧቸው ባሎች ስለሞቱባቸው፣
   ለ) ሀብት ስላልነበራቸው፣
   ሐ) ቆንጆ ስላልሆኑ፣
   መ) እድሜያቸው ገፍቶ ስለነበር

5. እመት ውድነሽ በመጨረሻ አያ ቦጋለን ለማግባት የተስማሙት እንዴት ነበር?

ሀ) የንስሐ አባታቸው ግፊት ስላደረጉባቸው እንጂ እሳቸው አልፈለጉም።

ለ) የቀደሙት ባሎቻቸው በመሞታቸው የሰዎችን አፍ ፈርተው እንጂ ውስጣቸው ደስተኛ ነበር።

ሐ) አያ ቦጋለ መልከ መልካም እና ሀብታም ስለ ነበሩ በጋብቻው ውስጣቸው ተደስቷል።

መ) አያ ቦጋለ መልከ መልካም አልነበሩም፤ ነገር ግን ሀብታም ስለነበሩ በልባቸው ተደስተዋል።

6. በጽሑፈ-ተውኔቱ የመጀመሪያ ትዕይንት ውስጥ የተገለፀው መቼት (መቼ? እና የት?) እንዴት ያለ ነው?

ሀ) ምሽት፣አያ ቦጋለ ቤት፣

ለ) ረፋድ ላይ፣መስክ፣ከብቶች ሳር የሚግጡበት ቦታ፣

ሐ) ምሽት፣እመት ውድነሽ ቤት፣

መ) ምሽት፣ቄስ ታምሩ መኖሪያ ቤት፣

7. በቀረበው ተውኔት ውስጥ የታየው ግጭት በምን ምክንያት የተፈጠረ ነው?

ሀ) አያ ቦጋለ፣ እመት ውድነሽን ሲያገቡ የሚሞቱ መስሎ የታያቸው መሆኑ፣

ለ) ለእመት ውድነሽ፣ በአከባቢያቸው የሚኖሩ ሰዎችን ሀሜታ መፍራታቸው፣

ሐ) ቄስ ታምሩ፣ እመት ውድነሽ አያ ቦጋለን ለማግባት እንደማይፈልጉ መገመታቸው፣

መ) እመት ውድነሽ፣ሀብታም ሰው ለማግባት ፍላጎት ያላቸው መሆኑ፣

8 በሁለተኛው ትዕይንት በተውኔቱ ውስጥ የተገለጸው መቼት በየትኛው ይገለጻል?

ሀ) ምሽት፣እመት ውድነሽ በጣሙ ቤት፣
ለ) ንጋት፣ እመት ውድነሽ በጣሙ ቤት
ሐ) ምሽት፣ ቄስ ታምሩ ቤት፣
መ) ንጋት፣ቄስ ታምሩ ቤት፣

9 በቀረበው ጽሑፈ-ተውኔት ውስጥ ምክንያትና ውጤት የተፈጠረው እንዴት ነው?

ሀ) እመት ውድነሽ በጣሙና አያ ቦጋለ መብራቱ ቢጋቡ ተረዳድተው መኖር መቻላቸው፣
ለ) እመት ውድነሽ በጣሙ አያ ቦጋለ መብራቱን ቢያገቡ አያ ቦጋለ መብራቱ የሚሞቱ መሆናቸው፣
ሐ) አያ ቦጋለ መብራቱ እመት ውድነሽ በጣሙን ቢያገቡ እመት ውድነሽ ሊሞቱ መቻላቸው፣
መ) አያ ቦጋለ መብራቱ እና እመት ውድነሽ በጣሙ ቢጋቡ ሁለቱም ሊሞቱ የሚችሉ መሆናቸው፣

**፪. ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት የሚከተሉት ቃላት ወይም ሐረጎች በምንባቡ ውስጥ የገቡበትን ፍች ስጡ።**

| | |
|---|---|
| 1. ትዕይንት | 5. ተውኔት |
| 2. ሙዳይ | 6. የገሀድ ዓለም |
| 3. መድረክ | 7. አሳረገ |
| 4. ክዋኔ | 8. ውሃ አጣጪ |

**፫. የተዉኔቱን ዋና ዋና ድርጊቶች ቀደም ተከተላቸዉን ጠብቃችሁ ግለጹ፤ አሠራራችሁ በድርጊት አንድ በተገለጸው ምሳሌ መሠረት ይሁን፡፡**

**ድርጊት አንድ፣** <u>አያ ቦጋለ፣ እመት ውድነሽ በጣሙን ለማግባት ስለሚችሉበት ሁኔታ ከቄስ ታምሩ ጋር ተመካከሩ</u>፡፡

**ድርጊት ሁለት፣**--------------------------------------------------

**ድርጊት ሦስት፣** --------------------------------------------------

**ድርጊት አራት፣**--------------------------------------------------

## ክፍል ሁለት፡- ንግግር

### የተውኔት አላባውያን

የተውኔት አላባውያን የሚባሉት ገጸባህርያት፣ ታሪክ፣ መቼት፣ ትልም (ምክንያትና ውጤት) እና ግጭት ናቸው፡፡

- ገጸባህርያት በአንድ ተውኔት ውስጥ በጸሐፌ-ተውኔቱ የሚፈጠሩ እና በተፈጠሩበት ተውኔት ውስጥ የሚያከናውኑት የሥራ ድርሻ ያላቸው፣ በገሀዱ ዓለም ሰውን መስለውና ሰውን ወክለው እንደ ሰው በመናገርና የተለያዩ ተግባራትን በመፈጸም የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ገጸባህርያት የሚናገርዋቸው ሆነ የሚፈጽሟቸው ድርጊቶች ለአንባቢያን ሆነ ለተመልካቾች ሙሉ በሙሉ ግልጽ ናቸው፡፡
- **መቼት**፡- ሌላ የተውኔት አላባ ነው፡፡ በአንድ ተውኔት ውስጥ ድርጊቱ መቼ እንደ ተፈጸመ፣ ጊዜውንና የት እንተፈጸመ ቦታውን ይገልጻል፡፡
- **ታሪክ**፡- በአንድ ተውኔት ውስጥ በንግግርም ሆነ በገጸባህርያት በድርጊት የሚከናወነው የአንድ ተውኔት ታሪክ ነው፡፡ የተውኔት ታሪክ ሌሎችን አላባውያን ይይዛል ማለት ነው፡፡ ገጸባህርያት፣ መቼት፣ ትልም እና ግጭት የሚፈጠሩት በአንድ ተውኔት ታሪክ ውስጥ ነው፡፧
- **ትልም**፡- ሌላው የተውኔት አላባ ነው፡፡ ገጸባህርያት የሚፈጽሟቸው ድርጊቶች ምክንያትና ውጤትን ተከትለው የሚካሄዱ እንደመሆናቸው፣ ትልም በተውኔቱ ውስጥ የሚካሄዱትን ነገሮች ምክንያትና ውጤት ያሳያል፡፡
- **ግጭት**፡- በአንድ ተውኔት ውስጥ የሚገኘው ሌላው አላባ ግጭት ነው፡፡ በአንድ ተውኔት ውስጥ ገጸባህርያት በሚያራምዱት ተግባር ወይም በሚያከናውኑት ታሪክ እርስበርሳቸው ወይም ይህን ላድርግ ወይስ አላድርግ በሚል በግል ከራሳቸው ጋር ይጋጫሉ፡፡ማንኛውም የተውኔት ታሪክ ያለግጭት ሊፈጠር አይችልም፡፡ ያለግጭት የሚፈጠር ታሪክ ተራ ታሪክ እንጂ የተውኔት ታሪክ አይሆንም፡፡

**፩. ቡድን በመመሥረት በትምህርት ቤታችሁ ወይንም በትምህርት ቤታችሁ አካባቢ ከሚገኝ ቤተመጻሕፍት ውስጥ፤ የተውኔት መጻሕፍትን በማንበብ፣**

1. አንድ የተውኔት ጽሑፍ ምረጡ፡፡
2. የመረጣችሁትን የተውኔት ታሪክ ዋና ዋና ነጥቦችን ለይታችሁ መዝግቡ፡፡
3. የተውኔት ታሪኩ ከምትኖሩበት የእውነታ ዓለም ጋር እንዴት ያለ ግንኙነት እንዳለው አጭር ማስታወሻ ጽፋችሁ ማብራሪያ ስጡ፡፡

## ክፍል ሦስት፡- ጽሕፈት

**፩. ጥንድ ጥንድ በመሆን በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ከቀረቡት አማራጮች መካከል መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላት (ሐረጎች) የሆኑትን በመምረጥ አሟሉ፡፡**

**በባዶ ቦታዎች ሲገቡ የሚችሉ መሸጋገርያና አያያዥ ቃላትና ሐረጎች**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. በማስከተል | ለ. በመቀጠል | ሐ. ዳግመኛ |
| መ. በተደጋጋሚ | ሠ. ከዚህ ቀጥሎ | ረ. እስከዚህ ድረስ |
| ሰ. ከዚህ በማያያዝ | ሸ. ከዚህ በኋላ | ቀ. ታዲያ |
| በ. በሌላ ጊዜ | ተ. በዚህ አኳኋን | ቸ. ወደፊት |
| ኀ. ደግሞ | ነ. ብቻ | |

1. ተጋባዡ ተናጋሪ፣ መጻሕፍት የማንበብ ልምድን በሚመለከት ገለጻ አደረጉ፤ __________ ስለሚያነቧቸው መጻሕፍት በራስ አባባል ማስታወሻ መጻፍ ጠቃሚ እንደሆነ ተናገሩ፡፡
2. የጤና ባለሞያው የኤች አይ ቪ ኤድስን የመተላለፊያ መንገዶች በሚመለከት ዋነኛ የሆኑትን በዝርዝር አቀረቡ፤ __________ በዚሁ ጉዳይ ላይም ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸውን ነጥቦች ለይተው ገለጻ በመስጠት ንግግራቸውን ደመደሙ(ጨረሱ)፡፡

3. ተውኔትን በሚመለከት ግጥሞችን አስፋፍቶ ተውኔቶችን እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል ተምረናል፡፡ ________ አያያዥ ቃላትን ወይም ሐረጋትን እንማራለን፡፡
4. እስካሁን ያለው የንባብ ልምዳችን ብዙ የሚያኮራን ላይሆን ይችላል፤ _______ ግን አስፈላጊነቱን ስለተረዳን ጠንክረን ልናሻሽለው እንችላለን፡፡
5. ሁሉም ኢትዮጵያዊ የየድርሻውን በተሰማራበት ተግባር ለአገሩ እድገት ማበርከት አለበት፡፡ ________ የተሠሩት ሥራዎች በቂ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡
6. እንደሌሎች ክበቦች ሁሉ በትምህርት ቤታችን የተውኔት ክበብ በሚገባ ተደራጅቷል፡፡ ክበቡ _______ በየሦስት ወራት የተለያዩ ተውኔቶችን ለተማሪዎች ያሳያል፡፡

**፪. በሚከተሉት አያያዥ ቃላት (ሐረጎች)፣ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ። በመሠረታችኋቸዉ ዓረፍተነገሮች ውስጥ በተጠቀማችኋቸዉ አያያዦች ዙሪያ ሀሳብ ተለዋወጡና በሚሰጣችሁ ማሻሻያ መሠረት ዓረፍተነገሮቻችሁን እንደገና ጻፉ።**

| |
|---|
| እና፣ ይሁን እንጂ፣ ሆኖም፣ ስለዚህ፣ ወይም፣ ነገር ግን፣ ከዚያም |

***ምሳሌ፣*** ሀ) በሕይወት ውስጥ የኑሮን ውጣ ውረድ መታገል እና ማሸነፍ ያስፈልጋል፡፡ (መታገልና ማሸነፍ የሚሉት ቃላት በ "እና" ተያይዘዋል)፡፡

ለ) ኃይሌ በብዙ ቦታዎች በሩጫ ስለ ተወዳደረ እና ስለ አሸነፈ ጥንካሬውን አረጋግጧል፡፡ (ስለተወዳደረ እና ስለአሸነፈ የሚሉት ሐረጎች በ"እና" ተያይዘዋል)፡፡

ሐ) የኤች አይ ቪ ኤድስ ሕመምተኛው ብቸኛ ነው፤ ስለዚህ በአጠገቡ ሆኖ የሚንከባከበው ሰው ያስፈልገዋል፡፡ (ሁለቱ ዓረፍተነገሮች በአያያዥ ቃል "ስለዚህ" ተያይዘዋል)፡፡

## የሥራ ደብዳቤ

ብዙ የደብዳቤ ዓይነቶች አሉ፡፡ ከነዚህ ዉስጥ አንዱ የሥራ ደብዳቤ ነው፡፡ የሥራ ደብዳቤ በተቋማት፣ በተለያዩ ድርጅቶች፣ በትምህርት ቤት ወዘተ. ውስጥ ለተለያዩ ክፍሎችና ለግለሰቦች ይጻፋል፡፡ የሥራ ደብዳቤ፣ የሚመለከተውን አካል ለማስታወስ፣ አንድ መሰረታዊ ጉዳይ ላይ ትኩረት እንዲደረግ ለማሳሰብና ትእዛዝ ለማስተላለፍ አገልግሎት ልይ ይዉላል፡፡ የሥራ ደብዳቤ ሲጻፍ የሚከተለውን ቅርጽ ይይዛል፡፡

1. የሥራ ደብዳቤ የተጻፈለት ሰው ወይም ክፍል አድራሻ
2. የሥራ ደብዳቤውን የጻፈው ሰው ወይም ክፍል አድራሻ
3. የተጻፈበት ቀን
4. የተጻፈበት ጉዳይ
5. ዝርዝር ሐተታ
6. «ከሰላምታ ጋር» የሚለው ቃል እንደ መልካም ምኞት መግለጫ

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን የሥራ ደብዳቤ ናሙና በአስተውሎት ተመልከቱ::

ታህሳስ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ለመምህር ከበደ ታገል
የፀረ-ኤድስ ክበብ አስተባባሪ

ጉዳዩ፡ በፀረ-ኤድስ ክበብ ተሳታፊ ያልሆኑትን የክበብ አባላት ስለማሳወቅ፣

ጥቅምት ፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም የትምህርት ቤቱ የፀረ-ኤድስ ክበብ ሰብሳቢ ሆኜ መመረጤ ይታወሳል፤ ይሁን እንጂ፣ ሥራዬን ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ አንዳንድ አባላት በምናደርገው ስብሰባና በምናከናውናቸው ተግባራት ላይ ፈጽሞ ተገኝተው አያውቁም:: ከዚህ በፊት ይህንን ችግር በቃል ገልጬልዎት፣ በክበቡ ሥራ ውስጥ የማይሳተፉትን ተማሪዎች ስም ለይቼ በጽሁፍ እንዳቀርብልዎ መጠየቅዎ ይታወሳል:: በመሆኑም የተማሪዎቹን ዝርዝር ከዚህ እንደሚከተለው አቅርቤያለሁ::

1. ገመቹ ቱፋ
2. ተስፋዬ ጎይቶም
3. አየለች መታፈሪያ
4. ከድር ኡስማን
5. አስማማው ለገሰ

ከዚህ በላይ ስማቸው የተዘረዘረው ተማሪዎች በመደበኛ ስብሰባ ወቅትም ሆነ በሚደረገው የሥራ ክንውን ውስጥ አንድም ጊዜ ተገኝተው የማያውቁ መሆናቸውን በአክብሮት እገልጻለሁ::

ከሰላምታ ጋር
ፊርማ
ከተማሪ መዝሙር ወርዶፋ
የትምህርት ቤቱ የፀረ-ኤድስ ክበብ ሰብሳቢ

፫. የቀረበላችሁን የሥራ ደብዳቤ በመከተል በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ በሚገኙት ክበቦች ውስጥ በአንዱ ሰብሳቢ ሆናችሁ እንደተመረጣችሁ በመገመት የክበቡ አባል ሆነው አብዛኛውን ጊዜ ለማይገኙ ተማሪዎች የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ጻፉ::

## ክፍል አራት፣ ሰዋስው

፩. የሚከተሉትን መነሻና መድረሻ ቅጥያዎች በመጠቀም ቃላትን መስርቱና ዓረፍተነገሮች ሥሩባቸው።

ምሳሌ፣ -ዎች፣ -ኦች፣ ሲ-፣ እየ-፣ ስለ-፣ በ-

፪. ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት ዓረፍተነገር መሥርቱባቸው፤ ከዚያም በመሰረታችሁት ዓረፍተነገር ውስጥ የቃላቱን ሙያ "ባለቤትነት፣ ተሳቢነት" እያላችሁ ግለጹ::

ምሳሌ፣ወጣቱ ትውልድ ሀገር ተረካቢ ነው::

በዚህ ዓረፍተነገር ‹‹ትውልድ›› የሚለው ቃል ሙያ ባለቤትነት ነው::

1. ትውልድ
2. ግንባታ
3. የእጅ ኳስ
4. መንቀፍ
5. ማህበር
6. ልማት
7. ሥነ ምግባር
8. አታላይ

፫. የሚከተሉትን ቃላት በነፃና በጥገኛ ምዕላድ ከፋፍሉ፤ ሙከራችሁንም ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማቅረብ ተነጋገሩባቸው::

ምሳሌ፣ሰዎች፤ ሰው-ኦች

ነፃ ምዕላድ ← ሰው-ኦች → ጥገኛ ምዕላድ

1. ገበሬዎች
2. ወንድሟ
3. ስሙ
4. በናትህ
5. ባርኔጣዎች
6. አገሯ
7. ገንዘቧ
8. ደብተርሽ
9. ቤቶች
10. አምራቾች

፲. በቡድን ሆናችሁ የራሳችሁን ነፃ እና ጥገኛ ምዕላድ የያዙ አምስት ቃላት በመፈለግ በቃሎቹ ውስጥ ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን ለዩና መልሳችሁ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡና ተነጋገሩባቸው፡፡

## ክፍል አምስት:- ስነጽሑፍ

፩. የሚከተለውን ግጥም (ልጅቱ የዘመነችቱ) ወደ ተውኔት ለውጣችሁ ካዘጋጃችሁ በኋላ፣ ክፍል ውስጥ መድረክ ላይ አቅርቡ፡፡ የተሻለ አቀራረብ አለዉ የምትሉትን ቡድን በጋራ ውይይት ምረጡ፡፡ (ከክፍል ውጭም በተለያዩ የትምህርት ቤቱ ክበባት መድረክ አዘጋጅታችሁ ተመልካች ባለበት ልትተውኑ ትችላላችሁ)፡፡ ግጥሙን ወደ ተውኔት በምትለውጡበት ጊዜ የሚከተሉትን በቅደም ተከተል አከናውኑ፡፡

1. የቀረበውን ግጥም በሚያመቻችሁ መንገድ ማስፋት፣
2. ወደ ተሟላ ጽሑፈ-ተውኔት (የተውኔት ጽሑፍ) መለወጥ፣
3. ተውኔቱ የሚዘጋጅበትን መድረክ ማመቻቸት
4. በተውኔት ውስጥ በሚፈጠሩት ገጸ-ባህርያት መሠረት ተዋንያን /ተዋንያት/ መምረጥ
5. ለተውኔቱ አስፈላጊ የሆኑትን አልባሳት ማዘጋጀት፤
6. ተውኔቱን ማጥናት፣
7. ተውኔቱን መለማመድ
8. በልምምድ ላይ የሚታዩትን ስህተቶች ማረም፣
9. በመድረክ ላይ ማዘጋጀት እና የተመልካቾችን አስተያየት መቀበል

**የሚከተሉት ቃላት ቀጥሎ ከቀረበው ግጥም ውስጥ የወጡ ናቸው። ግጥሙን ወደ ተውኔት ከመለወጣችሁ በፊት፣ ግጥሙን ለመረዳት እንዲያግዛችሁ አገባባዊ ፍቻቸውን አስተውሉ።**

1. ***የዘመነችቱ***፣ ዘመናይ መሆን፣ (በግጥሙ ውስጥ አጉል ሥልጣኔን የሚያመለክት ነው።)
2. **ዳሩላዋን**፣ የታሰረ ፀጉሯን (ሴቶች በእንቅልፍ ሰዓት ፀጉራቸውን በወፍራሙ በሹሩባ ዓይነት ይቋጥሩትና ሻሽ ያስሩበታል፤ እንዳይበላሽ ለመጠበቅ ነው።)
3. **ጥፍት**፣ መነካካት፣ (‹‹ጥ›› ይጠብቃል፤ በእጅ ጣቶች)
4. **ዱቅት**፣ ቅብት (‹‹ቅ›› የጥጠብቃል፤ መቀባት)
5. **ሱርት**፣ ልብስ (‹‹ብ›› ጠብቆ ይነባል፤ቃሉ ድርጊታዊ ቃል ነው፤ ሱሪ ከሚለው ቃል ነው የተመሠረተው፣ አለባበሷን ያመለክታል።)
6. **ጭምት**፣ ጫማ ማድረግ፣መጫማት (‹‹ጭ››ይጠብቃል፤ ይህም ድርጊታዊ ቃል ነው፤ ጫማ ከሚለው ቃል ነው የተመሰረተው፣)
7. **ቅብትት**፣ እስር፣ አጥብቆ ማሰርን ያመለክታል፤ (በቃሉ መጨረሻ ላይ ያለው ‹‹ት›› ይጠብቃል፤ ይህም ቀበቶ ከሚለው ቃል የተመሰረተ ነው።)
8. **ጅክት**፣ ልብስ (ይህም ቃል ጃኬት ከሚለው ቃል የተመሰረተ ድርጊታዊ ቃል ነው።)
9. **ፕሮቫ**፣ የአለባበስ፣ የአጊያጊያጥ የአረማመድ ወዘተ. ልምምድ፤
10. **ገሪብ**፣ ያልሰለጠነ (በልጅቷ አስተሳሰብ ወላጆቿን ያልሰለጠኑ ናቸው ማለትዋ ነው።)
11. **እያሳቀለች**፣ እየረገመች፣
12. **እየገረመመች**፣ በግልምጫ እየተመለከተች፣

## ወደ ተውኔት የሚለወጠው ግጥም

(ይህ ግጥም በምጸት የቀረበ ነዉ፡፡ ልጅቷ የሰለጠነች የሚመስሳት፣ ነገር ግን ያልሰለጠነች፣ ጥራዝ ነጠቅ መሆንዋን ያመለክታል፡፡)

### ልጅቱ - የዘመነችቱ

ልጅቱ - የዘመነችቱ

ጧቱን ብድግ ንሥት
ትለውና
ፊቷን ትጥብ እሸት
ፍትግ ፍትግትግ
ዳሩላዋን ልቅቅ ጥፍት
ሌላ ምናምን ዱቅት
ሽፋሏን ቅልም ጥቁርት
ከንፈርዋን ቅብት ቅልት
ታደርግና፤

ልጅቱ - የዘመነችቱ

ሱሪዋን ለምቦጫሙን - ሱርት
ጫማዋን ነጠላውን - ጭምት
ቀበቶዋን ሰፊውን - ቅብትት
ጃኬቷን የቆዳውን - ጅክት
ታደርግና ፤

ልጅቱ - የዘመነችቱ

መስቷቱ - ትልቁ መስቷት ፊት
ትቆምና፤
ሣቅ ግጥጥ … ሣቅ ግጥጥ … ሣቅ

ደርሶ ፍልቅ … ፍልቅልቅ … ፍልቅልቅልቅ
ከንፈር ገጠም … ደሞ ከፈት …
ደሞ ገጠም … ገጠምጠምጠም
ወደጓላ ሂድት … ሂድት
ደሞ ምልስ … ምልስ … ምልስልስልስ
ሽንጧን ሰበር … ቅልስ … ቅልስልስልስ
ዳሌዋን ውዝ ውዝ
ቂብ ቂብ … ቁንን ቁንን
ክው ክው … ጅንን ጅንን
ደሞ ፈገግ … ደሞ ቅጭም … ቅጭምጭምጭም
ዐይኗን ከፈት … ደሞ ጨፈን … ስልምልምልም
ደሞ ጉርጥ … ደሞ ጥቅስ … ደሞ ጉልጉል
(በራሷ ትቀልድ ይመስል)

ልጅቱ - የዘመነችቱ
ፕሮቫው ብሎ ጥቅልል
ወደ ቁርሷ መለስ ስትል
እማማዋ ንድድ ቁጥት
ትንሽ እህቷን ጥርት
በኩርኩም ግጭት!
"ገና ካሁኑ ይወጣብሽ
ለምነው ጧት መነሣትሽ?"
ደሞ ማለት፡፡
አባባዋም እዝን ቁጭት
ጸሎታቸውን ዝንግት
"ውይጉድ መበላሸት"
አርዝመው እያዩ ማለት፡፡

ልጅቱ - የዘመነችቱ

ገራብ ገራብ እያለች
እማየዋን እያሣቀለች
አባዬዋን እየገረመመች
ቦርሳዋን እንደ ቦረሠች
ላስቲክ ብጤ ነገር ባፍዋ እያላመጠች
እያንቀጫቀጨች
ርፍድ ብሎባት ችኩል ችኩል እያለች
እሑድ ጧቱን ባንድ ሰዓት ውልቅ ያለች
(አፍታም ሳትቆይ - ወድያውኑ)
ሰኞ ጧቱን ምልስ ትላታለች።
ልጅቱ - የዘመነችቱ።

*(ደበበ ሰይፉ፣ 1980፣ 44 — 45)*

**፪. በሚከተለው ግጥም ውስጥ በሰውኛ ዘይቤ የቀረቡትን ክፍሎች ከለያችሁ በኋላ በግጥሙ ውስጥ የሚታየውን የሰውኛ ዘይቤ አጠቃቀም እና ባህርይ በማብራራት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።**

## ስደተኛው ዐባይ

ከኢትዮጵያ፣ ካፍሪቃውያን ገነት፤
በጐጃሙ ክፍል፣ ሰከላ ከሚሉት፤
ከዚያ ከረግረጉ፣ ከግሽ ዓባይ መሬት፤
ከዚያ ነው የፈለቅሁ፣ ዕወቁኝ ሊቃውንት።

ከዚያ ተነስቼ፣ ለመሄድ አቀድኩኝ፤
በኮረኮንች መንገድ፣ ጉዞየን ቀጠልሁኝ፤
በጥንተ ተፈጥሮ፣ እኔን የመሰሉኝ፤
በግራና በቀኝ፣ እክብረው አጀቡኝ፤
ትንሽ ወረድ እንዳልሁ “ወተት ዐባይ” አሉኝ።

ከዚያ ተነሥቼ፣ እየተዝናናሁኝ፤
በጣና ሐይቅ ላይ፣ አለፍኩና ሄድኩኝ፤
ከዚያ በኂላማ፣ ታላቅ ጅረት ሆንኩኝ፡፡
ከዚያ አልፌ ስደርስ፣ ከታላቁ ቋጥኝ፤
ፏፏቴ ሆንሁና፣ ከሰማይ ወረድኩኝ፡፡
ካጠገቤ ቁመው፣ የተመራመሩኝ፤
“ጢስ ዐባይ” አሉና፣ ሰሜን አወጡልኝ፡፡

ጐጃምን ከጐንደር፣ እያካለልኩት፤
ወሎንም ከጐጃም እያዋሰንኩት፤
ሸዋንም ከጐጃም፣ እያካፈልኩት፣
ወለጋን ከጐጃም፣ እያካለልኩት፤
መንቀሳቀስ ጀመርሁ ወደተለምኩት፡፡

*(ዜና ማርቆስ እንዳለው፣ 1992፣ 27-28)*

**፫. ከሚከተለው ግጥም ውስጥ አነጻጻሪ እና ለዋጭ ዘይቤዎችን ለዩና አጠቃቀማቸው እንዴት እንደሆነ በመግለጽ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርባችሁ ተነጋገሩባቸዉ፡፡**

## ሙዚቃ

ፈልቀሽ የተገኘሽ፣ ከሹበርት ራስ፣
ከቤቶቨን ናላ፣ ከሞዛርት መንፈስ፤
ከሾፐን ትካዜ፣ ከያሬድ ልቦና፤
መዓዛ የሞላብሽ፣ የብስጭት ቃና፤
ረቂቋ ድምጽ ሆይ፣ ውቢቷ ሙዚቃ፤
ንጹሕ እንደ ፀሐይ፣ ውብ እንደጨረቃ፡፡
የጨዋታሽ ለዛ፣ የድምጽሽ ፍስሐ፤
መሳይ ድንቅ አረቄ፣ የነፍስ እህል ውሃ፡፡
አገርሽ ገነት ነው፣ ሰፈርሽም ኤደን፤

በሰማንሽ ቁጥር፣ ባሳብ መንገድ ሄደን፤
ታጫውቺናለሽ፣ በሕሊና ቋንቋ፤
ነፍሴ ካንቺ ጋራ፣ በመተዋወቋ፤
ትሽቆጠቆጣለች፣ ድምጽሽን ስትሰማ፤
ጠባይሽ ሲገለጥ፣ በምድራዊ ዜማ፤
መስሎ የሚመነጭ፣ ከገነት የወጣ፤
ጣዕሙ አይጠገብም፣ ቢጠጣ ቢጠጣ።
የትካዜ ከርቤ፣ የብስጭት ዕጣን፤
የመልአኮች ቋንቋ፣ የሱራፌል ልሳን፤
ቃናሽ ነፋስ ሆኖ፣ ድምጽሽ ሠረገላ፤
ውሰጃት እባክሽ፣ ነፍሴን ወደ ሌላ።

*(ከበደ ሚካኤል፣ 1994፣ 125)*

## ማጠቃለያ

በምዕራፍ ስድስት ውስጥ የተውኔት አላባውያን ቀርበዋል፡፡ የተውኔት አላባ ውያን፣ገጸባህርያት፣ታሪክ፣መቼት፣ምክንያትና ውጤት፣ግጭት እና ጭብጥ ናቸው፡፡

ሐሳብን በጽሑፍ በመግለጽ ውስጥ የአጻጻፍ ሥርዓት አለ፡፡ በጽሑፍ የሚገለጽ አንድ ርዕሰ ጉዳይ በተለያዩ አንቀጾች ይገለጻል፡፡ ከአንድ አንቀጽ ወደ ሌላኛው አንቀጽ ለመሸጋገር አያያዥ ቃላትን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

በንግግር እና በጽሑፍ በሚገለጹ ዓረፍተነገሮች ውስጥ የመነሻና የመድረሻ ቅጥያዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ቅጥያዎች በትክክል መጠቀም የተፈለገውን ሀሳብ በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ለሌላው ሳይሳሳት በሚገባ ለማስተላለፍና ለማድረስ ያግዛል፡፡

በንግግርም ሆነ በጽሑፍ በዓረፍተነገሮች አማካይነት የሚሸጋገሩትን ሀሳቦች ከስህተት የጸዱ እንዲሆኑ የመቆጣጠሪያው መንገድ በዓረፍተነገር ውስጥ በባለቤትነት፣ በተሳቢነትና በማሰሪያ አንቀጽነት የሚያገለግሉትን ቃሎች መለየት ይሆናል፡፡ እነዚህ ቃሎች መስተአምሮችን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

የሥራ ደብዳቤዎች በድርጅቶች፣ በመስሪያ ቤቶች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በተለያዩ ተቋማት፣ ወዘተ. ለተለያዩ ክፍሎችና ግለሰቦች የሚጻፉ ደብዳቤዎች ናቸው፡፡ የሥራ ደብዳቤ የራሱ የሆነ የአቀራረብ ቅርጽ እንዳለው መረዳት ይገባል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በቀረበው ጽሑፈ-ተውኔት፣ በትእይንት አንድና ሁለት ውስጥ ያሉት ገጸባህርያት ምን ዓይነት ድርጊት እንደሚፈጽሙ ለይታችሁ አመልክቱ።
2. ነፃ እና ጥገኛ ምዕላድ የያዙትን አምስት ቃላት በመምረጥ በነፃና በጥገኛ ምዕላዶች ከከፋፈላችሁ በኋላ ለነፃ እና ጥገኛ ምዕላድ መግለጫ በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።
3. በስም እና በግስ የቃል ክፍሎች ባለቤት ተሳቢና ማሰሪያ አንቀጽ ያላቸው አምስት ዓረፍተነገሮች ከመሰረታችሁ በኋላ በባለቤት በተሳቢና በማሰሪያ አንቀጽ ያገለገሉትን የቃል ክፍሎች በመለየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡና ተነጋገሩባቸው።
4. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ካሉት ክበባት በአንዱ፣ ሊቀመንበር እንደሆናችሁ ራሳችሁን በመቁጠር ክበቡ በሚያደርገው ስብሰባ ብዙ ጊዜ ለሚቀረው አንድ አባል የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ጻፉ።

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስድስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ በነጥቦቹ ላይ በቂ ግንዛቤ ጨብጣችሁ ከሆነ /✓/ ምልክት አስቀምጡ፡፡ ግንዛቤያችሁ አጠራጣሪ ከሆነ የጥያቄ ምልክት(?) አድርጉ፡፡ ሙሉ ለሙሉ ግንዛቤ ከሌላችሁ /x/ ምልክት አስቀምጡ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | ✓ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የተውኔትን ምንነት እና የተውኔት አሳባውያንን መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 2. | የተወሰኑ ጽሑፈ-ተውኔቶችን አጥንቼ መጫወትና፤ መተወን እችላለሁ፡፡ | | | |
| 3. | በምጽፈው ጽሑፍ ውስጥ መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትን በተገቢው ቦታቸው መጠቀም ችያለሁ፡፡ | | | |
| 4. | ከቃላት ውስጥ መነሻና መድረሻ ቅጥያዎችን በመለየት አመለክታለሁ፡፡ | | | |
| 5. | ቃላትን እንደባለቤት፣እንደተሳቢና እንደማሰሪያ አንቀጽ ተጠቅሜ ዓረፍተነገሮች እመሠርታለሁ፡፡ | | | |
| 6. | የቃላትን ነፃና ጥገኛ ምዕላዶች ለይቼ አገልፃለሁ፡፡ | | | |
| 7. | የተለያዩ የሥራ ደብዳቤዎችን መፃፍ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 8. | ከግጥሞች ውስጥ አነፃፃሪ፣ ለዋጭና ሰውኛ ዘይቤዎችን መለየት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 9. | የውይይትን ሥርዓት በመጠበቅ በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ መወያየት እችላለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(x) ምልክቶች ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

## አካባቢያችን

**የምዕራፉ ዓላማዎች:- ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- አካባቢን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በመረጃ የተደገፈ ሃሳብ ታቀርባላችሁ::
- ካዳመጣችሁትና ካነበባችሁት ጠቃሚውን በመለየት ማስታወሻ ትይዛላችሁ::
- በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ በስርዓት ትጨዋወታላችሁ::
- መመሪያን ተከትላችሁ ክርክር ታካሂዳላችሁ::
- አስተዋፅኦ ነድፋችሁ አስረጅ ድርሰት ትጽፋላችሁ::
- በአካባቢያችሁ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በፈርጅ በፈርጃቸው ትሰበስባላችሁ::

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. የአካባቢ ብክለትን የሚያስከትሉ ምን ምን ነገሮች ናቸው? በቡድን ተወያዩና በጋራ ውይይት አንድ አቋም ላይ ድረሱ፡፡ የደረሳችሁበትን ከምንባቡ ጋር አገናዝቡ፡፡

፪. የአካባቢ ንጽህና አለመጠበቅ፣ ምን ዓይነት ችግሮችን ያስከትላል?

፫. የግልና የአካባቢያችንን ንጽህና ለመጠበቅ ከእያንዳንዳችን ምን ይጠበቃል?

## ቆሻሻና አወጋገዱ

ቆሻሻ ከመኖሪያ ቤታችን፣ ከቢሮዎችና ከኢንዱስትሪዎች እያወጣን የምንጥለው የማይፈለግ ነገር ነው፡፡ ቆሻሻ ሲባል በየቦታው **ተዝረክርኮ** ወይም በየቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ውስጥ ያለ ደረቅ ቆሻሻ፣ አለዚያም እርጥብ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁላችንም ቁርጥራጭ ወረቀቶችን፣የምግብ ትራፊዎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን በምንጥልበት ወቅት ቆሻሻ እንፈጥራለን፡፡ የኢንዱስትሪ ምርቶች በሚመረቱበት ጊዜም ቆሻሻ ይፈጠራል፡፡

ቆሻሻ ቁጥጥር ካልተደረገበትና በማንኛውም ቦታ የሚጣል ከሆነ፣ በአካባቢና በሰው ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ስለዚህም፣ አፈርን ወይም ውሃን በማይበክልበት ቦታና ሰዎችም በዚሁ **ሳቢያ** ለአደጋ **በማይጋለጡበት** ሁኔታ ማስወገድ አለብን፡፡

ማንኛውም የቆሻሻ ዓይነት በአግባቡ ካልተያዘ እኛንና አካባቢን ሊጎዳ ይችላል በአግባቡ **የአካባቢን እይታ** ያበላሻል፤ መጥፎ ጠረን ያስከትላል፡፡ ለዝንቦች፣ ለአይጦችና ልዩ ልዩ ተዋህስያን መራቢያ በመሆን በሽታ እንዲስራጭ ያደርጋል፡፡ ዕፅዋትን፣ እንስሳትንና ሰዎችን ይመርዛል፡፡ አየርና ውሃን **ይበክላል**፡፡ የረጅም ጊዜ ጎጂ ተፅኖው ደግሞ መርዛማ ኬሚካሎች በአካባቢው ውስጥ ሳይሰባበሩ መቆየታቸውና በአየርና በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጉዳት ማድረሳቸው ነው፡፡

ሁላችንም ብንሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቆሻሻ ስለምንፈጥርና ይህም ቆሻሻ ብክለትን ስለሚያስከትል፣ በአግባቡ የመያዝ ኃላፊነት አለብን፡፡

የቆሻሻ አያያዝ በአራት ደረጃዎች ይካሄዳል:: ይህም **የተቀናጀ** የቆሻሻ አያያዝ ይባላል:: የመጀመሪያው ደረጃ ኢንዱስትሪዎች በተቻለ መጠን አነስተኛ ቆሻሻ የሚፈጠርበትን የአመራረት ሂደት መከተላቸው ነው:: ይህ በንፁህ የአመራረት ሂደት መጠቀም ይባላል:: ሁለተኛው እርምጃ ተመልሶ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለውን ማንኛውንም ነገር ከቆሻሻ መለየት ነው:: ይህ ቆሻሻን መልሶ መጠቀም ወይም ሀብት **እንዲያገግም** ማድረግ ይባላል:: ሶስተኛው እርምጃ እያንዳንዱን የቆሻሻ ዓይነት አነስተኛ ቦታ እንዲይዝ አድርጎ **ማጨቅና** ጉዳቱ እንዲቀንስ ማጣራት ነው:: አራተኛው እርምጃ ከላይ የተጠቀሱት ተግባሮች ከተከናወኑ በኋላ የሚቀረውን ማንኛ ውንም ቆሻሻ በአግባቡ ተጠንቶ ወደ ተሠራ የቆሻሻ መጣያ ወስዶ መጣል ነው::

ከላይ በተጠቀሱት መንገዶች ቆሻሻን ከምንጩ ጀምሮ እስከሚወገድበት ስፍራ ድረስ የሚደረግ ክንውን፣ ቆሻሻን ከምንጩ እስከ መቀበሪያው የመቆጣጠር መርሆ ይባላል:: ይህንን መርሆ በመተግበር **የምናልመውን** ንጹህ አካባቢ መፍጠር **ፋይዳው** ብዙ ነውና ዛሬውኑ ለተግባር እንነሳ::

*(ተፈጥሮ መጽሔት፣ የካቲት 1997፣ መሻሻል ተደርጎበት የቀረበ)*

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ:- ንባብ

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ፤ ምክንያታችሁንም ከምንባቡ ውስጥ በመጥቀስ ግለፁ::**

1. ቆሻሻን በመፍጠር በኩል ሁሉም ሰው የየራሱ ድርሻ አለው::
2. መርዛማ ኬሚካሎች ሳይሰባበሩ መቆየታቸው ጉዳቱ ወዲያው የሚታይና ወዲያው ሊወገድ የሚችል ነው::
3. ቆሻሻን በአግባቡ የመያዝ ሐላፊነት የከተማ ማዘጋጃ ቤቶች ነው::
4. የቆሻሻ አያያዝ አራት ደረጃዎች አሉት::
5. በንፁህ የአመራረት ሂደት መጠቀም ከኢንዱስትሪዎች ማምረት ጋር የተያየዘ ነው::

**፪. የሚከተሉት ጥያቄዎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው። በምንባቡ መሠረት ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጭ መልሶች ትክክለኛውን ምረጡ።**

1. ቆሻሻን በሚመለከት ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ) ኢንዱስትሪዎች በሚያመርቱበት ጊዜ ቆሻሻ ይፈጠራል።
   ለ) ቁርጥራጭ ወረቀቶች ንፁህ ይሁኑ እንጂ፣ የትም ቢጣሉ ቆሻሻ አይባሉም።
   ሐ) ማንኛውም ቆሻሻ ሰውን ሊጎዳ ይችላል።
   መ) ማጨቅና ማጣራት ሶስተኛው የቆሻሻ አያያዝ ደረጃ ነው።

2. በአራት ደረጃዎች የሚካሄድ የቆሻሻ አያያዝ ----------- የቆሻሻ አያያዝ ይባላል።
   ሀ) የተቀናጀ፣ ሐ) ንፁህ፣
   ለ) ፍትሀ፣ መ) የኢንዱስትሪ

3. በአግባቡ ያልተያዘ ቆሻሻ በሽታን እንዲሰራጭ የሚያደርገው በምንድን ነው?
   ሀ) መጥፎ ጠረን በማምጣት፣
   ለ) የአካባቢ እይታን በማበላሸት፣
   ሐ) የልዩ ልዩ ተዋህስያን መራቢያ በመሆን፣
   መ) ጠጣር ሆኖ ለብዙ ጊዜ በመቆየት።

4. ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለውን ነገር፣ ከቆሻሻ መለየት--------- ይባላል።
   ሀ) ሀብትን እንዲያገግም ማድረግ፣ ሐ) ማጣራት፣
   ለ) ምርትን መልሶ መጠቀም፣ መ) ከብከባ ማፅዳት፣

5. ቆሻሻን በጥናት ወደ ተሰራ መጣያ ወስደን ከመጣላችን በፊት መከናወን ያለበት ተግባር የትኛው ነው?
   ሀ) በንፁህ የአመራረት ሂደት መጠቀም
   ለ) ሀብት እንዲያገግም ማድረግ
   ሐ) ማጨቅና ማጣራት
   መ) ሁሉም መልስ ናቸው

**፪. ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ ፍች ስጡ፡፡ አገባባዊ ፍች ለመስጠት የተጠቀማችሁበትን ዘዴም ግለጹ፡፡**

| ተ.ቁ | ቃል | ፍች | ተ.ቁ | ቃል | ፍች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተዝረክርኮ | | 6 | የተቀናጀ | |
| 2 | በማይጋለጡበት | | 7 | እንዲያገግም | |
| 3 | ሳቢያ | | 8 | ማጨቅ | |
| 4 | የአካባቢ እይታ | | 9 | የምናልመው | |
| 5 | ብክለት | | 10 | ፋይዳ | |

## ክፍል ሁለት፡- ጽሕፈት

**፩ ምሳሌውን መሰረት በማድረግ ቃላቱ በዓረፍተነገሩ ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ ፍች ጻፉ፡፡ አገባባዊ ፍቻቸውንም ከመዝገበ ቃላት ፍችዎቻቸው ጋር ልዩነት ያለውና የሌለው መሆኑን አነጻጽሩ፡፡**

***ምሳሌ*፡- የተዘራው ጤፍ <u>በቅሎ</u> ይታያል፡፡**

አገባባዊ ፍች - ቡቃያ ሆኖ፣

1. ጨቤዋ ከነአሮጌ <u>አፎቷ</u> ተሰቀለች፡፡
2. ብርድ፣ ፍርሐትና ድንጋጤ አሰፋን <u>ሰለቁት</u>፡፡
3. በጁ ገፋ ሲያደርገው፣ በሩ ሲከፈት <u>ተንሳጠጠ</u>፡፡
4. በረሃብ የተጠቃ ወገኑን <u>ለመታደግ</u> ቆርጦ ተነሳ፡፡
5. በጎቹን <u>ከጉረኖ</u> አውጥቶ እየነዳ ወደ ገበያ ሔደ፡፡

**፪. ባነበባችሁት ጽሑፍ (ቆሻሻና አወጋገዱ) ውስጥ በዋናነት የተነሱ ጉዳዮችን በጽሑፍ አቅርቡ፡፡**

**፫. የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ አባባሎች በራሣችሁ አባባል እንደገና ጻፉ፡፡**

1. ማንኛውም የቆሻሻ አይነት እኛንና አካባቢን ሊጐዳ ይችላል፡፡
2. ሁላችንም ብንሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቆሻሻ ስለምንፈጥር…
3. አነስተኛ ቦታ እንዲይዝ አድርጐ ማጨቅና ጉዳቱ እንዲቀንስ ማጣራት፣
4. በአግባቡ ተጠንቶ ወደተሠራ የቆሻሻ መጣያ ወስዶ መጣል፡፡

5. አፈርን ወይም ውሃን በማይበክልበት ቦታና ሰዎችም በዚሁ ሳቢያ ለአደጋ በማይጋለጡበት ሁኔታ ማስወገድ አለብን፡፡

## የቃላት መጥበቅና መላላት

በአማርኛ ቋንቋ አንዳንድ ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የተለያየ ፍች ይሰጣሉ፡፡ እንደነዚህ አይነት ቃላት በተናጠል ሲታዩ፣ የትኛውን ፍች እንደያዙ ወይም ጠብቀው ይሁን ላልተው እንደሚነበቡ ለመለየት ያስቸግራል፡፡ በዓረፍተነገር ውስጥ ሲገኙ ግን ይህንን ለመለየት ይቻላል፡፡ በአማርኛ ጠባቂ ድምፆች በአብዛኛው የሚገኙት በቃሉ መካከል ሲሆን አልፎ አልፎ በቃሉ መጨረሻ ላይም ይገኛሉ፡፡ በአማርኛ የቃል መጀመሪያ የሆነ ድምጽ አይጠብቅም፡፡

**፬. የሚከተለውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ የቀረቡት ቃላት በመጀመሪያ ጠብቀው፣ ቀጥሎም ላልተው ሲነበቡ (ሲባሉ) የሚሰጡትን ፍች ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በምትሠሯቸው ዓረፍተነገሮች አመልክቱ፡፡**

***ምሳሌ፡-*** *<u>በራ</u> - መብራቱ በአስራ ሁለት ሰዓት <u>በራ</u>፡፡*

*- ሙባረክ ራሱ <u>በራ</u> ስለሆነ፣ ኮፍያ ማድረግ ያዘወትራል፡፡*

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | አጣና | 6 | አያት |
| 2 | ዋና | 7 | ጠላት |
| 3 | አካፋ | 8 | አስ |
| 4 | አባይ | 9 | አዳኝ |
| 5 | አላት | 10 | ሰባ |

## አስረጅ(ገላጭ) ድርሰት

አስረጅ ድርሰት ከድርሰት ዓይነቶች አንዱ ነው። የአንድን ነገር ምንነት፣ አገኛኘት፣ ባህሪያት፣ ዓይነት፣ መጠን፣ ቅርጽ፣ አሠራር፣ ጠቀሜታ፣ ጉዳት ወዘተ፣ የሚያብራራ የድርሰት ዓይነት ነው። አንድን ተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሠራሽ ነገር አስመልክቶ ምንድን ነው? ምን ማለት ነው? የተሰራው ከምንድን ነው? እንዴት ተሠራ? እንዴት እንደዚህ ሊሆን ቻለ? ምን ጉዳት ወይም ጥቅም አለው? ወዘተ. በሚል ለሚቀርቡ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ለመስጠት የሚሞክር ድርሰት ነው።

**፭. ከላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ስለ አካባቢያችሁ የሚያስረዳ አንድ አስረጅ ድርሰት ጻፉና ለክፍላችሁ በንባብ አሰሙ። ለመጻፍ በቅድሚያ ርዕስ ምረጡ፤ በመረጣችሁት ርዕስ ዙሪያ ምን ምን ጉዳዮች ሲነሱ እንደሚችሉ አስተዋፅኦ ንደፉ። ከዚያም በነደፋችሁት አስተዋፅኦ መሠረት ድርሰታችሁን ጻፉ። የጻፋችሁትን ለጓደኞቻችሁ በማሣየት፣ ማሻሻያ ሃሳብ ተቀበሉና ድርሰታችሁን እንደገና ጻፉ።**

***ለክፍል ከማቅረባችሁ በፊት፡-***

- ድርሰታችሁ ከሰዋስው፣ ከስርዓተነጥብ፣ ከሀሳብ ፍሰት ወዘተ አንጻር ያሉበትን ችግሮች እየተወያያችሁ ማስተካከላችሁን አረጋግጡ።

**፮. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ።**

1. በአካባቢያችሁ ጽዳትን በተመለከተ የሚታዩ ችግሮችን በዝርዝር ጽፋችሁ አቅርቡ።
2. በአካባቢያችሁ የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት ምን መልክ እንዳለው የሚመለከታቸውን በማነጋገር ማስታወሻ ያዙና በራሳችሁ አባባል ጽፉችሁ ለክፍላችሁ አንብቡ።

፯. ያነበባችሁት ጽሑፍ (ምንባቡ) ምን ዓይነት ጽሑፍ ነው? መልሳችሁን በምክንያት አስደግፋችሁ ግለጹ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ንግግር

፩. የአካባቢ እንክብንቤን አለዚያም ሌሎች አካባቢያዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ የሚደረጉ ውይይቶችን፣ ማብራሪያዎችንና ገለጻዎችን፣ አዳምጣችሁ በማስታወሻ በመያዝ በራሳችሁ አባባል በጽሑፍ አዘጋጁ፡፡ በጽሑፍ ያዘጋጃችሁትንም ለክፍላችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

፪. በቀዳሚ ምዕራፎች ስለማስታወሻ አያያዝ የተማራችሁትን መነሻ በማድረግ፣ ከንግግር ማስታወሻ የሚይዝ ሰው ማድረግ ያለበትንና የሌለበትን ጉዳዮች በሰንጠረዥ አዘጋጁና በቃል አቅርቡ፡፡

*ምሳሌ፡-*

| ማድረግ ያለበት | ማድረግ የሌለበት |
| --- | --- |
| በጥሞና ማዳመጥ | እያዳመጡ ሌላ ሥራ መሥራት |

### ጭውውት

ጭውውት ሁለት ወይም ከዚህ በላይ የሆኑ ሰዎች እርስ በእርስ የሚያካሂዱት ውይይት ነው፡፡ በጭውውት አንዱ ከሌላው የችግሩን መፍቻ ሀሳብ ያገኝበታል፤ ልምድ ይጋራበታል፡፡ በጭውውት ጊዜ የእርስ በእርስ መደማመጥና መከባበር ይታያል፡፡ ጭውውት ቀልዶች የሚታከሉበትና ዘና ብሎ የሚካሄድ ነው፡፡

፫. በክፍላችሁ ውስጥ እንደ ፍላጎታችሁ በጥንድ በጥንድ ተሰባሰቡና በመረጣችሁት ጉዳይ ላይ ጭውውት አድርጉ፡፡ ስትጨርሱም ጭውውት ያደረጋችሁበትን ጉዳይና የጨበጣችሁትን ግንዛቤ ለክፍላችሁ አሳውቁ፡፡

፬. የተለያዩ ቡድኖችን በመመስረት፣ ከየቡድናችሁ ተከራካሪዎች ምረጡ፤ ከዚያም መምህራችሁ ከሚሰጧችሁ የመከራከሪያ ርዕሶች መካከል አንዱን በመውሰድ ቡድናችሁን ወክለው ለሚከራከሩት፣ የመከራከሪያ ሀሳቦች ስጧቸውና መመሪያን የተከተለ ክርክር አካሂዱ፡፡ በክርክሩ ሒደትም የቡድናችሁን አቋም የሚያንጸባርቅ የማዳበሪያ ሃሳብ ስጡ፡፡

**ለክርክሩ የሚከተሉትን ነጥቦች አስታውሱ**

- በቂ ዝግጅት ማድረግ፣
- ዳኞችን መምረጥ፣
- በርዕሱ ላይ ያተኮሩ ፍሬ ነገሮችን ብቻ መናገር፣
- ለተቃዋሚ ሀሳብ በማስረጃ የተደገፈ ትክክለኛ መልስ መስጠት፣

## ክፍል አራት፡- ሰዋስው

**፩. ቀጥሎ የቃል ክፍሎቻቸው የተገለጹ ቃላት ቀርበዋል፡፡ ቃላቱን በዓረፍተነገር ውስጥ በትክክለኛ ቦታቸው ተጠቅማችሁ አሳዩ፡፡ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመተራረም ዓረፍተነገሮቻችሁን አሻሽሉና አቅርቡ፡፡**

***ምሳሌ*** - ነገረኛ (ቅፅል) - ነገረኛ ሰው አይግጠማችሁ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | በሬ (ስም) | 6 | ፈጣን (ቅፅል) |
| 2. | ደግ (ቅፅል) | 7 | ቶሎ (ተውሳከ ግሥ) |
| 3. | ተጫወተ (ግሥ) | 8 | ወደ (መስተዋድድ) |
| 4. | ደን (ስም) | 9 | አሠረ (ግሥ) |
| 5. | ስለ (መስተዋድድ) | 10 | ክፉኛ (ተውሳከ ግሥ) |

**፪. በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ግሶች በምሳሌው መሰረት ለክፍት ቦታዎች በሚስማማ መልክ በመቀየር (ሌሎች ግሶች በመመስረት) ዓርፍተነገሮችን አሟሉ፡፡**

***ምሳሌ***፡- ህጻኑ ልጅ ልብሱን በእናቱ (አጠበ) ፡፡ መልስ፡- <u>አሳጠበ</u>

1. ህብረተሰቡ ወንጀለኛውን ለፖሊስ በመጠቆም (አሠረ) ____________፡፡
2. የስፖርት ልብሱን ለብሶ ዱብ ዱብ በማለት ሰውነቱን (አሞቀ)_____፡፡
3. ደረቅ እንጨት ሰበሰበና ክብሪት ተጠቅሞ፣ እሳቱን (አቃጠለ)_____፡፡
4. ሀገር ጎብኚው ያለ ፈቃድ አውሬ (ገደልኩ)____________ብሎ ተከራከረ፡፡
5. የቆሻሻ መጣያ ጉድጓድ በሠራተኛ (ቆፈርኩ)_________________፡፡

**፫. ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ጠብቀውና ሳልተው ሲነበቡ የተለያዩ ፍችዎች የሚሰጡ ቃላትን ሰብስቡና ፍችዎቻቸውን በዓረፍተነገር አሳዩ፡፡**

## ክፍል አምስት፡- ስነ-ጽሑፍ

**፩. ከሚከተሉት በአንደኛው ላይ የሚያተኩሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን አሰባስባችሁ አቅርቡ፡፡**

***ምሳሌ*:-** የመተባበርን አስፈላጊነት የሚያስተምሩ፣

- ድር ቢያብር አንበሳ ያስር፡፡
- አንድ  አይነድ ፣ አንድ አይፈርድ፡፡
- በአንድ እጅ አይጨበጨብም፡፡
- ሀምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ፣ ለሃምሳ ሰው ጌጡ ነው፡፡

1. ሰነፍን የሚወቅሱ ታታሪን የሚያሞግሱ፣
2. የችኮላን ጎጂነት፣ የማስተዋልን ጠቃሚነት የሚያመለክቱ፣
3. ጀግንነትን የሚያሞግሱ፣ ፈሪነትን የሚነቅፉ፣
4. አስነዋሪ ባህርያትን የሚቃወሙ፣ መልካም ስነ ምግባርን የሚደግፉ፣
5. የመጠንቀቅን አስፈላጊነት የሚመክሩ፣
6. ርህራሔንና ይቅርታ ማድረግን የሚያበረታቱ፣

# ማጠቃለያ

በምዕራፍ ሰባት ስር የቀረበው ትምህርት አካባቢን በሚያመለክቱ ጉዳዮች ላይ ሀሳብ መስጠትን፣ ከንግግርና ጽሑፍ ማስታወሻ መያዝን፣ መመሪያን ተከትሎ ክርክር ማካሔድን፣ ጭውውት ማድረግን፣ አስተዋጽኦ ነድፎ አስረጅ ድርሰት መጻፍን ያጠቃልላል፡፡

ክፍል አንድ አንብቦ ከመረዳት ጋር ቆሻሻ እንዴት እንደሚፈጠር፣ የሚያስከትለው ጉዳትና አራቱን የአያያዝ መንገዶች አይተናል፡፡ የተለያዩ ቃላትን አገባባዊ ፍችዎችም ተመልክተናል፡፡

በክፍል ሁለት ላይ ጠብቀውና ሳልተው ሲነበቡ የተለያዩ ፍችዎችን ስለሚሰጡ የአማርኛ ቃላት አንስተናል፡፡ እንደነዚህ አይነት ቃላት በተናጠል የትኛውን ፍቻቸውን እንደያዙ ለመለየት እንደማይቻል አስተውለናል፡፡ መልመጃዎችን ሠርተናል፡፡ አስረጅ ድርሰት የአንድን ነገር ምንነት፣ አይነት አሠራር፣ ባህርይ ወዘተ የሚያብራራ የድርሰት አይነት መሆኑንና ይህ ድርሰት አንድን ነገር፣ ምንድን ነው? ምን ማለት ነው? እንዴት ተገኘ ወዘተ. ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ እንደሚሰጥ ተብራርቷል፡፡ አስረጅ ድርሰትንም ሆነ ሌሎች የድርሰት ዓይነቶችን ለመጻፍ በቅድሚያ አስተዋጽኦ ማዘጋጀት አስፈላጊ እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡

በክፍል ሶስት ውይይቶችንና ገለጻዎችን ወዘተ. አዳምጦ ማስታወሻ በመያዝ በራስ አባባል በጽሑፍ ማዘጋጀትና በንግግር ማቅረብን ተለማምደናል፡፡ ጭውውት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች እርስ በእርስ የሚያካሔዱት ውይይት መሆኑንና አንዱ ከሌላው ሰው ሀሳብ የሚያገኝበት፣ ልምድ የሚጋራበት፣ በቀልዶችና ጨዋታዎች የታጀበ እንደሆነም ተመልክተናል፡፡ የክርክር ስርዓትን በመከተልም ተከራክረናል፡፡

በአራተኛው ክፍል፣ ስለ ቃል ክፍሎች አንስተናል፡፡ በየቃል ክፍሉ የተመደቡ ቃላትን በዐረፍተነገር ውስጥ ተጠቅመናል፡፡ ከግስ ግሶችን በመመስረትም በዐረፍተነገር ማስገባትን ተለማምደናል፡፡

በክፍል አምስት ላይም ምሳሌያዊ ንግግሮችን የሚመለከቱ መልመጃዎችን ሠርተናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. አካባቢያችሁን በተመለከተ የሚታዩ ችግሮችን ወይም በጎ ነገሮችን አስመልክቶ ምን ግንዘቤ እንደ ጨበጣችሁ ግለፁ፡፡
2. ከዚህ በታች የቀረቡት ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የሚሰጡትን ፍች በዐረፍተነገር ውስጥ አሳዩ፡፡
   ሀ) ይመራል
   ለ) እንሥራ
   ሐ) ቀና
   መ) ገና
   ሠ) መጋዝ
3. በዐረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ከየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመደቡ ግለጹ፡፡
   ሀ) አበበ ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡
   ለ) የተናደደ ሰው አደጋ ሊያደርስ ይችላል፡፡
   ሐ) ሐኪሙ ለሥራ ወደ ገጠር ሔደ፡፡
   መ) አውሮፕላኗ እየበረረች ሔደች፡፡
   ሠ) የችኮላ ሥራ አያስተማምንም፡፡
4. አንድን ድርሰት ለመጻፍ በቅድሚያ አስተዋፅኦ ማዘጋጀት ምን ጥቅም ያስገኛል?
5. አስረጅ ድርሰት ምላሽ የሚሰጣቸው ጥያቄዎች ምን ምን የሚሉ ናቸው?

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሰባት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘባችሁት የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል። በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመገንዘባችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✓)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተገነዘባችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | ✓ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ለቃላት አገባባዊና ቀጥተኛ ፍች ሰጥቻለሁ። | | | |
| 2. | ቃላት ጠብቀውና ሳልተው ሲነበቡ የተለያዩ ፍችዎች እንዳሏቸው ተገንዝቤያለሁ። | | | |
| 3. | ከግስ ግሶችን በመመስረት በዓረፍተነገር ውስጥ በትክክለኛ ቦታቸው ማስገባት እችላለሁ። | | | |
| 4. | አንብቤና አዳምጬ ዋና ዋና ሐሳቦችን በራሴ አባባል መጻፍ እችላለሁ። | | | |
| 5. | በመመሪያው ተመርቼ ክርክር ማካሄድ እችላለሁ። | | | |
| 6. | አስተዋፅኦ ነድፌ አስረጅ /ገላጭ/ ድርሰት መፃፍ እችላለሁ። | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(x) ምልክቶችን ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ።

# ምዕራፍ ስምንት

## መገናኛ ብዙሃን

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡- ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎትና ጠቀሜታን ትገልጻላችሁ፡፡
- በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ መልእክቶችን አዳምጣችሁ ትገልጻላችሁ፡፡
- በመሸጋገርያና አያያዥ ቃላት ተጠቅማችሁ ሐረጎችንና ዓረፍተነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡
- የአንቀፅ አጻጻፍ ሥርዓትን ተከትላችሁ ተገቢዎችን መሸጋገርያ ቃላት በመጠቀም አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- ከአካባቢያችሁና ከመገናኛ ብዙሃን የደስታ፣ የኀዘንና የሥራ ግጥሞችን ትሰበስባላችሁ፡፡
- ሥርዓት ጠብቃችሁ ትወያያላችሁ፤ ትጨዋወታላችሁ፡፡
- የሥራ ደብዳቤ ትጽፋላችሁ፡፡
- ከተለያዩ ጭውውቶችና ገለጻዎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በማስታወሻ ትይዛላችሁ፡፡

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. መገናኛ ብዙሃን ተብለው የሚጠቀሱት የትኞቹ ናቸው? ዘርዝሩ፡፡
፪. አዘውትራችሁ የምትከታተሉት የትኛውን መገናኛ ብዙሃን ነው? ለምን?
፫. መገናኛ ብዙሃን ባይኖሩ ምን የሚከሰት ይመስላችኋል?
፬. ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን መረጃ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው ምን ማድረግ አለበት ትላላችሁ?
፭. ርዕሱንና የመጀመሪያውን አንቀፅ አንብቡና ምንባቡ ስለምን ሊያወሳ እንደሚችል ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት ገምቱ፡፡

## "ለወሬ ሞትኩ ይበሉ"

ጧት ጧት ከመኝታዬ ተነስቼ ፊቴንና እጆቼን ታጥቤ ወደ ሳሎን እንደገባሁ ሬዲዮኔን ከፍቼ ዜና መስማት የቆየ ልማዴ ሆኗል፡፡ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥንን፣ እንዲሁም ሌሎች የሀገራችን ሬዲዮ ጣቢያዎችን፣ “ቢ.ቢ.ሲ.”ንም ሆነ “ቮይስ ኦፍ አሜሪካ”ን “ዶቸቬሌ”ንም ሆነ “ሬዲዮ ፍራንስ ኢንተርናሽናል”ን ወይም ሌላ ሬዲዮ ጣቢያ ስከፍት፣
"አሜሪካን አገር ውስጥ በከፍተኛ ፍጥነት የሚገሰግስ አውሎ ንፋስ ከባድ ጉዳት አደረሰ..."፤
“ጃፓን ከፍተኛ የሆነ የመሬት መንቀጥቀጥ ደረሰባት፤ የመሬት መንቀጥቀጡ ‘ሱናሚ’ም ያስከተለ ነበር”፤
"ሕንድ አገር ውስጥ የመሬት ነውጥ ተከስቶ ብዙ ሕዝብ አለቀ..."፤
"ቻይና ውስጥ በተወሰነ አካባቢ ርእደ መሬት ደረሰ፡፡"
የሚሉ እና ሌሎችም የተለያዩ ዜናዎች በየጊዜው አገኛለሁ፡፡ ለኔም ይሁን እንደኔ ላሉት እንዲህ ዓይነት ዜናዎችና ሌሎችም ምን ይረቡ ይሆን? የሰው ልጅ ሕይወት ተመሳሳይነት ስላለው ይሆን በሌሎች አገሮች የተከሰተውን ዜና ለመስማት ጉጉት የሚያድርብን? “ከዚህ ጋር ግንኙነት ያለው አደጋ ወይም ጉዳት በኔም አገር ሊከሰት ይችላል” በሚል ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ፍራቻ የዓለምን ዜና የምንከታተል ይመስለኛል፡፡

በተጠቀሰውም ምክንያት ይሁን ወይም በሌላ ተመሳሳይ ምክንያት፣ እኔ ብቻ ሳልሆን የመላው ዓለም ሕዝብ፣ ወሬ ፍለጋ በነጋ በጠባ ሬዲዮ እንደሚጎረጉር፣ ቴሌቪዥን እንደሚከፍት፣ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ገዝቶ እደሚያነብ አውቃለሁ፡፡ የሰው ልጅ የማወቅ ፍላጎት ባይኖረው ሬዲዮና ቴሌቪዥን መች በተፈጠሩ ነበር! ጋዜጠኝነትስ መች በተጀመረ ነበር!

ስለ ሰው ልጅ የማወቅ ፍላጎት ሳነሳ፣ አንዲት ሴት ወይዘሮ ትዝ ይሉኛል፡፡ እኚህ የመሥሪያ ቤት ባልደረባዬ ቀልደኛ ቢጤ ነበሩ፡፡ ሁለታችንም እየተከባበርን የምንጠራራው በአንቱታ ነበር፡፡

ታዲያ! እኚህ ቀልደኛ ሴት ወይዘሮ አልፎ አልፎ ቢሮዬ ድረስ ይመጡና እየሳቁ፣ "ለወሬ ሞትኩ ይበሉ... የምነግርዎት አለኝ" ይሉኛል፡፡

እኔም ፈገግ ብዬ፣ "የሚነግሩኝ ካለዎት እንዲሁ ይንገሩኝ እንጂ፣ እኔስ 'ለወሬ ሞትኩ' አልልም እላቸዋለሁ"፡፡ ወሬያችንን እንዲህ በሳቅ ከጀመርን በኋላ፣ አንዳንድ አዳዲስ የሰሙትን ነገር አውግተውኝ፣ እኔም ስለ አጫወቱኝ ነገር አመስግኛቸው እሳቸውም ወደ ቢሮአቸው ይመለሳሉ፡፡

እንደጥንቱ አባባል እንኳ፣ "ለወሬ የለውም ፍሬ" ይባል ነበር፤ ነገር ግን ይህ አባባል በዛሬው ዘመን ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ይልቁንስ በዘመናችን የተለያዩ ወሬዎች መረጃዎች ስለሆኑ፣ "ያለመረጃ፣ያለወሬ መኖር የለም ዛሬ!" ቢባል ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

በኢትዮጵያ በ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ዮናታን ዲምብልቢ የተባለው ዜና አቅራቢ፣ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ወሎ ውስጥ በድርቅ ምክንያት እንደ ቅጠል ሲረግፉ የነበሩትን አዛውንቶች፣ ጎልማሶች፣ ወጣቶችና፣ ሕጻናትን ፊልም አንስቶ ተደብቆ የነበረውን የረሃብ ዜና ይፋ ባያወጣው ኖሮ፣ የ፲፱፻፷፮ የኢትዮጵያ አብዮት ይከሰት ነበር ብሎ መገመት አይቻልም፡፡ በእርግጥ ለአብዮቱ መቀጣጠል ሌሎች በርካታ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ "ለወሬ የለውም ፍሬ" የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ጊዜ ያለፈበት መሆኑን የሚያስረዳን፣ ይህ የተጠቀሰው ሌሎች እርምጃዎችን ያስከተለ ዜና ነው፡፡

በየጊዜው ዜናዎችን አዘጋጅተው በመገናኛ ብዙሃን የሚያሰራጩት ጋዜጠኞች ስለሆኑ፣ ጋዜጠኛ እና ዜና የተዛመዱ ናቸው። እንዲያውም ጋዜጠኛ ካለ ዜና አለ፤ ዜና ካለ ጋዜጠኛ አለ ማለት ይቻላል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ጋዜጠኝነት የተጀመረው በአፄ ሚኒልክ ዘመነ መንግሥት እንደሆነ ይነገራል። ከዚያ በፊት በኢትዮጵያ የጋዜጠኝነት ሙያ አይታወቅም ነበር። በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት ሙያው ተስፋፍቶ የሬዲዮና የቴሌቪዥን አገልግሎቶች ታከሉበት። በኢትዮጵያ እስከደርግ ዘመን የነበረው ጋዜጠኝነት ሙሉ በሙሉ መንግሥታዊ ነበር ለማለት ይቻላል።

የግል ጋዜጠኝነት በሰፊው ሊታይ የቻለው፣ ከ፲፱፻፹፫ ዓ.ም ወዲህ፣ በተለይም የፕሬስ ነጻነት ከታወጀበት ከ፲፱፻፹፬ ዓ.ም ጀምሮ ነው። ከፕሬስ ነፃነት አዋጅ በኋላ፣ በየዕለቱም ባይሆን በየሳምንቱና በየወሩ አዳዲስ ጋዜጦችና መጽሔቶች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። በአንድ ወቅት የግል ጋዜጦችና መጽሔቶች በብዛት ይታተሙ ስለነበር፣ "እንደ አሸን ፈሉ!" ተብሎ ነበር። ብዙዎች በግል ይታተሙ የነበሩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ግን ዘላቂነት አልታየባቸውም።

*(ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም፣ 1992፣102-104 ለማስተማርያነት እንዲያገለግል መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተዘጋጀ)።*

## ክፍል አንድ፡- ንባብ

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ አብራርታችሁ መልሱ።**

1. ሰዎች፣ በዓለም ውስጥ የተለያዩ የሬዲዮ ጣቢያዎችን፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን እና የሚታተሙ ጋዜጦችና መጽሔቶችን ከመከታተል እና ከማንበብ ምን ያገኛሉ?
2. “ለወሬ ሞትኩ ይበሉ” የሚለው አባባል ምን ማለት ነው?
3. "ለወሬ ሞትኩ ይበሉ" እና "ለወሬ ሞትኩ ለሥራ ሰነፍኩ" ሁለቱ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ይለያያሉ? እንዴት?

4. በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ እንግሊዛዊው ጋዜጠኛ ዮናታን ዲምብልቢ እንዴት ሊጠቀስ ቻለ?
5. ዜና እና ጋዜጠኝነት ወይም ጋዜጠኝነትና ዜና ምን ግንኙነት እንዳላቸው ግለጹ።
6. በኢትዮጵያ የጋዜጠኝነት ሙያ የተጀመረው በማን ዘመነ መንግሥት ነው?
7. የግል ጋዜጠኝነት ከመንግሥት ጋዜጠኝነት በምን ይለያል?
8. በኢትዮጵያ የግል ጋዜጠኝነት መቼ ተጀመረ?
9. በኢትዮጵያ፣ የግል ጋዜጠኝነት እንዲጀመር ምክንያት የሆነው ምን ይመስላችኋል?

**፪. ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጎች በምንባቡ ውስጥ የያዙትን ፍች የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮች መስርቱና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።**

ሀ) ዓለም አቀፍ
ለ) ሬዲዮ መጎርጎር
ሐ) "አንቱታ"
መ) ማውጋት
ሠ) እንደቅጠል ሲረግፍ
ረ) ይፋ ማውጣት
ሰ) መቀጣጠል
ሸ) እንደአሸን ፈሉ

## ክፍል ሁለት፡- ጽሕፈት

**፩. በሚቀጥለው ታሪክ ውስጥ ቃልን ከቃል፣ ዓረፍተነገርን ከዓረፍተነገር፣አንቀጽን ከአንቀጽ ያያያዙ  መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትን ጥንድ ሆናችሁ ለዩ።**

“በአሥራ ስምንተኛው ምዕተ-ዓመት አጋማሽ ገደማ፣ የሱዳን ጦር ምዕራባዊውን የኢትዮጵያን ድንበር እያለፈ ዘረፋ በማካሄድ የአካባቢውን ሕዝብ በጣም ያስቸግር ነበር። ከዚህም የተነሣ፣ የወገን ጦር (የኢትዮጵያ ጦር) ከጎንደር በመንቀሳቀስ፣ በሀገሩ ላይ የተቃጣውን ሕገ ወጥ ድርጊት

ለመበቀል ወደ ሰነዓር (በነጭና በጥቁር ዓባይ መካከል በሚገኘው ቦታ) ዘምቶ ተዋግቷል፡፡ በዚህ ወቅት፣ የሀገራቸውን ክብርና የወገናቸውን ደህንነት ለማስከበር ከዘመቱት ሰዎች ጋር ፈረሶችም ይገኙባቸዋል፡፡ ከጌቶቻቸው ጋር ከዘመቱት ፈረሶች መካከልም ሱቤ ወይም ዞብል በመባል ይታወቅ የነበረው ፈረስ ይገኝበታል፡፡ ሱቤ ወይም ዞብል በዚህ ዘመቻ ከጌታው ጋር እንዳለ በጠላት እጅ ወደቀ ወይም ተማረከ፡፡ ሱቤ ወይም ዞብል ከጌታው ጋር ሲማረክ ቆስሎ ወይም ማምለጥ ተስኖትም አልነበረም፤ ነገር ግን ጌታው ሲማረክ ጌታውን ጥሎ ለመሄድ አልፈለገም፡፡”

"ታዲያ የሱዳን ወታደሮች ሱቤ (ዞብል)ን ሲያዩ በግዝፈቱ፣ በግርማ ሞገሱና በውበቱ ስለተማረኩ ከሌሎች ምርኮኛ ፈረሶች ነጥለው ለሰንዓር ንጉሥ ገጸበረከት አቀረቡለት፡፡ በዚህ ጊዜ ንጉሡና የንጉሡ ወታደሮች ዓይኖቻቸውን በዞብል (ሱቤ) ላይ ሰቅለው ውበቱን ማድነቅ ጀመሩ፡፡ በተለይ በሱቤ(በዞብል) ውበት የተደነቀው ንጉሥ በወቅቱ የአገሩ ጦር ድል ለማድረግ የበቃበትን ሁኔታ ማወደስና የድሉን ደስታ ምክንያት በማድረግ ወታደሮቹን ግብር ማስገባት ነበረበት፡፡ሆኖም በፈረሱ ላይ ባደረበት አድናቆት የተነሳ ማድረግ የሚገባዉን ሁሉ ረስቶት ነበር፡፡”

*(ጌታቸው ክብረሥላሴ፣1997፣70)*

**፪. በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ዙርያ አንቀጽ መጻፍ የሚያስችሉ አንዳንድ መንደርደሪያ ዓረፍተነገሮችን ጻፉና አንዱን በመምረጥ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡**

1. በትምህርት ቀናት የአሥራአምስት ደቂቃ የእረፍት ጊዜዬ፤
2. የትምህርት ቤታችን ትንሿ የሬዲዮ መገናኛ (“ሚኒሚዲያ”) አገልግሎት፤
3. አካል ጉዳተኝነትና ሥራ፤
4. የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ጠቀሜታ፤
5. የትምህርት ቤታችን የአካባቢ ጥበቃ ክበብ፤

**፫. የሚከተለውን ጽሑፍ በማንበብ ማስታወሻ ከያዛችሁ በኋላ አሳጥራችሁ አቅርቡ፡፡ (ማስታወሻ አያያዝን በተመለከተ በምዕራፍ አንድ የተማራችሁትን አስታውሱ)**

“በወንጂ ከሸንኮራገዳ እርሻ በሰንሰለት ታስሮ፣ በጋሪ ተጭኖ የመጣው ሸንኮራገዳ ተመዝኖ መጠኑ ከታወቀ በኋላ ሰንሰለቱ ተፈትቶለት ወደ መሸረካከቻ ቦታ ይቀርባል፡፡ አገዳው ከተሸረካከተም በኋላ በመዳመጫው ወፍጮ ጥርስ ይገባል፡፡ ወፍጮው አገዳውን ፈጭቶ ወለላውን ከገለባው ይለየዋል፡፡”

“ወፍጮ ውስጥ ገብቶ የነበረው አረንጓዴ ሸንኮራገዳ ፈሳሽ ወለላ ሆኖ ከወፍጮው በሚወጣበት ጊዜ መልኩን ቀይሮ ቢጫ ይሆናል፡፡”

“ቢጫው ወለላ እንደመረብ በተተበተቡ ቧንቧዎች ውስጥ አልፎ ግዙፍ ወደሆኑ የብረት ጋኖች ተጋብቶ ይቆያል፡፡ ቀጥሎ ያለውን ሥራ የሚያከናውኑ ሌሎች ባለሙያዎች አሉ፡፡ እነዚህም የቅመማ ክፍል ሠራተኞች ወይም ‹ኬሚስቶች› ተብለው ይጠራሉ፡፡ የቀማሚዎች ወይም የ “ኬሚስቶች” ዋነኛ ሥራ ፈሳሹ ወለላ ንፅሕናውን እንዲጠብቅ ማድረግ ነው፡፡”

"… የቅመማ ባለሙያዎች ከወለላው ናሙና እየወሰዱ በቤተ ሙከራቸው ይመረምሩታል፡፡ ፈሳሹም ውስጥ ድኝና ኖራ በመጨመር ከማንኛውም ጉድፍ እንዲጣራ ያደርጉታል፡፡"

"… ቀጥሎ ፈሳሹ ወደ ጠጣርነት መለወጥ ስላለበት ውሃው ፈልቶ በትነት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ ወለላው ወደ ጠጣርነት በሚለወጥበት ክፍል ረጅም ጊዜ ከቆየ ስኳሩ ግርድፍ ይሆናል፡፡ ለአጭር ጊዜ ብቻ ከቆየ ግን ደቃቅ ይሆናል፡፡ የአንኳሩ መጠን አንደ ተፈላጊነቱ ይሆናል ማለት ነው፡፡"

"…. ስኳር ግርድፍም ይሁን ደቃቅ መልኩ አንደበረዶ የነጣ ነው፡፡ ስኳሩ ወደንጣት ከመለወጡ በፊት በሶስት ዓይነት የቀለም ለውጥ ደረጃ ያልፋል፡፡ በሸንኮራገዳነት እያለ መልኩ አረንጓዴ፣ አልፎ አልፎ ደግሞ ቡናማ ነው፡፡ ቀጥሎ ሸንኮራገዳው ፋብሪካ ውስጥ ሲገባ ቀለሙ ወደ ቢጫ ወለላነት ይለወጣል፡፡ በመጨረሻም በፋብሪካው ውስጥ ወደ ስኳርነት ሲለወጥ መልኩ ነጭ ይሆናል፡፡ ቡናማ ስኳር ሲያስፈልግ ቡናማ ቀለም እንዲይዝ ይደረጋል፡፡"

" ከዚህ በኋላ ለገበያ እስኪቀርብ ስኳሩ በመቶና በሃምሳ ኪሎ ጆንያ ውስጥ ገብቶ ወደማከመቻ አዳራሽ ተወስዶ ከዚያ ያቆያል፡፡

*(ሣህለሥላሴ ብርሃነማርያም፤ 1992:75-83)*

**፬. ከሚከተሉት ክበቦች ውስጥ የአንዱን ክበብ የሥራ አፈጻጸም በሚመለከት፣ የተካሄዱ ተግባራትንና ሳይካሄዱ የቀሩ ተግባራትን የሚገልጽ ሐሳብን የያዘ ደብዳቤ የትምህርት ቤታችሁን አድራሻ በመጠቀም ጻፉ፡፡ የጻፋችሁትን ደብዳቤ ለጓደኞቻችሁ አሳዩና በሚሰጧችሁ አስተያየት እንደገና አሻሽሉ፡፡**

1. የሥነጽሑፍ ክበብ
2. የተውኔት ክበብ
3. የ"ኤች. አይ. ቪ. ኤድስ" ክበብ
4. የበጎ አድራጎት ክበብ
5. የሥነዜጋ ክበብ፣ ወዘተ.

## ክፍል ሦስት፡- ንግግር

**፩.ከሚከተሉት ርዕሶች መካከል አንደኛውን በመምረጥ እና አስፈላጊውን መረጃ በማዘጋጀት ተወያዩ፡፡**

ሀ) የውሃ ቀን
ለ) የሴቶች ቀን
ሐ) የስደተኞች ቀን
መ) የአዛውንቶች ቀን

**፪. ከመገናኛ አውታሮች ባገኛችኋቸው ወቅታዊ ጉዳዮች(ኤች አይ ቪ፣ ሙስና፣ የጾታ እኩልነት፣ ወዘተ.) ላይ በቡድን ሆናችሁ ተጨዋወቱ፡፡**

፫. መገናኛ ብዙሃን ባይኖሩ በዓለም ላይ ምን ይፈጠር ነበር ትላላችሁ? በቡድን ሆናችሁ ተወያዩና በጋራ ውይይት ድምዳሜ ላይ ድረሱ፡፡

፬. የሸንኮራገዳ ተክል እንዴት እንደሚመረትና በፋብሪካ ውስጥ ወደ ስኳር ምርትነት እንዴት እንደሚለወጥ በማስታወሻችሁ ላይ ተመሥርታችሁ ለጓደኞቻችሁ ገለጻ አድርጉ፡፡

## ክፍል አራት፡- ሰዋስው

፩. ከሚከተሉት ቃላት አምስቱን ምረጡና ስማዊ ሐረጎችን መሥርቱ፤ ከዚያም ዓረፍተነገር ሥሩባቸዉ፡፡

***ምሳሌ፣***

| • ረጅም ገመድ፣ | • የእግር መንገድ፣ | • የፈተና ወረቀት፣ |
|---|---|---|
| • ረጅም | • መንገድ | • ወረቀት |
| • ትልቅ | • ሰው | • አካፋ |
| • ቀይ | • ቤት | • ብዕር |
| • አዲስ | • ሹራብ | • መጽሐፍ |
| • ሰባራ | • ምጣድ | |

፪. በሚከተሉት ቃላት አምስት ቅጽላዊ ሐረጎችን በመመስረት ዓረፍተነገር ሥሩባቸውና ለጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

***ምሳሌ፣***

| • የልጅ አዋቂ | • የሕፃን ብልጥ | • የተማሪ ብልህ |
|---|---|---|
| • አዋቂ | • ብልህ | • ደግ |
| • አዋኪ | • የልጅ | • የተማሪ |
| • ብልጥ | • የሕፃን | • ቁም ነገረኛ |
| • የወጣት | | |

## ዓረፍተነገር

ዓረፍተነገር ከስማዊ ሐረግና ከግሳዊ ሐረግ ይመሠረታል፡፡ ስማዊ ሐረግ የዓረፍተነገር የባለቤት ክፍልን የሚያመለክት ሲሆን፣ ግሳዊ ሐረግ ደግሞ የዓረፍተነገር የማሰሪያ አንቀጽ ክፍልን ያመለክታል፡፡

**ምሳሌ**፣ ሰዓት አሳልፎ የመጣው ልጅ፣ የመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ትምህርት አመለጠው፡፡

በቀረበው ዓረፍተነገር ውስጥ "ሰዓት አሳልፎ የመጣው ልጅ" ስማዊ ሐረግ ሲሆን፣ የዓረፍተነገሩ የባለቤት ክፍል ነው፡፡

".. የመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ትምህርት አመለጠው" የሚለው ግሳዊ ሐረግ ሲሆን፣ የዓረፍተነገሩ የማሠሪያ አንቀጽ ክፍል ነው፡፡

የዓረፍተነገር ዓይነቶች ሁለት ናቸው፤ ተራ እና ውስብስብ ዓረፍተነገር ይባላሉ። ተራ ዓረፍተነገር ከአንድ ማሠሪያ አንቀጽ ብቻ ሊመሠረት የሚችል ሲሆን ውስብስብ ዓረፍተነገር ደግሞ ከሁለት እና ከሁለት በላይ ማሰሪያ አንቀጾች(ግስ ከሆኑ ቃሎች) ይመሠረታል፡፡

**ምሳሌ**፣ ሀ. አርሴማዊት ብቻዋን አንድ ሊትር ወተት ጠጣች፡፡

በቀረበው ዓረፍተነገር ውስጥ ያለው ማሰሪያ አንቀጽ አንድ ብቻ ("ጠጣች") በመሆኑ ዓረፍተነገሩ ተራ ዓረፍተነገር ይባላል፡፡

ለ. ዘርትሁን የክፍል ጓደኞቿን ሰብስባ ችግሯን አወያየቻቸው፡፡

በ"ለ" በቀረበው ዓረፍተነገር ውስጥ ሁለት ማሰሪያ አንቀጾች ወይም ግሶች (ሰብስባ እና አወያየቻቸው) ስላሉ ውስብስብ ዓረፍተነገር ነው፡፡ ዓረፍተነገር "ለ"ን ለሁለት መክፈል ይቻላል፡፡

ዘርትሁን የክፍል ጓደኞቿን ሰበሰበች፡፡

ዘርትሁን ለክፍል ጓደኞቿ ችግሯን አወያየቻቸው፡፡

**፫. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች እያንዳንዳቸውን በስማዊ ሐረግና በግሳዊ ሐረግ ከፍላችሁ በሰንጠረዡ በማቅረብ፣ ዓረፍተነገሮችን በስማዊ ሐረግና በግሳዊ ሐረግ ለመክፈል ምክንያት የሆናችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርባችሁ ተነጋገሩበት፡፡**

***ምሳሌ፣*** *ትናንት የመጣችው ተማሪ በኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ከፍተኛ ውጤት አመጣች፡፡*

| ስማዊ ሐረግ | ግሳዊ ሐረግ |
|---|---|
| ትናንት የመጣችው ተማሪ | በኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ከፍተኛ ውጤት አመጣች፡፡ |

1. ሁለት መሉ ልብስ እንድታሰፋ ጓደኛዋ ገንዘብ ሰጣት፡፡
2. ቁርሳቸውን በልተው በጥዋት ወደ ትምህርት ቤት የመጡት ተማሪዎች የቅርጫት ኳስ ይጫወታሉ፡፡
3. ጓደኞቻችን ጥዋት ጥዋት ተነስተው ስፖርት ስለሚሠሩ ቀልጣፎች ናቸው፡፡
4. ታናሽ እህቴ ከቤተሰባችን ሁሉ የተለየች ባለሙያ ናት፡፡
5. ንጽሕናው ያልተጠበቀ ምግብ የበላው ተማሪ ታመመ፡፡

**፬. ከሚከተሉት ዓርፍተነገሮች ውስጥ ተራ እና ውስብስብ የሆኑትን በመለየት "ተራ" እና "ውስብስብ" ያላችሁባቸውን ምክንያቶች ለይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

1. ልጁ ዛሬ ጥዋት ብዙ ጥያቄዎች አቀረበልኝ፡፡
2. ጨዋታውን ፊት ለፊት በማየቴ ደስ አለኝ፡፡
3. ግርማ ሆስፒታል ሄዶ ወንድሙን ጠየቀ፡፡
4. መኪና እንዳይገጫት ስለፈራች መንገዱን ተሻግራ ሄዳ ዶሮ ለመግዛት አልፈለገችም፡፡
5. እንግዳው ሰውዬ ዛሬ ጥዋት ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡

## ክፍል አምስት:- ስነጽሑፍ

### የሥነቃል አሰባሰብ

የዘፈንና የኃዘን ግጥሞች ከየት ይሰበሰባሉ? ከተለያዩ ቦታዎች (ሁኔታዎች) ሊሰበሰቡ ይችላሉ፡፡ እንደዚህ ያሉ ግጥሞች ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች፣ ከመጽሔቶች፣ ወዘተ ይሰበሰባሉ፡፡ እነዚህን በጥናት ውስጥም ማግኘት ይቻላል፡፡

የዘፈንና የኃዘን ግጥሞች ከመስክም ሊሰበሰቡ ይችላሉ፡፡ ከመስክ ይሰበሰባሉ ሲባል ከመንደር፣ ከቀበሌ (ከተለያዩ ሰዎች) ወዘተ ይሰበሰባሉ ማለት ነው፡፡ እንዴት ይሰበሰባሉ? ከሰነዶች የሚሰበሰቡት፣ እያነበቡ ማስታወሻ በመያዝ ይሆናል፡፡ ከመስክ የሚሰበሰቡት ግን በቃለ መጠይቅ ሊሆን ይችላል፡፡ የሚቀርበው ቃለ መጠይቅ ግን ደረቅ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የሚቀርበው ቃለ መጠይቅ ጥሩ የመግባባት ችሎታ ያለበት ጭውውታዊ ቃለ መጠይቅ ቢሆን ተመራጭ ነው፤ የተፈለገውን መረጃ ለማግኘት ያስችላልና፡፡

*(ፈቃደ አዘዘ፣1991፣117-122 ከቀረበው ላይ ለደረጃው እንዲያመች ሆኖ የተዘጋጀ)*

**፩. በቡድን ሆናችሁ ከተለያዩ የልቦለድ መጻሕፍት፣ ከጋዜጦች፣ ከመጽሔቶች፣ ወዘተ የተለያዩ የዘፈን የኀዘን እና የሥራ ግጥሞች ሰብስቡ። በዓይነታቸው (የዘፈን፣ የኀዘን፣ የሥራ...)ከፍላችሁ ይዘታቸውን የሚመለከት መግለጫ ከሰጣችሁ በኋላ፣ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡**

## ማጠቃለያ

የመገናኛ ብዙሃን አገልግሎት በጣም ሰፊ ነው፤ የተሻለ አኗኗርን ለመከተል፣ ራስን ከአደጋ ለመጠበቅ፣ ወዘተ. ከመገናኛ ብዙሃን ብዙ መረጃ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ከመገናኛ ብዙሃን የሚገኙ መረጃዎች ለኑሮ በጣም አስፈላጊ ናቸው፡፡ ያለ መገናኛ ብዙሃን መኖር ያስቸግራል፡፡ ስለዚህ ስለመገናኛ ብዙሃን በሰፊው ማጥናት ያስፈልጋል፡፡

ቋንቋ በድምጸ-ልሳናት፣ በቃላት፣ በሐረጋት እና በዓረፍተነገሮች ይገለጻል፡፡ ስለዚህ ሀሳብን፣ በንግግር ሆነ በጽሑፍ ለመቀበል እና ሀሳብን በሁለቱም ለሌላው ሰው ለመግለጽ የሐረጋትና የዓረፍተነገሮችን የአወቃቀር ሥርዓት ማጥናት ተገቢ ነው፡፡ ሀሳብ በጽሑፍ ሲገለጽ የራሱ ሥርዓት አለው፡፡ በጽሑፍ የሚገለጽ ሀሳብ አንቀጽን መሳሪያ ያደርጋል፤ አንቀጽ ደግሞ የራሱ የግንባታ ሥርዓት ይኖረዋል፡፡ በተለያዩ አንቀጾች በሚገለጽ አንድ ርዕስ ውስጥ የመሸጋገሪያ ቃሎችን መጠቀም ይገባል፡፡

የዘፈንና የኀዘን ግጥሞች መሰብሰብና ማጥናት የህብረተሰቡን ባህል፣ ወግና ሥርዓት ለማጥናት አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ የማህበረሰብን ባህላዊ ጉዳዮች ለመረዳት እነዚህን የመሰሉ ሥነ ቃሎችን በመሰብሰብ እና መግለጫ በመስጠት መጨዋወትና መወያየት ያስፈልጋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የመገናኛ ብዙሃንን የተለያዩ አገልግሎቶች መዝግቡና ለጓደኞቻችሁ አሳዩ፡፡
2. በተለያዩ የኀዘን አጋጣሚዎች የተቀነባበሩ የኀዘን ግጥሞች፣ አገልግሎታቸው ምን እንደሆነ ግለጹ፡፡
3. የተለያዩ ክብረ-በዓላትን መዝግቡና የምታስታውሷቸውንና በእነዚህ ክብረበዓላት የሚዘፈኑ  ግጥሞች ጻፉ፡፡
4. ዓረፍተነገር በዋናነት ከምንና ከምን ይመሠረታል?
5. ስነቃል የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስምንት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘባችሁት የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመገንዘባችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✓)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተገነዘባችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የመገናኛ ብዙሃንን አገልግሎት (ጠቀሜታ) እገልጻለሁ፡፡ | | | |
| 2. | የተለያዩ መገናኛ ብዙሃንን መልእክቶች መግለፅ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 3. | በመሸጋገርያና አያያዥ ቃላት ተጠቅሜ ሐረጎችንና ዓረፍተነገሮችን መመስረት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 4. | ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ መረጃዎች በማስታወሻ እንዴት እንደሚያዙ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 5. | የአንቀጽ አጻጻፍ ሥርዓትን ጠብቄ፣ ተገቢዎቹን መሸጋገርያና አያያዥ ቃላትን ተጠቅሜ፣ አንቀጽ መጻፍ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 6. | ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃንና ከአካባቢዬ የአሰባሰብ ሥርዓቱን ጠብቄ የዘፈን፣ የኃዘንና የሥራ ግጥሞችን መሰብሰብ ችያለሁ | | | |
| 7. | ከተለያዩ ጭውውቶች፣ ውይይቶችና ገለጻዎች የሚተላለፉ ቁምነገሮችን በማስታወሻ መያዝ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 8. | በውይይት ወቅት የውይይትን ሥርዓት መጠበቅ እንደሚገባ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 9. | የአጻጻፍ ስርአቱን ጠብቄ የሥራ ደብዳቤ መፃፍ እችላለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(x) ምልክቶች ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ምርጥ ንግግር

**የምዕራፉ ዓላማዎች:- ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- የምርጥ ንግግር መለያዎችን ዘርዝራችሁ ታቀርባላችሁ።
- በተለያዩ ርእሶች ላይ ተዘጋጅታችሁ የንግግርን ሥርዓት ጠብቃችሁ ትናገራላችሁ።
- የተወሰኑ መረጃዎችን በማስታወሻ ይዛችሁ በቃል በማጥናት ንግግር ታደርጋላችሁ።
- ከዓረፍተነገር ውስጥ የቃላት ክፍሎችን ተግባር ታመለክታላችሁ።
- የእርባታ መሥራች ምዕላዶችን ሙያ ትለያላችሁ።
- ሀሳባችሁን በጽሑፍ ስትገልጹ ሥርዓተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታቸው ታስገባላችሁ።
- ከተለያዩ ንግግሮች ውስጥ ምሳሌያዊ እና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ለይታችሁ ፍቻቸውን ትሰጣላችሁ።
- ከተለያዩ ንግግሮች ውስጥ የሚገኙትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ያላቸውን ቃላት ለይታችሁ ፍቻቸውን ታቀርባላችሁ።
- የተወሰኑ ቅኔዎችን ኅብረቃል ለይታችሁ ሰምና ወርቃቸውን ትፈታላችሁ።

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. የምርጥ ተናጋሪ ጥበብ እንዴት ያለ ነው?
፪. ስለ ጥንት የግሪክ ሥልጣኔ አንብባችሁ ወይም ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
፫. ጥሩ ተናጋሪ መሆን እንዴት ያሉ ጥቅሞች አሉት?
፬. አንድ ንግግር የአድማጩን ቀልብ ሊስብ ወይም ላይስብ የሚችልባቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

# ዴሞስቴን፣ የምርጥ ንግግር አባት!

ዛሬ፣ የዓለም ሥልጣኔ በደረሰበት ደረጃ፣ የሕዝብ መሪዎች የመንግሥት መማክርት በሚገኙበት ጉባኤ፣ ወይም ሕዝብ በተሰበሰበበት ሸንጎ አን ደበተ-ርቱዕ በመሆን የደጋፊዎቻቸውን መንፈስ በንግግራቸው እየቀሰቀሱ ልባቸውን ለመማረክ ብርቱ ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ፡፡ ይህ ጥረታቸው የሰመረ የሚሆነውም የጥሩ ንግግር ስጦታና ችሎታ ባለቤቶች ሆነው ሲገኙ ነው፡፡ የጥሩ ተናጋሪነት ችሎታን እንደሌሎቹ ጥበቦች ሁሉ በትምህርት ቤት ውስጥ ባላሰለሰ ልምምድ ማፍራት ይቻላል፡፡ ለመሆኑ በግሪክ ሥልጣኔ ውስጥ ንግግር እንዴት ያለ መድረክ ነበረው?

በግሪክ የቀድሞ ሥልጣኔ ውስጥ፣ ንግግር እንዴት ያለ ተቀባይነት እንደነ በረው ለማውሳት ግሪካዊውን ዴሞስቴንን ማስታወስ የግድ ይላል፡፡ ዴሞስቴን፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ፫፻፹፬ ተወለደ፤ በ፫፻፳፪ ሞተ፡፡ የዴሞስቴን ታሪክ የንግግር ጥበብ ለማስተማር ስለሚያስችል፣ ለምን ተናጋሪ ለመሆን እንደፈለገና እንዴት ጥሩ ተናጋሪ መሆን እንደቻለ በተከታዩ ታሪኩ እንመለከታለን፡፡

ዴሞስቴን በሕጻንነቱ አባቱ ሞቱበት፤ በዚህም ምክንያት ባለአደራዎች ሆነው የአባቱን ገንዘብ የተረከቡት ሰዎች ገንዘቡን አባከኑበት፡፡ ለአቅመ አዳም ሲበቃ፣ ከአባቱ በአደራ የተቀበሉትን ገንዘብ ያባከኑበትን ሰዎች ከሶ የአባቱን ሀብት ለማስመለስ ያስብ ነበር፡፡ አንድ ቀን፣ የዴሞስቴን

አስተማሪዎች በዘመኑ ንግግር አዋቂ በመሆን ይመሰገን የነበረውን ክሊስትራት የሚባለውን ሰው ሲናገር ለመስማት ወደ ሸንጎ ሲሄዱ፣ ዴሞስቴንም ከነርሱ ጋር ንግግሩን እንዲያዳምጥ አስከተሉት፡፡

ዴሞስቴን ክሊስትራት የሚባለውን ሰው ንግግር በመስማትና በሸንጎ ላይ በነበሩ ሰዎች ዘንድ ምን ያህል እንደተደነቀ በማስተዋል፣ ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን ብርቱ ስሜት በውስጡ አደረ፡፡ እንዲያውም ዴሞስቴን ወደ ንግግር ጥበብ የተሳበው ከዚያን ቀን ጀምሮ እንደሆነ የሚናገሩ ሰዎች አሉ፡፡

ግሪክ፣ የባለቅኔዎች፣ የፈላስፎች፣ የሊቃውንት እና የደራሲያን አገር በመሆኗ፣ ለማንኛውም ሰው ቢሆን በአቴና ሕዝብ ዘንድ ቀርቦ በጉባኤ ፊት ለመናገርና ተሰሚነት ለማግኘት፣ ከዚህም በላይ ደግሞ ምርጥ ተናጋሪ ሆኖ ለመመስገን፣ ቀላል ነገር አልነበረም፡፡ በዚህ ሁኔታ ዴሞስቴን በመጀመሪያ ጊዜ በጉባኤ ፊት ቀርቦ ሲናገር፣ ንግግር የማይችል ሆኖ ስለተገመተ፣ ንግግሩን እያቋረጡበት "እንዲህ ይባላል፤ እንዲህ አይባልም" በሚል ዓይነት ሁለት ጊዜ አስደገሙት፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት፣ ዴሞስቴን ሲናገር ድምጹ ደካማ፣ ምላሱ ኮልታፋ እና ትንፋሹ ቁርጥ-ቁርጥ የሚል፣ አጭር፣ ስለነበር ንግግሩ እየተቆራረጠበት በሰዎች ዘንድ ሊደመጥ የማይችል እና የማይገባ ሆኖ በመገኘቱ ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ፣ ዴሞስቴን ከሰው ተለይቶ እንደ ባሕታዊ ብቻውን እየኖረ ንግግር የማሳመርን ጥበብ ይማር ጀመር፡፡ የሚንተባተበውን ምላሱን ለማፍታታት ሲል፣ ባፉ ውስጥ ጠጠር እየጨመረ፣ ብቻውን ሆኖ እንደ እብድ ሰው ከፍ ባለ ድምጽ በመናገር አንደበቱን ገራው፡፡ እንደዚሁም ደግሞ፣ በጉባኤ ፊት ቀርቦ በሚናገርበት ሰዓት፣ ሕዝብ ንግግሩን ለማቋረጥ የሚያደርግበትን የተቃዋሚነት ሁካታ ለመልመድና ለማሸነፍ እንዲረዳው ሲል፣ ከባህር ዳር ቆሞ በመናገር የባሕሩ ማዕበል ሲመታው ከሚያሰማው ጩኸት ጋር ንግግሩን ያወዳድር ነበር፡፡ በመሬት ውስጥ

የሚኖርበትንም ዋሻ አዘጋጅቶ፣ ብዙ ወራት ሙሉ ከዚያ ሳይወጣ፣ ሰው ሀሳቡን በመልካም ንግግር የሚገልጥበትን ዘዴ ሲሻ፣ ቱሲዳድ የሚባለው ሊቅ የጻፈውን መጽሐፍ እየደጋገመ እስከ ስምንት ጊዜ ይገለብጥ ነበር፡፡ ከተደበቀበትም ጉድጓድ ውስጥ ወጥቶ፣ ሕዝብ ወደሚገኝበት ቦታ የመሄድ ሀሳብ በመንፈሱ ውስጥ እንዳይገባ ለማድረግ፣ የራሱን ጠጉር ግማሹን ተላጭቶ፣ ግማሹን ትቶ ከሰው ዘንድ ሊቀርብ የማይችል አስቀያሚ መልክ ይዞ ኖረ፡፡

ዴሞስቴን ይህን በመሰለ አኳኋን ብቻውን እየኖረ፣ ራሱን ለራሱ መምህር አድርጎ በማሰብና በመመራመር፣ ቃላቱን ከፍ አድርጎ ብቻውን በመናገር፣ በመጻፍና በመገልበጥም ስምንት ዓመት ሙሉ መንፈሱን እያበለጸገ አንደበቱን ካረመና ምላሱን ካሰላ በኋላ፣ እንደገና ጉባዔ ፊት ቀርቦ ተናገረ፡፡ በዚህ ጊዜ በቦታው የተሰበሰቡት ሰዎች ሁሉ ንግግሩን ሲሰሙ እጅግ አድርገው ተደነቁ፤ ዴሞስቴንም አስቦበት ከነበረው ዓላማ ደረሰ፡፡

*(ከበደ ሚካኤል፣ 1994፣ 31-32 ለማስተማሪያ እንደሆን መስስተኛ ለውጥ ተደርጎበት የተዘጋጀ)*

## ክፍል አንድ፡- ንባብ

**፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቂ ማብራሪያ በመስጠት በቃል መልሱ፡፡**

1. በጥንታዊው የግሪክ ሥልጣኔ ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን እንዴት ያሉ ዝግጅቶችን ይጠይቃል?
2. ባለንበት ዘመን አስፈላጊ ምክንያቶች አቅርቦ በሰላ (በጠነከረ) አንደበት አድማጮችን መሳብ ጠቃሚ የሚሆነው እንዴት ነው?
3. ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን እንዴት ይቻላል?
4. ከግሪክ ጥንታዊ ሥልጣኔ ጋር በተያያዘ የዴሞስቴንን ታሪክ ማጥናት ለምን ይጠቅማል?

2. በዚህ ዘመን ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን እንደ ጥንታዊው ግሪካዊ ዴሞስቴን ከሰዎች ተገልሎ ለብቻ በመሆን ንግግር መለማመድ አስፈላጊ ይሆናል? እንዴት?
3. ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን መሰልጠን ወይም መገራት ያለባቸው የአካል ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?
4. ዴሞስቴን ራሱን ወደጥሩ ተናጋሪነት ለማሸጋገር ያደረጋቸው ጥረቶች ምንድን ናቸው?

፪. በቀረበላችሁ ምንባብ አማካይነት ሊተላለፍ የተፈለገዉ ዋና መልእክት (ጭብጥ) ምንድነው? በአጭሩ ግለጹ፡፡

፫. ለሚከተሉት ቃላት ወይም ሐረጎች በምንባቡ ውስጥ የያዙትን ፍች በተብራራ መንገድ ስጡ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. የንግግር ጥበብ | 4. አንደበተ - ርቱዕ |
| 2. የተገራ አንደበት | 5. መንፈስ ማበልጸግ |
| 3. የታረመ አንደበት | 6. ምላስ ማስላት |

## ክፍል ሁለት፡- ንግግር

፩. ዴሞስቴን ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን ያደረጋቸው ጥረቶች ተገቢነት እንዳላቸዉና እንደሌላቸው የሚያስረዳ የጋራ ውይይት አካሂዱ፡፡

፪. በምርጥ ንግግር አቀራረባቸው የምታደንቋቸው ሰዎች (መምህሮቻችሁ፣ የክፍል ወይም የትምህርት ቤት ጓደኞቻችሁ ወይም ሌሎች) የንግግር አቀራረባቸው (በይዘትና በቅርጽ) እንዴት እንደሆነ በመዘርዘር ክፍል ውስጥ ተወያዩ፡

፫. ቡድን መሥርታችሁ፣ ንግግርን በጽሑፍ አዘጋጅቶ ከማንበብና ንግግርን በጽሑፍ አዘጋጅቶ አጥንቶ በቃል ከመናገር የትኛው አድማጭን ማርካት እንደሚችል ተወያዩ፡፡

## የንግግር መመሪያ

በመድረክ ላይ የሚቀርብ ንግግር (የመድረክ ንግግር ሊባል ይችላል) በሚከተሉት መመሪያዎች መሠረት ይዘጋጃል፤ ለመድረክም ይቀርባል።

**ሀ. የንግግር አዘገጃጀት**

- የንግግር ርዕስ መምረጥ፣
- የንግግርን ርዕስ መወሰን ወይም ማጥበብ፣
- የንግግሩን ዓላማ በግልጽ መረዳት፣
- የአድማጭን ማንነት መለየት፣
- ንግግር በሚደረግበት ርዕስ ላይ ሰፋ ያለ መረጃ ማሰባሰብ፣
- መረጃን የሚያመለክት ሀሳብ በአስተዋጽኦ መልክ ማዘጋጀት፣
- በመድረክ ላይ የሚቀርበውን ንግግር እንዴት እንደሚቀርብ መለማመድ፤

**ለ. የንግግር አቀራረብ**

- አድማጮችን በሚያረካ መንገድ ንግግር ማድረግ፣
- ንግግር በማቅረብ ሂደት ውስጥ የአድማጮችን ሁኔታ በመከታተልና የንግግሩ ሐሳብም ሆነ አቀራረቡ ማራኪ እንዲሆን ማድረግ።
- በንግግር ማቅረብ ሂደት የመግቢያ፣ የዝርዝር ሐሳብና የማጠቃለያ ሐሳብ እንዴት ያለ አቀራረብ ሊኖረው እንደሚገባ አስታውሶ መተግበር

*(ዓለም እሸቱ፣ 1999፣ 130-123 ለማስተማሪያነት እንዲያገለግል መጠነኛ ለውጥ በማድረግ የተወሰደ)*

**፬. የሚከተለውን በጽሑፍ የቀረበ ንግግር መነሻ በማድረግና ተያያዥነት ያለው ሐሳብ በመጨመር ለጓደኞቻችሁ የቃል ንግግር አድርጉ።**

ይድነቃቸው ተሰማ በ፲፱፻፲፬ ዓ.ም ተወለዱ። ዕድሜያቸውን ሙሉ ከስፖርት ዓለም ያልተለዩት ይድነቃቸው ተሰማ ከአገር ውስጥ እስከ ዓለም አቀፍ የስፖርት አስተዳደሮች በብዙ ቦታዎች ሠርተዋል። ሌላው ቀርቶ ሰውነታቸው በህመም በተዳከመበትና በህይወት ለመቆየት አስጊ

ደረጃ ላይ በነበሩበት ጊዜ እንኳ፣ ከሦስት ዓመት በላይ በፕሬዝዳንትነትና በምክትል ፕሬዝዳንትነት ያገለገሉትን የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደረሽን (CAF) እንቅስቃሴ ከማገዝ አልተቆጠቡም ነበር።

በኢትዮጵያ ሬድዮ እረጅም ዓመት በተወዳጅ የስፖርት ጋዜጠኝነት ያሳለፈው አንጋፋው የስፖርት ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ፣ ይድነቃቸው ከታላቅ ተጫዋችነት፣ አሠልጣኝነትና መሪነት በተጨማሪ የተዋጣላቸው ተንታኝ፣ የአድማጭን ጆሮ መሳብ የሚችሉ ተናጋሪ እንደነበሩ መስክሯል። በዓለም ዋንጫና በአፍሪካ ዋንጫ ውድድር ወቅት የይድነቃቸው ተሰማ ትንታኔ ይናፈቃል። የስፖርት ክሥተቶች ታሪካዊ ቅደም ተከተል የማይዛነፍባቸው፣ የግለሰቦችን ስምና የሚገኙበትን ክለብ፣ መቼና ምን እንደሆነ ሳይቀር፣ ዐውደ ጥበባዊ በሆነ የመረጃ ስፋትና ምርጥ ቃላት፣ ኀሊና ገዥና አሳማኝ ንግግር፣ ትንታኔ የማቅረብ ችሎታ ነበራቸው።

ይድነቃቸው ተሰማ ለማንበብ  የማይታክቱ ሰው መሆናቸው ሌላው ተሰጥኦዋቸው ነበር። በነጋ በጠባ ቁጥር "ዓለምና ስፖርት እንዴት አደሩ?" ብለው ሳይጠይቁ ወደ ሌላ ተግባር አይሸጋገሩም ነበር። ከንባብ ቋሚ ልምዳቸው ጋር በተያያዘ፣ እንደ ሁነኛ ውጤት ሊጠቀሱላቸው የሚችሉ ልዩ ልዩ ሰነዶችን ያረቀቁና የጻፉ ናቸው። ለሕዝብ ታትሞ በመውጣት ደረጃ እንደምሳሌ ሊጠቀስ የሚችለውም፣ "ሕዝብና አስተዳደር፣ ሞራል" የተሰኘው መጽሐፋቸው ነው።

ለይድነቃቸው ስፖርት ምን ጊዜም ለሕዝቦች የእርስ በርስ መቻቻልና የሰላም ቦታ መሆኑን ማረጋገጥ፣ በእምነትና በዘር ላይ የተመሠረቱ ክለቦች እንዳይኖሩ መጣር፣ ቀዳሚ ዓላማቸውና ተግባራቸው ነበር። ለደቡብ አፍሪካ የፀረ-አፓርታይድ ትግልም ስፖርቱን በሚገባ ተጠቅመውበታል። እኒህ ታሪካዊ ሰው በአፍሪካ የስፖርት "ኮንፍረስ"፣ በዓለም አቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ፣ በ"ፊፋ"ና በአፍሪካ ኦሎምፒክ ኮሚቴ በፕሬዝዳንትነትና በሌሎች ከፍተኛ የአመራር ሃላፊነት ቦታዎች ሁሉ ተመድበው አገልግለዋል። ከነዚህ ሁሉ አገልግሎቶች በኋላ በ፲፱፻፹፱ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

*(ሰለሞን ጥላሁንና ስምረት ገብረ ማሪያም፣ 2000፣125-127፣ ለማስተማሪያነት እንዲያገለግል መለስተኛ ለውጥ ተደርጐበት የተዘጋጀ)።*

**ጅ. የሚከተለውን በጽሑፍ የቀረበ ሀሳብ በቃላችሁ በማጥናት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡ (ጽሑፍን አጥንቶ በቃል ስለማቅረብ በምዕራፍ አምስት የተሰጠውን ማስታወሻ እንደገና ተመልከቱ)**

## ዲን ሱዊፍት

ዲን ሱዊፍት የሚባለዉ የእንግሊዝ ደራሲ፣ አዲስ አሽከር በቀጠረ ቁጥር እንዲህ ይለው ነበር፡፡ «እንድትፈጽማቸው የምለምንህ ሁለት ነገሮች ብቻ ናቸው፡፡ አንዱ የምለምንህ ነገር፣ ምን ጊዜም ቢሆን በቤትህ ውስጥ ስትተለላፍ ከአንዱ ክፍል ወጥተህ ወደአንደኛው ክፍል ስትገባ በሩን እንድትዘጋ ነው፡፡ ሁለተኛው የምለምንህ ነገር፣ እንደዚሁ ሁሉ፣ ካንዱ ክፍል ወጥተህ ወደ ደጅ ስትሄድ የከፈትኸውን ቤት ዘግተህ እንድትሄድ ነው፡፡»

አንዱ አገልጋይ፣ ከዕለታት አንድ ቀን፣ ወደሱ ዘንድ ቀርቦ፣ «እኅቴ ልትዳር ነውና ለሰርግዋ እንድሄድ ፍቀድልኝ» አለው፡፡ ዲን ሱዊፍትም ደስ እያለው ፈቀደለትና እሱ ከሚቀመጥባቸው ፈረሶቹ አንደኛው ተጭኖለት፣ አንድ ሌላ አገልጋይ ተከትሎት ሄዶ ከቤቱ አድርሶት እንዲመለስ አዘዘ፡፡ አገልጋዩም ከደስታ ብዛት ጌታው ያስጠነቀቀውን ትእዛዝ ዘንግቶ በሩን ከፍቶ ሳይዘጋው ሄደ፡፡ ከሄደ በኋላ ጥቂት ቆይቶ፣ ዲን ሌላ አገልጋይ ጠራና “ፈረስ ጭነህ ጋልበህ ድረስባቸውና ምንም ያህል ርቀው ቢሄዱ፣ ከደረሱበት ቦታ ተመልሰው በፍጥነት እንዲመጡ ንገራቸው” ብሎ ላከው፡፡

የተላከው አገልጋይ በፈረስ ጋልቦ ግማሽ መንገድ እንደሄዱ ደረሰባቸውና የጌታውን ትእዛዝ ነገራቸው፡፡ ፈቃድ ተቀብሎ የነበረው አገልጋይ «ምክንያቱ ምን ይሆን?» እያለ ደንግጦ እየሰጋ ተመልሶ መጣ፡፡ ከጌታውም አጠገብ ቀርቦ፣«እነሆ ተመልሼ መጣሁ፤ ትእዛዝዎን ይስጡኝ» አለው፡፡ ዲን ሱዊፍት፣ «አይ የጠራሁህ ለሌላ ነገር አይደለም፡፡ ከፍተህ ትተኸው የነበረውን በር ዘግተህ እንድትሄድ ነው፡፡» ብሎ መለሰለት፡፡

*(ከበደ ሚካኤል፣1994፣20-21)*

## ክፍል ሦስት:- ጽሕፈት

**፩. የሚከተለው አንቀጽ ሥርዓተ ነጥቦች የሚገቡባቸው 14 ክፍት ቦታዎች አሉት:: የቀረበውን ታሪክ በጥንቃቄ በማንበብና የተሰጡት 4 ሥርዓተ ነጥቦች የት የት ቦታ እንደሚገቡ በማጤን ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በክፍት ቦታዎች ላይ ሙሉ::**

1. አራት ነጥብ (::)
2. ነጠላ ሰረዝ (፣)
3. ቅንፍ(    )
4. ትእምርተ ጥቅስ (« »)

በጣልያን ወረራ ዘመን ለሀገራቸው ነጻነት ከተዋደቁት በርካታ ወጣቶች ውስጥ አንዱ ዘርጋ ናጂ ነበር_1_ ዘርጋ ናጂ_2_ ቁመቱ ረጂም_3_ አጥንቶቹ ሰፋፊ _4_ መልኩ ቀይ _5_ ፀጉሩ ከልክ በላይ አድጎ በሦስትዮሽ የተሸረበ ነበር _6_ ያ ፀጉሩ በጀርባውና በትክሻው ላይ ተንዠርግጎ ወርዶ ሲታይ ልዩ ግርማ ያጎናጽፈዋል _7_ ዘርጋ ጢም አልባ ሲሆን _8_ ጠቅላላ ገጽታው የሰው ዓይን የሚማርክ ሸበላ _9_ ቆንጆ _9_ ነበር _10_ ዘርጋ ለአራት ዓመታት ያህል በዋሻና በጫካ ውስጥ ሲኖር _11_ ሹሩባው በወገቡ ከታጠቀው የቆዳ ዝናር በታች ወርዶ ይታይ ነበር _12_ በጎታ ገበያም ሆነ በሌሎች ስፍራዎች አጋጥሟት ያየችው ሴት ሁሉ _13_ ዐይኔ ይፍሰስልህ _13_ ሳትል አታልፍም ነበር _14_

*(ዓለም እሸቱ፣ ዓለማየሁ ነሪን በመጥቀስ፣ 1999፣ 24)*

## ክፍል አራት:- ሰዋስው

**፩. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን የስም እና የግሥ ሙያዎች ለይታችሁ በመተንተን አሳዩ::**

*ምሳሌ*:- “ሜላት የቤቱን ወለል አጠበች::” በሚለው ዓረፍተነገር ውስጥ ስም የሆኑ ቃሎች “ሜላት እና የቤት ወለል” ናቸው:: ስለዚህም የዓረፍተነገሩ:-

ሀ) ባለቤት – ሜላት

ለ) ተሳቢ – የቤቱ ወለል

ሐ) ማሰሪያ አንቀጽ – አጠበች

ይሆናል ማለት ነው፡፡

1. ልጅቷ ላሚቷን አለበች፡፡
2. ህፃኗ ልጅ የመስኮቱን መጋረጃ ጐተተችው፡፡
3. ሠራተኞች የእንስራውን ውሃ ደፉት፡፡
4. ወታደሩ የታጠቀውን ሽጉጥ አወጣ፡፡
5. ችግኞችን ውሃ አጠጣች፡፡

**፱. በሚከተሉት ቃላት ባለንብረትነትን፣የዓረፍተነገር ባለቤትነትንና ተሳቢነትን እንዲያመለክቱ በማድረግ ዓረፍተነገር ሥሩባቸው፣ ዓረፍተነገሮቻችሁንም፣ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማሳየት አስተያየት እንዲሰጡባቸው አድርጉ፡፡ በሚሰጥዋችሁ አስተያየት መሠረትም አሻሽላችሁ ጻፉ፡፡**

**ምሳሌ፡**
- የተሰበረው **ቀንድዋ** ነው፡፡ (ባለንብረትነትን)
- **ቀንድ** ለዋንጫ መሥሪያነት ያገለግላል፡፡ (ባለቤትነትን)
- ገበያ ወጥቼ **ቀንድ** ገዛሁ፡፡ (ተሳቢን)

1. በሬ 2. ልብስ 3. ሴት 4. ውሻ 5. ሥጋ 6. ጽሑፍ

**፲. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉት ቅጥያዎች የሚያመለክቱትን (ባለቤትነትን፣ አገናዛቢ አጸፋነትን፣ ተሳቢነትን፣ ብዙ ቁጥርን) ግለጹ፡፡**

ሀ) ተናገረች

ለ) መጽሐፋቸውን

ሐ)ሥራን

መ) ልብሶች

## ክፍል አምስት፡- ስነጽሑፍ

**፩. ጥንድ ሁናችሁ ከሚከተለው አንቀጽ ውስጥ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ያላቸው አምስት ቃላት አውጡና እማሬያዊ እና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን ስጡ፡፡**

ከዱሮ የእንጨት ጉምሩክ አጠገብ ወደ ምሥራቅ ሲል ካለው ወንዝ ማዶ፣ ድልድዩን ወደ ምሥራቅ ተሻግሮ፣ መጀመሪያ የሚገኘው አነስተኛ ሳር ክዳን ቤት፣ የተበጀ ቤት ማለት ያ ነው፡፡ ተበጀ፣ በዚያው በቤቱ

ውስጥ፣ በዚያው በጉለሌ የተወሰኑ ዘመናት ኖሯል። እንጨቱን ተሸክሞ አፈሩን ቆፍሮ ቤቱን የሠራው እርሱ ነው። ዋጋ ከፍሎ አስከድኖታል። ተበጀን፣ ኩራት ተሰማው። ቆይቶ ደግሞ፣ ዓይኖቹ እንባ አዘሉ። በጉንጮቹም የእንባ ዘለላዎች ወረዱ። በግራ እጁ መዳፍ በጉንጮቹ ላይ የተንከባለሉትን የእንባ ዘለላዎች ጨፈለቃቸው። ዓይኖቹ እንባ ያፈሰሱት የራሱ ጉጆ ስላለው በልቡ ውስጥ ክብርና ኩራት ተሰምቶት ነው። ሊነገር በማይችል ደስታ ልቡ ተነክቷል።ዝናብ ያበረራቸው፣ ከቤቱ ጥግ ሲጠለሉ ይችላሉ። ቤት የእግዚአብሔር ነውና ወጀብ እንዳያገኛቸው ከቤቱ ውስጥ ዝናቡ እስኪያባራ ይቆያሉ። ተበጀን፣ "ቤትህ ይባረክ" ሲሉት ነው። እንግዲህ መንገደኛው ሁሉ "ይህ የማን ቤት ነው?" ብሎ ሲጠይቅ "የተበጆ! ሊባል ነው" አለ። ቀጥሎ ደግሞ "ተበጆ የትኛው ነው?" ሲባል "ዶሮ ነጋዴው! ሰከራሙ!"፣ ሊባል ነው። "አወይ! እኔ ተበጆ፣ ተበላሽቻለሁ" አለና ደነገጠ። ከዚህ በኋላ "ስለቤቱ ክብር እንኳ፣ መጠጥ መተው ይገባኛል" አለ።

*(ተመስገን ገብሬ፣ 2001፣ 119-120 አነስተኛ ለውጥ ተደርጎበት የቀረበ)*

**፪. በሚከተለው ጽሑፍ ውስጥ ያሉ ፈሊጣዊ እና ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በቀጣዩ ሰንጠረዥ ዓይነት ለዩና ፍች ከሰጣችኋቸው በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።**

**ምሳሌ፣**

| ፈሊጥ | ፍች | ምሳሌያዊ አነጋገር | ፍች |
|---|---|---|---|
| የህይወት ስርንጉጥ | ችግር፣መከራ | ስምን መልአክ ያወጣዋል | ስም፣ ለተሰያሚዉ መጪዉን ዕድሉን ያመለክታል። |
| ሀ. | | | |
| ለ. | | | |
| ሐ. | | | |
| መ. | | | |

በቀድሞ አጠራር ኢሉባቦር ክፍለ አገር፣ ሁሩሙ በምትባል መንደር በ፲፱፻፵፪ ተወለደ፡፡ ‹‹ስምን መልአክ ያወጣዋል›› እንደሚባለው ‹‹ሂካ‹‹ የተሰኘ የተጸውዖ ስም ተሰጠው፡፡ ይህ ‹‹ተርጓሚ›› ለተሰኘው የአማርኛ ቃል አቻ ቀረቤታ ያለው የኦሮምኛ ስያሜ ከ ‹‹ሰውዬው›› ኋለኛ የሥራ ሕይወቱ ጋር የተጣመረ በመሆኑ፣ በርካታዎችን ሳያስደምም አላለፈም፡፡ ምዕዋ ዘልቆ በስመ ጥምቀቱ (በጥምቀት ስሙ) ‹‹ኦኔሲሞስ›› የሚል መጠሪያ የተሰጠው ሂካ፣ በኦሮምኛ ቋንቋ ቅዱሳት መጻሕፍትንና ሌሎችንም ጽሑፎች በመተርጐም ለቋንቋው ሥነጽሑፋዊና ሥነልሳናዊ እድገት ሁነኛ አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ኦኔሲሞስ ወደዚህ ዓቢይ የትርጉምና ጽሑፍ ሥራ ከመዝለቁ አስቀድሞ፣ መሪርና አስከፊ በሆነ የሕይወት ስርጓጉጥ ውስጥ አልፏል፡፡

“ፀሐይ ሳለ ሩጥ፣ አባት ሳለ አጊጥ” የሚባለው እድል አላጋጠመውም፡፡ ገና የአራት ዓመት ልጅ ሳለ ወላጅ አባቱን ሞት ነጠቀበት፡፡ ድንጋጤው በቀሪው ቤተሰብና በጨቅላው ሂካ ሕይወት የጨለማ ድባብን አጠላ፡፡ የመከራው ገፈት በዚህ ሳያበቃ፣ ተጨማሪ ስቃይና ኀዘን ወደዚህ ጎጆ መንደርደር ጀመረ፡፡

“የመከራ ቀን ሲደርስ አይታወቅም” እንደሚባለው በዘመኑ የድሃውን ጎተራ እየገለበጠ፣ ከብት በዝርፊያ እየነዳ፣ እንደ ቋያ እሳት ቀዬ እያጋየና የሰፈሩን ማቲ ለባርነት እየዳረገ የሚዘዋወር የሽፍታ መንጋ፣ በሁሩሙ መንደር ዘልቆ ጎጡን ማመስ ጀመረ፡፡ ይኼኔ የሂካ ወላጅ እናት፣ “እናት ለልጇ አራስ ነብር ናት” እንደሚባለው፣ ከዚህ መዓት ልጇን ለመታደግ ሽሽት ገባች፡፡ ሆኖም የዕለቱ ጀምበር ፊት ነስቷት ኖሮ፣ ሰይፍ ከሚነቀንቁ የሞት መልእክተኞች ጋር ፊት ለፊት ተፋጠጠች፡፡ በወቅቱ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ የነበረው ሂካ፣ ያቺን ቅጽበት ከጊዜ በኋላ እንዲህ ያስታወሳታል፡፡

“አንድ ሰው እየተንደረደረ መጣና እጄን በመጐተት ወደራሱ ሳበኝ፤፡፡ እናቴም የቀረውን እጄን አጥብቃ በመያዝ፣ ‘ፈጽሞ አትወስደውም!’ ስትል ተከላከለች፡፡ ይኼኔ ሰውዬው ሰይፉን መዘዘና፣ ‘የማትለቂው ከሆነ

ሁለታችሁንም እገድላለሁ!’ ሲል ዛተ። እናቴም፣ ‘ከሚሞትብኝ ባርነት ቢገባ ይሻላል።’ በማለት እጇን አላላች”።

በዚህ ዘግናኝ ሁኔታ ከእናቱ መዳፍ ተመንጭቆ በወንበዴዎች እጅ የወደቀበት ቅጽበት፣ ከቶም ከምናቡ እንዳልተፋቀና ውስጡንም ያዋትተው እንደነበረ በ፲፰፻፹፯ ዓ.ም ባሳተመው መጽሐፍ ባሰፈራት ስንኝ አማካይነት መገንዘብ ይቻላል። “ሞትን መሻገር ከተቻለ አዲስ ሕይወትና እድል ይገኛል።” እንደሚባለው፣ወጣቱ “ሂካ” (በኋላ ኦኔሲሞስ ተብሎ የተሰየመው) በህይወት ዘመኑ ብዙ ሥራ ሠርቷል።

*(ሰሎሞን ፕሳሁንና ሥምረት ገብረማርያም፣ 2000፣ 22-23)*

## ቅኔ

ቅኔ በቃል ወይም በጽሑፍ በግጥም ወይም በዝርው የሚነገር ወይም የሚጻፍ ድርሰት ነው። ቅኔ መቀኘት ማለትም አመራማሪ የሆነ የተደበቀ ነገር ያለው ግጥም መግጠም፣ ሀሳብን አመራማሪ (ምስጢር) አድርጎ ማቅረብ ማለት ነው። ቅኔ በግጥም፣ ሲቀርብ አደራደሩ ወይም የምጣኔ ማሳያ ምቱ ምንም ሳይዛነፍ ዜማውን ጠብቆ ቅርጽና ይዘቱን አስማምቶ ከቀረበ ውበቱ በቀላሉ ይታያል፤ አንባቢን ወይንም ቅኔ ፈቺን ይስባል፤እንዲመራመር ያደርገዋል።

ቅኔ የሚነገረው ወይም የሚጻፈው በሰምና ወርቅ ነው።
“ሰሙ ደራሲው ሊናገረው ያሰበው ነገር የተሸፈነበት መጋረጃ ሲሆን፣ ወርቁ ደግሞ አንድን ቃል በማጥበቅ፣ በማላላት፣ ወይም አጠገቡ ካለው ከሌላው ቃል ጋር አያይዞ በማንበብና በመመርመር የሚገኘው ምሥጢር ወይም ፍሬ ነገር ነው”
*(ብርሃኑ ገበየሁ፣ 2001፣ 173)*።

ቅኔው የተመሠረተበት ቃል ኅብረ ቃል ይባላል። ኅብረ ቃሉ በፍች በሁለት ቦታ ተከፍሎ አገባባዊ ትርጉሙ ሰም፣ ከአገባብ ውጪ የሆነው ፍች ደግሞ ወርቅ ይባላል። በዚህም መሠረት የሚከተሉትን ቅኔዎች በምሳሌነት መመልከት አስፈላጊ ይሆናል።

**ምሳሌ፣**

ምነው ጌታዬ በደልከኝ
አጥፍቼም እንደሁ ሳትመክረኝ፣
በሰው ፊት ቀጣሽኝ ።

ኅብረ - ቃል፣በሰው ፊት
ሰም፣ሰው እያየ
ወርቅ፣ የሰው ፊት እንዳይ፣ እንድለምን ወይም ተረጅ እንድሆን አደረግሽኝ።

**፫. በቡድን በመሆን ከሚከተሉት ቅኔዎች ኅብረ ቃሎችን ከለያችሁ በኋላ ሰምና ወርቅ ብላችሁ ፍቻቸውን በመዘርዘር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።**

ሀ) እንዴት ያለ ሰው ነው የሌለው እምነት፤
እውነት ሞቷል ብለው ይለኛል ሐሰት።

ለ) እኛስ ሄደን ነበር ደኅና አገር መስሎን፤
ተመልሰን መጣን ጉጉት በዝቶብን።

ሐ) እዚያ ማዶ ሆና ትጣራለች እናት፤
ና ብላ ነው እንጂ ሌላም ጉዳይ የላት።

መ) እዩልኝ ያንን ልጅ ጌጥ አልጠግብ ባይ፤
መርገፍ ጨመረበት በጥበቡ ላይ።

ሠ) እያለለት መልኬ ካንገቴ በላይ፤
እጅ እጁን ያየኛል ያለም አታላይ።

ረ) ከልፍኝ አስወጥተው እዳስ አጉረው፤
ቅራሪውን ሰጡኝ ጠላ ነው ብለው።

ሰ) ለልጅ ልጅ ለምልሞ እንዲህ የሚታየው፤
ይህ አትክልታችን አዲስ አበባ ነው።

ሸ) ተዋት አትገላግሏት ሩቅ ነው መንገዷ፤
የከበደ ነገር ይዛለች በሆዷ።

# ማጠቃለያ

ምርጥ ንግግር የይዘትና የቅርጽ ድምር ነው፡፡ ይዘት የሚነገረው ጉዳይ ሲሆን፣ ቅርጽ ደግሞ አቀራረብ ነው፡፡ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ንግግር ለማድረግ በበቂ ሁኔታ መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

ንግግር፣ በጥንቃቄ መዘጋጀት እና በአዘገጃጀቱ ደግሞ ንግግሩ በሚቀርብበት ዓላማ እና በታዳሚዎች ማንነት ላይ ተመስርቶ መደራጀት ይኖርበታል፡፡
ምርጥ ንግግር ከፍተኛ ጥበብ ነው፤ ሀሳብን የማቅረብ ጥበብ፡፡ የንግግር ጥበብ ሀሳብ፣ ቋንቋ እና አቀራረብ ይሻል፡፡

የንግግር ቋንቋ ሲባል፣ ንግግሩ የሚቀርብበትን መደበኛ ሰዋስው፣ ከዚያም አልፎ ፈሊጣዊ ንግግሮች፣ ምሳሌያዊ አቀራረቦች፣ ተረቶችን፣ ወዘተ. ግብአት ያደርጋል፡፡ በምርጥ ንግግር ውስጥ፣ የንግግር ታዳሚዎችን ስሜት በአቀራረብ (በአንደበት፣ በአገላለጽ፣ ወዘተ) አጥብቆ መያዝና ወደ ሚፈለግበት አቅጣጫ መምራት ያስፈልጋል፡፡ ቃላት በዓረፍተነገር ወስጥ የተለያዩ ሙያዎች አሏቸው፤ በባለቤትነት ያገለግላሉ፤ በተሳቢነት ያገለግላሉ፤ በማሠሪያ አንቀጽነት ያገለግላሉ፡፡

ምዕላዶች በዓረፍተነገር ውስጥ በአጸፋ ባለቤትንና ተሳቢን ያመለክታሉ፤ እንዲሁም ባለ ንብረትነትን ይጠቁማሉ፡፡

በጽሑፍ ሀሳብን ለማስተላለፍ ሥርዓተ ነጥቦች በሥርዓት ከተያያዙ ቃላት ጋር በመጣመር አገልግሎት አላቸው፡፡ ስለዚህ በተገቢው ቦታ አስፈላጊውን የሥርዓተ ነጥብ ዓይነት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

ቅኔ በንግግርም በጽሑፍም ይቀርባል፡፡ ቅኔ ሀሳብን አመራማሪ አድርጎ ለማቅረብ ያገለግላል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የምርጥ ንግግር መለያ ይሆናሉ የምትሏቸውን ሦስት ነጥቦች ጻፉ።
2. በቃል አጥንቶ ንግግር ለማካሄድ በዝግጅት ወቅት ማድረግ የሚገባችሁን ሦስት ነጥቦች ጻፉ።
3. ዓረፍተነገሮችን ስትመሰርቱ የቃል ክፍሎች ተግባር እንዴት ያለ ነው?
4. የእርባታ ምዕላዶች ሙያ እንዴት ያለ ነው?
5. ስርአተ ነጥቦች በጽሕፈት ውስጥ ካላቸው አገልግሎት ሁለቱን ብቻ ጻፉ።
6. ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ ንግግሮች በንግግር ውስጥ እንዴት ያለ ጠቀሜታ እንዳላቸው ግለጹ።
7. የቃላት እማሬያዊ ፍች ምንድነው? ፍካሬያዊ ፍችስ?
8. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተማራችሁትን በመከተል ለቅኔ አፈታት መግለጫ ስጡ።

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ዘጠኝ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘባችሁት የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመገንዘባችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✓)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተገነዘባችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የምርጥ ንግግር መለያዎችን አመለክታለሁ፡፡ | | | |
| 2 | በደረጃው በሚመጥኑ ርዕሶች ላይ ንግግር ለማድረግ መዘጋጀትና የንግግር ሥርዓትን መጠበቅ እንደሚገባ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 3 | የተለያዩ መረጃዎችን በማስታወሻ በመያዝ እና በማጥናት የቃል ጥናት ንግግር እንዴት እንደሚቀርብ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 4 | በዓረፍተነገሮች ውስጥ የቃላት ክፍሎችን ተግባር መግለፅ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 5 | የርባታ ምዕላዶችን ሙያ የትኞቹ እንደሆኑ መዘርዘር ችያለሁ፡፡ | | | |
| 6 | ሀሳቤን በጽሑፍ ስገልጽ አስፈላጊ ሥርዓተ ነጥቦችን እጠቀማለሁ፡፡ | | | |
| 7 | ከተለያዩ የንግግር ዝግጅቶች ውስጥ ፈሊጣዊና ምሳሌያዊ ንግግሮችን ለይቼ በማውጣት ፍች መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 8 | ከተለያዩ የንግግር ዝግጅቶች ውስጥ እማሬያዊ እና ፍካሬያዊ ፍች ያላቸውን ቃላት በመለየት ፍቻቸውን ሰጥቻለሁ፡፡ | | | |
| 9 | ለቀረቡልኝ የተለያዩ ቅኔዎች ህብረ ቃል በመለየት የሰምና የወርቅ ፍቻቸውን ሰጥቻለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(x) ምልክቶች ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ አስር

## ክርክር

**የምዕራፉ ዓላማዎች:- ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- የቀረበላችሁን ፅሁፍ አንብባችሁ የተረዳችሁትን ትገልፃላችሁ::
- ስርዓት ያለው ክርክር ለማካሄድ የሚጠቅሙ ነጥቦችን ትገልጻላችሁ::
- ለቃላት አገባባዊና ቀጥተኛ ፍች፣ እንዲሁም ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍችዎች ትሰጣላችሁ::
- ከምታዳምጡት፣ ማብራሪያና ገለፃ የምታገኟቸውን ጠቃሚ ሀሳቦች በማስታወሻ ትይዛላችሁ::
- የቅኔን ህብረ ቃል፣ ሰምና ወርቅ ትገልጻላችሁ::
- ከአንድ ጽሑፍ ውስጥ መንስኤና ውጤትን የያዙ ዓረፍተነገሮችን ለይታችሁ ታወጣላችሁ::
- ገፀ ባህርያቱን ወክላችሁ ባህላዊ ሙግት ታደርጋላችሁ::

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. ክርክር ከውይይት ወይም ከጭውውት በምን ይለያል?
፪. ክርክር ለምን ይካሔዳል?
፫. ክርክር ሲደረግ አዳምጣችሁ ታውቃላችሁ? ያዳመጣችሁትን ክርክር ሂደት ምን እንደሚመስል ግለጹ፡፡
፬. ክርክር ሲካሄድ ታሳቢ የሚሆኑ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
፭. ስለክርክር አካሄድ ማወቅ ምን ጥቅም ይሰጣል ትላላችሁ?

# ክርክር

ክርክር ማለት በሁለት ሰዎች ወይም በሁለት ቡድኖች መካከል የሚካሄድ ሙግት ነው፡፡ በህብረተሰባችን በስፋት የተለመደ ሲሆን፣ ሲተገበርም በርካታ ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ለአሸናፊነት በሚደረገው ትግልና በአንዳንድ ሌሎች ነጥቦች ቢመሳሰሉም የጥንቱ ሙግትና የዛሬው ክርክር ሰፊ ልዩነት አላቸው፡፡ በሀገራችን ልዩ ልዩ አካባቢዎች ያሉ ባህላዊ የሙግት ስርዓቶችም እንደዚሁ ይለያያሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ጥንት በሰሜንና በመካከለኛው የሀገራችን ክፍል ይተገበር የነበረ "እሰጥ አገባ" ወይም ሙግት እንደ ምሳሌ እንመለከታለን፡፡

ዳኞች ወይም ሽማግሌዎች በዛፍ ስር ወይም በሜዳ ላይ ይቀመጣሉ፡፡ በፈቃዳቸው ወደ ችሎት የመጡ **ታዳሚዎችም** እንደዚሁ እርስ በርስ በመከባበር ፣ ለእድሜ ባለፀጋዎችና ለሹማምንት ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ቦታቸውን ይይዛሉ፡፡ በኋላ ላይም የፍርድ ትችት ይሰጣሉ፡፡

ሙግት ሲጀመር ከሳሽ በቀኝ ተከሳሽ በግራ ይቆማሉ፡፡ ሁለቱም አንድ አንድ እማኝ ይመርጡና እማኞቹ በበኩላቸው የመሀል ዳኛ **ይሰይማሉ**፡፡ በመቀጠል ከሳሽና ተከሳሽ የስርዓት(የስነ ስርዓት) ዋስ ይጠራሉ፡፡ ዋሶቹ መሐላ ከፈፀሙ በኋላም ክርክሩ ይቀጥላል፡፡



*(ስዕል ከ"ኢት. ልማዳዊ ህግ" መጽሐፍ የተወሰደ)*

## ሙግት

ከሳሽና ተከሳሽ እጀ ጠባብና ሱሪ ለብሰው፣ ኩታቸውን አደግድገው ይቀርባሉ። (ማደግደግ ማለት፣ ኩታ ወይም ሸማ በትከሻ ዞሮ ወገብ ላይ ይጠመጠምና የኩታውን አንዱን ጫፍ በቀኝ ወይም በግራ ትከሻ ማውረድ ነው)። ከሳሽ "እግዚአብሔር ያሳይዎ!" በሚል መግቢያ ክሱን ይደረድራል። ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ የካደ እንደሆነ፣ ከሳሽ ውርርዱን በማስቀመጥ ‹‹ብረታ!፣ ነጭ ማር፣ ነጭ ፈረስ፣ ሰጋር በቅሎ፣ ሰንጋ ወይም ሙክት እሰጥ!...›› በማለት፣ ዘንጉን በግራ እጁ ጨብጦ ፣ የቀኝ እጁን አመልካች ጣት ወደ ዳኛ ቀስሮ፣ ከፊት ወደ ኋላ ካፈገፈገ በኋላ፣ ክሱን ይደረድራል። ተከሳሽም ተመሳሳዩን ያደርጋል። ከዚያ **ብይን** ይሰጣል። ለምሳሌ፣ ላም የጠፋበት ሰው "አርዶ በልቷል" ብሎ ከጠረጠረው ሰው ጋር ሲከራከሩ "አለ" የተባለውንና የተከሳሹን ምላሽ በምሳሌነት እናንሳ፣

**ከሳሽ:-** ሳሜ ጠፍታ ከደጋ
ስከተል መጣሁ በደም ፍለጋ
ብደርስ በፍለጋ ከደጅህ
**ሙዳ** ስጋ ይዟል ልጅህ
ስለዚህ ሳሜን ትከፍላለህ።

**ተከሳሽ** :- ሳምህ ብትጠፋ ከደጋ
አንተም ብትመጣ ፍለጋ
ከደጄም ብታገኝ ሙዳ ስጋ
ከቤቴ በላይ አለ ተራራ
መዘዋወሪያው የጅብ ያሞራ
ከቤቴ በላይ ዛፍ አለ
በዛፉም አሞራ ያርፋል
በመንገዱም ጅብ ይሄዳል፡፡
አሞራና ጅብ ሲጣለፉ
ሙዳ ስጋ ቢተፉ
ነፍስ ያሳወቀ ልጅ ቢያነሳ
አያስከፍለኝም ነገርህን አትርሳ
ውርርድህን አንሳ፡፡

በዚህ መልኩ ሙግቱ ተካሂዶ ዳኞች ግራ ቀኙን አዳምጠው በእማኞች ትችትና አስተያየት ተደግፈው፣ ለተከሳሽ መልስ ዋጋ በመስጠት፣ ከሳሽን ተረቺ አደረጉ ይባላል፡፡

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. በምንባቡ የእስካሁን ክፍል ምን ምን ነጥቦች ተነሱ?
2. ምን አዲስ ነገር ጨበጣችሁ?
3. በቀጣዩ የምንባቡ ክፍል፣ ስለ ክርክር ምን የሚነሳ ይመስላችኋል?

በዘመናችን ክርክር፣ በከሳሽና በተከሳሽ መካከል ብቻ የሚደረግ አይደለም፡፡ በሌሎችም ዘርፎች በስፋት ይካሄዳል፡፡ ለምሳሌ ፖለቲከኞች፣ አንዱ ቡድን የራሱን አቋም በመደገፍና የሌላውን በመቃወም ይከራከራል፡፡ ህዝብ ዳኛ ይሆንና ፍርድ ይሰጣል፡፡ በፈራጅ ድምጽ መሠረትም አንዱ ባለድል ሌላው ተረቺ ይሆናል፡፡

በተማሪዎችም መካከል እንዲሁ በተቃራኒ ሀሳቦች ዙሪያ ክርክሮች ይካሄዳሉ፡፡ ተማሪዎች የሚያካሂዷቸውን እነዚህን ክርክሮች ዘርዘር አድርጎ መመልከት፣ ስለዘመኑ ክርክር መልካም ግንዛቤ ያስጨብጣል፡፡ የክርክሮቹን ሂደትም የዝግጅትና የክርክር ጊዜ ተግባራት በማለት በሁለት ደረጃ ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ ብዙዎቹ ጥሩ ተከራካሪ የሚባሉት፣ በዝግጅት ወቅት በቅድሚያ የመከራከሪያ ርዕሱን የሚመለከቱ ሀሳቦችን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች **ይቃርማሉ**፡፡ ይህም ባለሙያዎችን በማነጋገር ወይም ጽሑፎችን በማንበብ፣ ካስፈለገም ሁለቱንም መንገዶች በመጠቀም ሊሆን ይችላል፡፡

መረጃዎቹን ከሰበሰቡ በኋላ፣ ይበልጥ ጠቃሚ የሆኑትን በቅደም ተከተል በማደራጀት፣ በአጭሩ በትንሽ ወረቀት ላይ በማስታወሻ መልክ ያሰፍራሉ፡፡ ይህንን ማድረጋቸው፣ ላይ ታች ከመርገጥ ያድናቸዋል፤ የነገሮችን ፍሰት ጠብቀው ለማቅረብ ያግዛቸዋል፡፡ ተከራካሪዎች በየፊናቸው ለሚከራከሩበት ርዕሰ ጉዳይ የሚሆኑ መረጃዎችን ከሰበሰቡና ማስታወሻቸውን ካደራጁ በኋላ፣ ቀጣዩ ሥራቸው ልምምድ ይሆናል፡፡ ልምምድን የሚያካሂዱት በሁለት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው በየግል ራሳቸውን በመስታወት እያዩ መለማመድ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሌሎች ሰዎች ልምምዳቸውን አይተው አስተያየት እንዲሰጧቸው በማድረግ ይሆናል፡፡ በዚህ ሁኔታ ዝግጅት ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ዋና ዋናዎቹ የክርክር መድረክ ተግባራት ይገባሉ፡፡

ተከራካሪዎች ክርክራቸውን የሚጀምሩት ሰላምታ በመስጠትና ርዕሳቸውን በማስተዋወቅ ነው፡፡ አያይዘውም በተቀመጠው የሀሳብ ቅደም ተከተል እየተመሩ የክርክር ነጥቦቻቸውን ያቀርባሉ፡፡ ለዚህ አካሄዳቸው ማስታወሻ የያዙባት ትንሽ ወረቀት፣ ትልቅ ድርሻ አላት፡፡ ክርክራቸውን በወጉና በራስ የመተማመን መንፈስ ለማቅረብ ትረዳቸዋለች፡፡ እዚህ ላይ፣በራስ መተማመን የሚፈጠረው በቂ ዝግጅት ከማድረግ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል፡፡ ከተቃዋሚ ወገን የሚቀርቡ አስተያየቶችን **በጥሞና**

በማዳመጥ ማስታወሻ መያዝም፣ ሌላው ጠቃሚ የተከራካሪዎች ተግባር ነው:: ይህ የሚሆነው ለተዘረዘሩ ትችቶችና መቃወሚያዎች አፍራሽ ሀሳቦችን ለመስጠት ስለሚጠቅም ነው:: አላስፈላጊ እንቅስቃሴዎችን ከማድረግ መቆጠብ፣ ድምጽን ለታዳሚዎች በሚሰማበት መጠን መመጠንና እይታን ወደ አድማጮች ማድረግም ሌሎች የትኩረት ነጥቦች ናቸው::

ጥሩ ተከራካሪዎች ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ብቻ አያበቁም:: ለመከራከሪያ የሚያነሷቸው ፍሬ ሀሳቦች፣ ባጠቃላይም ክርክራቸው፣ አድማጮቻቸውን የሚስብ፣ ያድማጮቻቸውን ችሎታ ያገናዘበና የተከራካሪያቸውን ስብዕና የማይነካ፣ ማለትም ቅር የማያሰኝ፣ መሆኑን ያረጋግጣሉ:: ትግሉ ከተከራካሪያቸው ጋር ሳይሆን፣ ከሀሳቡ ጋር መሆኑን ያውቃሉና:: ንግግራቸው ከተሰጣቸው ጊዜ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ይጥራሉ:: ከርዕሳቸው እንዳይወጡ ይጠነቀቃሉ:: ሌላውን ወገን ሳያከብሩ መከበርን መናፈቅ አይቻልምና፣ ለተከራካሪና ለአድማጮች እንዲሁም ለዳኞች አክብሮትን **አይነፍጉም**:: ክርክራቸውን አጠቃለው ሲሰናበቱም ሁሉንም ታዳሚዎች ያመሰግናሉ:: የዳኞች ውሳኔ ምንም ይሁን ምን **በፀጋ** ይቀበላሉ::

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ:- ንባብ

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ::**

1. የጥንቱን ሙግትና የዛሬውን ክርክር የሚያመሳስላቸው ምንም ነገር የለም::
2. እሰጥ አገባ ሙግት ለዛሬው ክርክር ምሳሌ ሊሆን አይችልም::
3. ክርክር የሚካሄደው በከሳሽና በተከሳሽ መካከል ብቻ ነው::
4. ክርክር ውስጥ ከመገባቱ በፊት መረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ ነው::
5. ማስታወሻ እያነበቡ መከራከር የጥሩ ተከራካሪ ተግባር ነው::

6. "<u>ሬጋ</u> ባለና..." በሚለው ዓረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል የተፈለገውን መልዕክት እንዲያስተላልፍ ጠብቆ መነበብ አለበት።
7. አንድ ተከራካሪ ተቃዋሚውን ማክበር ያለበት ፍልሚያው ከተከራካሪው ጋር ሳይሆን ከሀሳቡ ጋር በመሆኑ ነው።
8. በጥንቱ ሙግት፣ ተመልካች የመተቸት መብት ነበረው።
9. በጥንቱ ሙግት፣ የመሐል ዳኛ የሚመረጠው በተከራካሪዎች አልነበረም።
10. በተማሪዎች ክርክር ተከራካሪው የመጨረሻውን የዳኞች ውሳኔ መቃወምና መንቀፉ የሚደገፍ ተግባር ነው።

**፪. ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. በቀረበው የእሰጥ አገባ ሙግት የከሳሹና ተከሳሹ ክርክር ምክንያት ምንድን ነው?
2. በእሰጥ አገባው ሙግት ዳኞች በሰጡት ብይን ትስማማላችሁ? ምክንያታችሁን ግለፁ።
3. በፖለቲከኞች ክርክር፣ "ህዝብ ዳኛ ሆኖ ፍርድ ይሰጣል" ሲባል፣ ፍርድ የሚሰጠው እንዴት አድርጎ ነው? አብራሩ።
4. በክርክር ወቅት መረጃዎችን በአጭር በአጭሩ በማስታወሻ መያዝ የሚያስፈልግበት ምክንያት ምንድን ነው?
5. በክርክር ጊዜ ጽፎ ማንበብ የማይመረጥበትን ምክንያት ግለፁ።
6. ክርክርን በተሰጠ የጊዜ ገደብ መጥኖ ማቅረብ ምን ጥቅም አለው?
7. "የነገሮችን ፍሰት ጠብቀው" የሚለው አገላለፅ ምን ያመለክታል?
8. ለልምምድ ይጠቅማሉ ተብለው የቀረቡት ሁለት መንገዶች ምንና ምን ናቸው?
9. አላስፈላጊ እንቅስቃሴ የሚባለው ምን አይነት እንቅስቃሴ ነው?
10. "ታዳሚዎች በኋላ ላይም የፍርድ ትችት ይሰጣሉ" ሲል መቼ? ማለቱ ነው?

**፫. የሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፣ አውዳዊ /አገባባዊ/ ፍቻቸውን ግለጹ፡፡**

***ምሳሌ፡-*** ትችት - አስተያየት

አለ - ተናገረ

| | | |
|---|---|---|
| 1. ለአብነት | 4. ቀሰረ | 7. ይቃርማሉ |
| 2. ታዳሚ | 5. ብይን | 8. በጥሞና |
| 3. ይሰይማሉ | 6. ሙዳ | 9. አይነፍጉም |
| | | 10. በፀጋ |

**፬. በቡድን ሆናችሁ በምንባቡ ውስጥ የተነሱትን ዋና ዋና ነጥቦች ለዩና፣ "በጣም ዋና ናቸው" የምትሏቸውን ነጥቦች አመልክቱ፡፡**

**፭. በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ መንስኤና ውጤት የያዙ ዓረፍተ ነገሮችን በመለየት በሰንጠረዥ አመልክቱ፡፡**

***ምሳሌ***

| ተ.ቁ | መንስኤ | ውጤት |
|---|---|---|
| 1 | በቂ ዝግጅት አደረገ | በራሱ የመተማመን ስሜት ፈጠረ |

## ክፍል ሁለት፡- ጽሕፈት

**፩. የሚከተሉትን ቃላት ትክክለኛ አውዳቸውን በመፈለግ አስገቡና አንቀፁን አሟሉ፡፡**

| | |
|---|---|
| መሠሪ | አግቦ |
| ማጥ | ደባ |
| ሲርድ | ፋይዳ |
| ባዝራ | አልባሌ |


ሰውየው ____1____ ይምሰል እንጂ፣ እንዲህ የዋዛ አይደለም፡፡ ሀብትን በተመለከተ ____2____ ከድንጉላ አለው፡፡ ታዲያ ምን ያደርጋል? በጐ የማያስብ ____3____ ነው፡፡ በሰው ላይ ____4____ ይፈጽማል፣ ____5____ መናገር ያዘወትራል፡፡ይህም መልሶ እራሱን ____6____ ውስጥ

ስለከተተው መውጫ አጥቶ ሲኳትን ይታያል:: ___7___ ለሌለው ነገር እንኳን ትኩረት ሰጥቶ ሲጨነቅና ሰውነቱ እንደቁጠማ ___8___ ይታያል::

**፪. መዝገበ ቃላትን በመጠቀም ለሚከተሉት ቃላት ፍች ከፈለጋችሁላቸው በኋላ ፍቻቸውን የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮች ከራሳችሁ አመንጭታችሁ ጻፉ::**

| | |
|---|---|
| 1. በሰና | 4. ቋፍ |
| 2. ተከነ | 5. ደብዛ |
| 3. አበሰ | |

**፫. በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ፣ ምንባቡን መሠረት አድርጉና ስዕላዊ መግለጫውን ወደ ጽሑፍ በመቀየር፣ የጥንቱን ሙግትና የዛሬውን ክርክር የየግልና የጋራ ባህርይ ዘርዝራችሁ በመፃፍ አቅርቡ:: እያንዳንዱ ክብም አንዱ በአንዱ ውስጥ ወይም አንዱ ከአንዱ ውጪ ለምን እንደዋለ አስረዱ::**




*መግለጫ*

- የጥንቱ ሙግት ባህሪ = ሀ
- የዛሬው ክርክር ባህሪ = ለ
- የጋራ ባህሪ = ሐ

**፬. ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ለሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሠረት ተመሳሳይ ፍች ሲሆኑ የሚችሉ ከአንድ በላይ ቃላትን ፃፉ::**

| | ቃል | ፍች |
|---|---|---|
| ምሳሌ | መነመነ | ከሳ፣ አነሰ፣ ቀነሰ |
| 1 | ቀና | |
| 2 | መሰናክል | |
| 3 | ሰፈረ | |
| 4 | ቆረጠ | |
| 5 | መጠጠ | |

**፭. ለተሰመረባቸው ተቃራኒ የሚሆኑ ቃላትን በክፍት ቦታዎቹ ላይ በማስገባት ዓረፍተነገሮችን አሟሉ::**

1. ትናንትና ያየሁት ነገር <u>ህልም</u> መስሎኝ ነበር፤ ነገር ግን _______ ሆኖ አገኘሁት::
2. እኔ <u>ሽቅብ</u> ስወጣ፣ እሱ ግን _______ ወረደ::
3. የአበበ ሰውነት <u>ደነደነ</u>፣ የሙባረክ ግን _______::
4. አባቴ <u>ለጋስ</u> ነው፤ አጎቴ ግን _______ ነው::
5. ከሌቦች አንደኛው፣ እጁን ለመስጠት <u>ፈቃደኛ</u> ሲሆን ሁለተኛው ግን _______ በመሆኑ ጉዳት ደረሰበት::

**፮. በቡድን በቡድን ሆናችሁ ከምንባቡ ውስጥ ለክርክር መመሪያነት የሚያገለግሉ ነጥቦችን ለይታችሁ አውጡ፤ ቀጥላችሁም በዚህ የመልመጃ ማብቂያ ላይ ከሰፈረው መመሪያ ጋር አነፃፅሩ::**

## የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ

- ርዕሱን በተመለከተ ከባለሙያ፣ ከጽሑፎች ወዘተ ሐሳብ መሰብሰብ፣
- ከተሰበሰቡት መረጃዎች ጠቃሚዎቹን ለይቶና በቅደም ተከተል አስተካክሎ በአነስተኛ ወረቀት መያዝ፣
- ክርክር ከመደረጉ በፊት በቂ ልምምድ ማድረግ፣
- ከክርክሩ በፊት አለባበስንና መሰል ነገሮችን ማስተካከል፣
- በክርክሩ አቀራረብ መግቢያ ላይ ሰላምታ በመስጠት ርዕስን ለአድማጮች ማስተዋወቅ፣
- የክርክሩን ፍሬ ሀሳቦች በቅደም ተከተል ማቅረብ፣
- ክርክሩን ረጋ ባለና በልበ ሙሉነት ማቅረብ፣
- ተገቢ ያልሆነ እንቅስቃሴ አለማድረግ፣
- ተቃዋሚ የሚሰነዝረውን ሀሳብ በማስታወሻ በመያዝ ተገቢ ምላሽ መስጠት፣
- ማስታወሻ የተያዘባትን ወረቀት ይፋ ሳያደርጉ መጠቀም፣
- ንግግርን ከአድማጮች ችሎታ ጋር የተጣጣመ ማድረግ፣
- ለክርክሩ የተሰጠውን የጊዜ ገደብ ማክበር፣
- የክርክሩ ሀሳብ ከርዕሱ እንዳይወጣ ጥንቃቄ ማድረግ፣
- ለተከራካሪ፣ ለአድማጭና ለዳኛ ተገቢውን አክብሮት መስጠት፣
- ክርክሩ ሲያበቃ ታዳሚዎችን አመስግኖ መሰናበት፣
- ዳኝነቱን በፀጋ መቀበል፣

፯. በ“ለ” ስር የሰፈሩ ውጤቶችን በ“ሀ” ስር ከቀረቡ መንስኤዎቻቸው ጋር አዛምዱ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. በጨለማ ተጓዘ | ሀ. ውጤት አልባ ሆነ፡፡ |
| 2. ነገር አሳበቀ | ለ. ላም ከነጥጃዋ ገዛ፡፡ |
| 3. አለታማ መሬት አረሰ | ሐ. የኢኮኖሚ አቅሙ ተናጋ፡፡ |
| 4. እንግዶች ጋበዘ | መ. እንቅፋት መታው፡፡ |
| 5. ትህትና ያበዛል | ሠ. ከአፍንጫው አርቆ አያስብም |
| 6. የንባብ ልምድ የለውም | ረ. ሰዎች አከበሩት |
| | ሰ. በልቶ ለበይ ሰጠው |
| | ሸ. ወንድማማቾቹ ተጣሉ |

፰. በክፍላችሁ የሚደረግን ክርክር እና መምህራችሁ የሚሰጡትን ገለጻ አዳምጣችሁ ማስታወሻ በመጻፍ ጥንድ እየሆናችሁ ተወያዩበት፡፡

፱. የየራሳችሁን መንስኤና ውጤት የያዙ ሶስት፣ ሶስት ዓረፍተነገሮች ፃፉ፡፡

## ክፍል ሦስት:- ንግግር

፩. በምንባቡ ውስጥ ያሉ ገጸባህርያትን ወክላችሁ ተሚገቱ፡፡

፪. የክርክርን አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያ ተከትላችሁ ክርክር አካሒዱ

## ክፍል አራት፣ ሰዋስው

፩. በምንባቡ ውስጥ የድምጽ መጥበቅና መላላት ባህሪ የሚያሳዩ ድምጾች ያሏቸው ቃላት አሉ፡፡ እነዚህን ቃላት በጥንድ በጥንድ እየሆናችሁ ድምጾቹ ሳልተውና ጠብቀው ሲባሉ የሚሰጡትን የፍች ልዩነት አመልክቱ፡፡

***ምሳሌ:-*** አሉ፣ ሲላላ→ ተናገሩ

ሲጠብቅ→ ተገኙ

## ክፍል አምስት፡- ስነፅሑፍ

**፩. ምሳሌውን መሰረት በማድረግ የቅኔዎቹን ህበረቃል፣ ሰምና ወርቅ ለዩ፡፡**

***ምሳሌ፡-*** ገና ስትወለድ ምን አጠነከራት፣
ድሃ አታውቅም እሷ እግዜር ከፈጠራት፡፡
**ህብረቃል** - ድሃ
**ሰም** - መዳህ አትችልም፡፡
**ወርቅ** ፡- ችግረኛ ሰው አይታ አታውቅም፡፡

1. ስጋ እበላ ብዬ የቆረጥኩትን ፣
   ላሳያችሁ መጣሁ እኔማ ጣቴን፡፡
2. ሁል ጊዜ ባሬራ ትበያለሽ ወይ፣
   አንዳንድ ቀን እንኳ ወጥ አትይም ወይ፡፡
3. መድኃኒት ፈልጉ ሰዎች እባካችሁ፣
   እናንተም፣ እናንተም፣ እናንተም ታማችሁ፡፡

**፪. በቡድን በቡድን ተከፋፈሉና ቅኔዎችን ከቅኔ መጻሕፍት፣ከጋዜጦች፣ ከመጽሔቶች ... በመሰብሰብ ህብረ ቃላቸውን፣ ሰምና ወርቃቸውን ተጠያየቁ፤ እርስ በርስም ተራረሙ፡፡**

## ማጠቃለያ

የምዕራፍ አስር ትኩረት በአመዛኙ ክርክር ላይ ነው፡፡ አንድ ተከራካሪ ለክርክር ሲነሳ በቅድሚያ መዘጋጀትና ሲከራከርም የክርክር መመሪያን ተከትሎ መከራከር ይጠበቅበታል፡፡

ዝግጅት የሚባለው መረጃ መሰብሰብን፣ ከተሰበሰቡት መርጦ በቅደም ተከተል መያዝንና መለማመድን ያጠቃልላል፡፡

በክርክር ወቅት ደግሞ ሰላምታ ሰጥቶና ርዕስን አስተዋውቆ መጀመር፣ ሐሳብን በቅደም ተከተል ማቅረብ፣ የተቃዋሚ ሐሳብን በጥንቃቄ አድምጦ ማስታወሻ መያዝና ምላሽ መስጠት፣ ንግግር የአድማጭን ችሎታ ያገናዘበ፣ የተከራካሪውን ስብዕና የማይነካ እንዲሆን መጠንቀቅ፣ ከርዕሱ አለመውጣትና ዳኝነትን በፀጋ መቀበል እንደ መመሪያ ልንወስዳቸው የሚገቡ ናቸው፡፡

ሌላው የምዕራፉ ትኩረት ቃላትን ይመለከታል፡፡ በዚህም በኩል ምንም አይነት የድምጽ ለውጥ ሳይኖራቸው የተለያዩ ፍችዎች ባሏቸው፣ እንዲሁም ጠብቀውና ላልተው የመነገር ባህሪ በተላበሱ ቃላት መልመጃዎች ሰርተናል፡፡ ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች የመፈለግ ሥራም አከናውነናል፡፡

ንግግርን አድምጦና ጽሑፍን አንብቦ ማስታወሻ መያዝ በተማረ ሰው ህይወት ውስጥ በየዕለቱ ሲያጋጥም የሚችል ተግባር እንደመሆኑ፣ ይህንን የሚመለከቱ መልመጃዎች ሠርተናል፡፡ ከምንባቡ መንስኤና ውጤት የያዙ ዓረፍተነገሮችን ለይቶ ከማውጣት ጋር ውጤቶችን ከመንስኤዎቻቸው የማጣመር ተግባርም አከናውነናል፡፡

ቅኔዎች ብዙውን ጊዜ በግጥም መልክ የሚቀርቡ፣ ግልፅና ስውር መልዕክቶችን አጣምረው የያዙ የሐሳብ ማስተላለፊያ መንገዶች ናቸው፡፡ ምዕራፉ የተጠናቀቀውም በቅኔዎች ህብረ ቃል፣ ሰምና ወርቅ ላይ ባተኮሩ መልመጃዎች ነው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በክርክር መመሪያነት የሚያገለግሉ ነጥቦችን ጻፉ::
2. በጥንቱ የክርክር ስርዓት (ሙግት) ላይ ያያችኋቸው ጉድለቶች ምን ምን ናቸው?
3. በዚህ ምዕራፍ በቀረበው ምንባብ ያልተዳሰሰው የመደበኛ ፍርድ ቤት ክርክር ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ክርክር በምን በምን ይለያል? በምንስ ይመሳሰላል ትላላችሁ?
4. ምንም የድምፅ ለውጥ ሳይኖራቸው ሁለት ሁለት ፍች ያላቸው አምስት ቃላት፣ በሚጠብቅና በሚላላ ድምፃቸው ምክንያት የተለያየ ፍች ያላቸው ደግሞ አምስት ቃላት ጻፉ::
5. የሚከተለውን ቅኔ ጎብረቃል፣ ሰምና ወርቅ ፈልጉ::

   ጠጅ እጠጣ ነበር ማለት አይቀርም ወይ፣
   እንዲያው የጠላ ሰው ያስታውቅ የለም ወይ::

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አሥር የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘባችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(✓)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (✓) | (?) | (x) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ያነበብኩትን ምንባብ ፍሬ ሃሳቦች ተረድቼ መግለጽ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 2 | ለቃላት አገባባዊና ቀጥተኛ ፍችዎች መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 3 | ቃላት ጠብቀውና ሳልተው ሲነበቡ የተለያየ ፍች እንደሚሰጡ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 4 | ንግግርን አድምጬ ወይም ጽሑፍን አንብቤ ቁም ነገሮችን በማስታወሻ መያዝ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 5 | ለክርክር መመሪያነት የሚያገለግሉ ነጥቦችን አውቄ በክርክር ውስጥ በስርዓት ተሣትፌአለሁ፡፡ | | | |
| 6 | በመንስዔና በውጤት የተደራጁ ዓረፍተ ነገሮችን ለይቼ አመልክቻለሁ፡፡ | | | |
| 7 | ለተለያዩ ቅኔዎች ህብረ ቃላቸውን በመለየት ሰምና ወርቅ ፍቻቸውን መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(x) ምልክቶችን ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# አባሪዎች

## ፩. ተጨማሪ የንባብ መጻሕፍት


### 1. ግጥሞች

መንግሥቱ ለማ (1955) *የግጥም ጉባኤ*:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

ፀጋዬ ገ/መድህን (1966) *እሳት ወይ አበባ*:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

ዓለማየሁ ዘውዴ (2003):: *ንስሐና ሌሎች ግጥሞች*::

ደበበ ሰይፉ (1980):: *የብርሃን ፍቅር*:: አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት::

### 2. ተውኔቶች

መንግሥቱ ለማ (1961) *የተውኔት ጉባኤ*:: አዲስ አበባ፣ ተራመድ ማተሚያ ቤት::

ተስፋዬ ገሠሠ (1961) *ሰቃው*:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

### 3. አጫጭር ልቦለዶች

ሰለሞን ለማ (1979) *የእግር እሳትና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች*:: አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት::

አብዱ ራህመቶና ሌሎች (1980) *አጫጭር ልቦለዶች*:: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት::

አምሳሉ አክሊሉ፣ (1981) *በዓለም የታወቁ አጫጭር ልቦለዶች*:: ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት::

### 4. ረጃጅም ልቦለዶች

ሀዲስ ዓለማየሁ (1958) *ፍቅር እስከ መቃብር*:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

ኃይለመለኮት መዋዕል (1982) *ጉንጉን*:: አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት::

## ፯. ማጣቀሻ መጻሕፍት


ባየ ይማም (2000) *የአማርኛ ሰዋስው፡፡* (ሁለተኛ እትም)፡፡ አዲስ አበባ፤እሌኒ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፡፡

- (2002) *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡* አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች፡፡

ተሰማ ሀ/ሚካኤል (1951) *ከሳቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

አለም እሸቱ (1992) *መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ፡፡* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

አምሳሉ አክሊሉና ደምሴ ማናህሎት (1982) *ጥሩ ያማርኛ ድርሰት እንዴት ያለ ነው?* አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

አምሳሉ አክሊሉና ዳኛቸው ወርቁ (1979) *የአማርኛ ፈሊጦች፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ዘሪሁን አስፋው (1992) *የስነጽሑፍ መሠረታውያን፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

የሻው ተሰማ(1996) *ልሳነ ብዕር ከመ ልሳን ሰብእ*፡፡ አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

ደረጀ ገብሬ (1996) *ተግባራዊ የጽሕፈት ማስተማሪያ፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ጌታሁን አማረ (1989) *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ፈቃደ አዘዘ (1991) *የስነቃል መመሪያ*፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚዎች፡፡

## ፫. ቃላት ከነፍቻቸው

| ቃላት | ፍቻቸው |
|---|---|
| ለበጠ | ሸፈነ፣ ደጐሰ፣ ጠረዘ |
| መስክ | በለምለም ሳር የተሸፈነ ሰፊ ሜዳ፣ መሬት |
| መረን | ባለጌ፣ ስርዓት የለሽ፣ ልቅ |
| ሜንጦ | ቆላፋ ብረት ወይም እንጨት |
| ርዕደ መሬት | የመሬት መንቀጥቀጥ |
| ሰየመ | ሾመ፣ መረጠ፣ |
| ሳቢያ | ምክንያት፣ ያረቄ ቀራሪ |
| ቋሳ | ቂም |
| ባተሌ | ፋታ የሌለው፣ በሥራ የተጠመደ |
| ባዝራ | ሴት ፈረስ |
| ተሰበጣጠረ | በየጣልቃው ገባ፣ ተበታተነ፣ ተራራቀ |
| ተነፈገ | ተከለከለ፣ መጥፎ ጠረን አመጣ |
| ተደራሲ | አንባቢ፣ አድማጭ፣ ተመልካች |
| ታዳሚ | ተጋባዥ፣ ተሳታፊ |
| ችብሃ | ለምለምነት የማይለየው ዛፍ |
| ንዋይ | ገንዘብ |
| ንፉግ | ስስታም |
| አለመ | ተመኘ፣ አነጣጠረ፣ ህልም አየ |
| አለባ | ፍሬ፣ የስራ ውጤት |
| አመነዠገ | እንደገና በማኘክ አደቀቀ፣ አመሰኳ |
| አሜካላ | በቆላና በወይናደጋ የሚበቅል የእሾህ ዓይነት |
| አምባረቀ | እንደመብረቅ ጮኸ |

| | |
|---|---|
| አሞካሸ | አቆላመጠ፣ አባበለ፣ አሞገሰ |
| አሸን | ክረምት አገቢና ከጉድጓድ እየወጣ ወደ ሰማይ በመብረር የሚርመሰመስ የምስጥ ዓይነት |
| አገገመ | ከበሽታው ሲድን ተቃረበ |
| አንዳ | የከብት ኮቴ |
| አደብ | ሥነስርዓት፣ ፀጥታ፣ ቅጣት(መቀጫ) |
| ኩታገጠም | ወሰንተኛ፣ ድንበርተኛ |
| ወረዛ | ረጠበ |
| ወበቅ | ሐይለኛ ሙቀት |
| ደንሳ | ወፍራም፣ ትልቅ |
| ድንጉላ | ወንድ ፈረስ |
| ጅብራ | ግንዱ ቀጥ ያለና ረጅም፣ ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ የዕጽዋት ዓይነት |
| ገልቱ | ሙያ የለሽ |
| ጥገት | የምትታለብ ላም |
| ፋይዳ | ጥቅም |
| ፎቄ | ቆራጭ ስለት |

## ፪. ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከነፍቻቸው

| ፈሊጣዊ አነጋገሮች | ፍቻቸው |
|---|---|
| ሀሳቡን ጣለ | ተረጋጋ |
| ሆዱን ሰጠ | ሚስጢሩን ገልጦ አወያየ |
| ልቡ ተነሳ | ለመሔድ ተቻኮለ |

| | |
|---|---|
| ልቡን ሰበረው | አሳዘነው |
| ልብ አጣ | ፈራ |
| መሬት አሚሸ | ሰው ባልተቀበረበት ድንግል መሬት ተቀበረ |
| ምራቁን የዋጠ | አስተዋይ፣ አዋቂ፣ ጭምት |
| ሰማይ ተደፋበት | ጨነቀው |
| ቃሉን ሰጠ | መሰከረ |
| በነገር ወጋው | በአሽሙር ተናገረው |
| ነብር ሆነ | ተቆጣ |
| አረፈ | ሞተ |
| አፉን አሚሸ | ቁርስ በላ፣ ምግብ ቀመሰ |
| እሳት ለብሶ እሳት ጐርሶ | ተናዶ፣ ተቆጥቶ |
| ከሰውነት ጉዳና ወጣ | ከሳ፣ ተጉሳቆለ፣ መነመነ |
| ደሙ ፈሳ | ተናደደ |
| ጠበቃ ወለደ | ጠበቃ አቆመ |
| ጥርስ ገባ | ተጠላ |
| ፍርድ ለበሰ | ሕግ ተማረ |

## ፭. የአማርኛ ቁጥሮች

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፩----1 | ፲፩----11 | ፲----10 | ፻፲፭----115 | ፴፻----3000 |
| ፪----2 | ፲፪----12 | ፳----20 | ፻፳----120 | ፵፻----4000 |
| ፫----3 | ፲፫----13 | ፴----30 | ፪፻----200 | ፶፻----5000 |
| ፬----4 | ፲፬----14 | ፵----40 | ፫፻----300 | ፹፻----8000 |
| ፭----5 | ፲፭----15 | ፶----50 | ፭፻----500 | ፼----10000 |
| ፮----6 | ፲፮----16 | ፷----60 | ፯፻----700 | ፪፼-----20000 |
| ፯----7 | ፲፯----17 | ፸----70 | ፲፻----1000 | ፱፼----90000 |
| ፰----8 | ፲፰----18 | ፹----80 | ፲፱፻፺----1990 | ፲፼----100000 |
| ፱----9 | ፲፱----19 | ፺----90 | ፳፻----2000 | ፳፼---200000 |
| ፲----10 | ፳-----20 | ፻----100 | ፳፭፻----2500 | ፻፻፻----1000000 |